# ክብረ ቅዱሳን

## ዜና ሐዋርያት

ከዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

ነቢያትን ትንቢት ያናገረ አምላክ፣ ወልደ አምላክ፣ ወልደ ማርያም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ፍጹም ሰው ሆኖ ከኃጢአት በስተቀር የሰውን ሥራ በመሥራት አደገ። በ፴ዓመቱም በባሪያው በቅዱስ ዮሐንስ እጅ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። በገዳመ ቆሮንቶስ ፵መዓልትና ፵ሌሊት ጾመ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ በዲያብሎስ ተፈተነ። ከዚህ በኋላ ወንጌልን ለማስተማር ሲጀምር ሐዋርያትን መረጠ። ሐዋርያ የሚለው ቃል "ሖረ" ከሚለው የግዕዝ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ለማስተማር የተላከ ማለት ነው።

የአሥራ ሁለቱም ሐዋርያትም ስም :- ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ፊሊጶስ፣ በርቶሎሚዎስ፣ ቶማስ፣ ማቴዎስ፣ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፣ ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ፣ ስምዖን ቀነናዊው በኋላ ናትናኤል የተባለው፣ ይሁዳ አስቆሮታዊ ናቸው።(ማቴ. ፲:፩-፬፤ማር. ፫:፲፫-፲፱፤ሉቃ. ፮:፲፫-፲፮)

፫ ዓመት ከ፫ወር ጌታ ከዋለበት እየዋሉ፣ ካደረበት እያደሩ፤ የቃሉን ትምህርት ሰምተዋል፣ የእጁን ተአምራት አይተዋል። ሆኖም ይሁዳ ከጌታ ይልቅ ገንዘብን ወዶ በመሄዱ፤ በምትኩ ማትያስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በመሆን በጸሎትና በዕጣ ተመርጦ ገብቷል።(የሐ.ሥ ፩:፲፭-፳፮)

የሐዋርያት የትውልድ ሐረግ ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ነው። ይኸውም ጴጥሮስና ወንድሙ እንድርያስ በአባታቸው ከነገደ ሮቤል ሲሆን በእናታቸው ከነገደ ስምዖን ናቸው። ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በአባታቸው ከነገደ ይሁዳ፣ በእናታቸው ከነገደ ሌዊ ናቸው። ፊሊጶስ ከነገደ ዛብሎን፣ በርቶሎሚዎስ ከነገደ ንፍታሌም፣ ቶማስ ከነገደ አሴር ማቴዎስ ከነገደ ይሳኮር፣ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ከነገደ ጋድ፣ ስምዖን ቀነናዊ የተባለው ናትናኤል ከነገደ ብንያም፣ ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ ከነገደ ዮሴፍ፣ ማትያስ ከነገደ ዳን ናቸው።

የአባቶቻችን የሐዋርያት የትውልድ ሐረግ ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቢሆንም፤ ወላጆቻቸው ከነገሥታት፣ ከመሳፍንት፣ ከባጸጎች ወገን ሳይሆኑ፤ ሠርተው የሚተዳደሩ፣ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ብቻ የነበራቸው ድሆች ነበሩ። ዓለምንና በውስጧ ያለውን ፈጥሮ የሚገዛ እግዚአብሔር፤ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ፤ እራሱን የሚያኖርበተ ሀብት፣ ንብረት፣ ጎጆ አልነበረውም። ተማሪዎቹም ከዕለት ጉርስ የተረፈ ሀብተ ሥጋ ስላልነበራቸው፤ እግዚአብሔር የድሆች አምላክ ወይም አምላከ ነዳያን እየተባለ ሲመሰገን ይኖራል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያው መልእክቱ "እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዚህን ዓለም ሰነፎችን መረጠ፣ ኃይለኞችን ያሳፍር ዘንድ የዚህን ዓለም ደካሞች መረጠ . . . ።" ብሏል (፩ቆሮ. ፩:፳፯-፳፱) እግዚአብሔር ዘመድ የሌላቸውን፣ የተናቁትን፣ ከቁጥር አይገቡ የነበሩትን በመምረጡ፤ ሰው በጥበቡና በኃይሉ፣ በትውልዱም በእግዚአብሔር ፊት መመካት እንደማይገባው በተግባር ጭምር አስገነዘበ።

ጌታ ሐዋርያትን ከመረጠ በኋላ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" እያላችሁ ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ አስተምሩ ብሎ አዘዛቸው። ሐዋርያትም ብሎ ከሰየማቸው በኋላ፤ ለጊዜው በምድረ እስራኤል ብቻ እንዲያስተምሩ ላካቸው። ለእግራቸው ጫማ፣ ለእጃቸው በትር፣ ቅያሪ ልብስና የዕለት ጉርስ እንዳይዙ መከራቸው፣ አስጠነቀቃቸው። በተጨማሪም ምን እንበላለን፣ ምን እንጠጣለን፣ ምን እንለብሳለን፣ ብንከሰስስ ምን እንመልሳለን ብለው እንዳይጨነቁ አዘዛቸው።

የዚህ ዓለም ወታደር ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ በቂ ስንቅና ትጥቅ እንሚሰጠው፤ ለቅዱሳን ሐዋርያትም ድውይ የሚፈውሱበት፣ ሙት የሚያስነሱበት፣ ጋኔን የሚያወጡበት፣ ለምፅ የሚያነጹበት ሙሉ ትጥቅ ሰጣቸው። አባቶቻችን የተላኩበት ዓለም በስንዴ የተመሰሉ ጻድቃንና በእንክርዳድ የተመሰሉ ኃጥአን የሚኖሩበት ስለሆነ፤ ለክፉዎች እንደ እባብ ጠቢባን፣ ለክርስቲያኖች እንደ ርግብ የዋህ ሆነው እንዲኖሩ መከራቸው፣ አስጠነቀቃቸው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በፅንስ የጀመረውን የማዳን ሥራ በሞቱ ፈጽሞ፤ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያርግበት ጊዜው ሲደርስ፤ የእርሱ በሥጋ መለየት ኀዘን እያዳያጸናባቸው "ልባችሁ አይደንግጥ፣ በእግዚአብሔር እመኑ፣ በእኔም እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ ማደሪያ፣ መኖሪያ አለ፤ አሁንም እንደምሄድ ቦታም እንደ ማዘጋጅላችሁ እነግራችኋለሁ፤ ወደ እኔም እውስዳችኋለሁ፤ እናንተም እኔ ካለሁበት ትኖሩ ዘንድ፤ ብሎ ጊዜ የማይሽረው፣ ዘመን የማይለውጠው ተስፋ ሰጣቸው። (ዮሐ. ፲፬:፩-፫) እነሱ ግን የጌታን ትዕግሥት፣ የአይሁድን ጭካኔ ተመልክተው፣ በፍርሃት ተውጠው፣ ተስፋ ቆርጠው ነበር። የሰውን ጥፋት የማይሻ ቸር አምላክ፤ ከሰው ተለይተው፣ ቤት፣ ዘግተው ሲያዝኑና ሲያለቅሱ በር ሳይከፈት ከዝግ ቤት ገብቶ፤ "ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደላከኝ እንዲሁ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ። ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ አላቸው።" (ዮሐ. ፳:፳፩-፳፪) በዚህ ቃል ዕንባቸው ደረቀ፣ በኀዘንና በጭንቀት የተዋጠ ልባቸው በደስታ ተሞላ። ፵ቀን ሙሉ ሲመክራቸውና ሲያስተምራቸው ቆይቶ በክብር ሲያርግ፤ ኃይል፣ ጽን የሚሆናቸውን መንፈስ ቅዱስ እስኪዋሐዱ ድረስ፤ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አስጠነቀቃቸው። በማይታበል ቃሉ እንደተናገረ ባረገ በ፲ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን (ጳራቅሊጦስን) ላከላቸው። ጳራቅሊጦስ የሚለው ስም የፅር ቋንቋ ሲሆን፤ ትርጉሙም የሚያጽናና፣ የሚያስደስት ማለት ነው።

አባቶቻችን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ፸፪ ቋንቋ ተገልጸላቸው፤ በእውቀት ጎለመሱ፣ ከብልየት ታደሱ፣ መከራ ሥጋ የማይፈሩ ሆኑ። ከዚህ በኋላ ዓለምን በዕጣ ተካፍለው፤ አምላክ ከሰማያት ወረደ፣ በድንግልና ተፀንሶ በድንግና ተወለደ፣ ወንጌልን አስተማረ፣ በአይሁድ እጅ ተገፈፈ፣ ተገረፈ፣ በመስቀል ተሰቀለ፣ ሞተ፣ መቃብር ክፈትሉኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በሥልጣኑና በኃየሉ ተነሣ፤ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ አረገ፣ ዳግመኛ ለፍርድ ይመጣል ብለው አስተማሩ። ለቤተክርስቲያን ሕግ አወጡ፣ ሥርዓት ደነገጉ። ነቢዩ ዳዊት



www.ethiopianorthodox.org

በመዝሙሩ "ውስተ ኩሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ" ትርጉሙም ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፤ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ ብሎ የተናገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ።

በትምህርታቸውና በትሩፋታቸው አልጫውን ዓለም አጣፈጡት። በክህደትና በጣዖት አምልኮ ለጨለመው የሰው ልቡና ወንጌልን አበሩለት። በዝሙትና በኃጢአት የረከሰውን የአዳም ዘር፤ በንጽሕናና በቅድስና አስጌጡት። ሞትን ይፈሩና ይሸሹ የነበሩ ሐዋርያት፤ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ብለው፣ የዚህን ዓለም መከራ ሥጋ ንቀው፣ አቃለው፣ በደስታ ተቀበሉት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ "የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል፤ ሕማም ነውን፣ መከራ ነውን፣ ስደተ ነውን፣ ረሀብ ነውን፣ መራቆት ነውን፣ ሰይፍ ነውን፣ ጭንቅ ነውን። መጽሐፍ እንዳለ አንተን ስላመንን ዘወትር ይገድሉናል፤ እንደ ሚታረዱ በጎችም ሆነናል። ነገር ግን እርሱ ወዶናልና ስዚህ ሁሉን ድል እንነሳዋለን። ነገር ግን አምናለሁ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያስተወን እንደሌ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትም ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ አለቆችም ቢሆኑ፣ የቀደሙትም ቢሆኑ፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይልም ቢሆን፣ ተራራም ቢሆን የክርስቶስን ፍቅር ሊያስተወን የሚልችል የለም።" በማለት እንደገለጸው፤ ቁልቁል ተሰቅለው፣ በሰይፍ ተከልለው፣ እንደ በግ ተገፈው፣ በእሳት ተጠብሰው፣ በድንጋይ ተወግረው ሰማዕትነትን ተቀበሉ። (ሮሚ. ፰:፴፭-፴፱)

ክርስቶስ በደሙ የመሠረታትን ቤተክርስቲያን ሐዋርያት፤ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደማቸውን አፍስሰው፣ ሥጋቸውን ቆርሰው ስለገነባት፤ ለመታሰቢያ እንዲሆናቸው የቤተክርስቲያን ጣራ ፲፪ አዕማድ (ምሰሶ) እንዲኖረው ሊቃውንት ወስነዋል። ጌታ የመሠረታትን፣ ሐዋርያት የገነቧትን ቤተክርስቲያን ለማፍረስ፤ አርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስ፣ ሰባልዮስና ሌሎችም ሞክረው አልተሳካላቸውም።

ሰውን ከሰው አናገናኝ ያለውን የቋንቋ፣ የጎሣ፣ የቅንዓትና የምቀኝነት ወንዝ ተሻግሮ፤ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር ከሚገኝበት ከተማ የሚያደርሰውን ድልድይ ገንብተው አልፈዋል። ተልኮአቸውን ሲጨርሱ "እኔ በርትቼ ግዳጄን ፈጽምኩ፣ ለሞትም ዕድሜዬ ደርሷል። ጽኑ ገድልን ተጋደልኩ፤ ዕድሜዬንም ጨረስኩ፤ ሃይማኖቴንም ጠበቅኩ እንግዲህስ የጽድቅ አክሊል ይቆየኛል፤ በዚያች ቀን እውነት የሚፈርድ እግዚአብሔር የሚሰጠኝ ለእኔ ብቻ አይደለም፤ የእርሱን መምጣት ለሚወዱ ሁሉ እንጂ" በማለት መስክረው አልፈዋል። (፪ጢሞ. ፬:፮-፰)

በአሁኑ ዕትማችን ስለ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለመግቢያ የሚሆነውን አቅርበናል። ወደፊት በየተራ ስለ አስተዳደጋቸው፣ ስለ ምርጫቸው፣ የት እንዳስተማሩ፣ ዜና ዕረፈታቸው መቼና እንዴት እንደሆነ፤ በዝርዝር ለማቅረብ እንሞክራለንና እግዚአብሔር በቸርነቱ ለቀጠሮ ያብቃን። አሜን።

## ላዩን ውብ ሆኛለሁ

ላዩን ውብ ሆኛለሁ ውስጤ ግን እረክሷል፣
ንጽህና የለም በኃዘጢያት ቆሽሿል።
አንደበቴ ኃያል ሁሉን አወቅሁ ባይ ነው፣
የተለሳለሰ ደግ መሳይ መርዝ ነው።
ለተመለከተኝ ላስተዋለኝ ሰው፣
ክንፍ እንጂ ምን ቀራት የማይል ማነው።
በጎ ስነ ምግባር ትህትና የሌለኝ፣
መስዬ የምኖር የስም ክርስቲያን ነኝ።
ፍሬ አልባ ወይን ነኝ የማላስደስት፣
አንተ ይቅር በለኝ አምላክ ምህረት።
መወደስ በከንቱ ከእንግዲህ ይብቃኝ፣
እውነተኛ እንድሆን ፈጣሪዬ እርዳኝ።

ሥርጉተ ገብርኤል
ከሮም ሰ/ት/ቤት

## የእምነት አርበኛው

ውስጡ ርሁሩህ ሆኖ፣
ውጩ ግን ስስታም፤
ሲያዩት ገራገር፣
ማረፊያ እንደሌለው
ሲዞር ካገር አገር፤
ቀኑም ሲመሽበት
ሲያጣ መጠለያ፣
ሲቆዝም ሲያነባ
ይመስላል ለሩቁ
ያጓ ማግበያ።
በፍጹም አይሻም
የሰውን ሽንገላ፣
እሰው ያልተነካ
ሁብት የሚበላ።
ጥሁበት ግን ሲያዩት
ከንፈር ያስመጥጣል፣
ቆዳው ተሸብሽቦ
ከከሳቱ ብዛት አጥንቱ ይታያል፤
እሱ ግን በመንፈስ
ህሊናው ደልቧል፤
ሰውም እንዳያውቀው
እራሱን ደብቋል።
ሀብት ንብረት አይል
ተአምር ነው ላየው፣
አይጨነቅ ለቤት
ብሉም ለመኖሪያው።
ከሰው ተለይቶ
ዱር ሲያድር አይፈራ፣
ተላምዶ ተቀቅሮ
ሲኖር ከአውሬ ጋራ።
ሰውነቱም ቻይ ነው
አየሩን ለምዶታል፣
በሽታም አያውቀው
ተስማሚ ሆኖታል።
ሐሩር አይወብቀው
ደጋውም አይበርደው፣
እሱ ማነው ብሎ
ላየው ላስተዋለው፣
ፀጉሩም ወርዶ ሲታይ
በሰው የተናቀው፣
መባለቂያ ሆኖ
ኋላ ግን ክብር ያለው፣
መስሎ ተመሳስሎ
የኖረው እንደኛው፣
ጻሚው ነው ሲገኝ
የእምነት አርበኛው።


ተድላ ፍጹም
ከቦሌ ቅዱስ ሚካኤል



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓምድ ቅዱሳን ተብለው ገድል የተፃፈላቸውና በስንክሳር ታሪካቸው የሚገኘው አባቶች በየዘመናቸው የሠሩት ተጋድሎና ያገኙት ጸጋ ከተሰጣቸው ቃልኪዳን ጋር ይተረካል።

# ዜና ሐዋርያት



# የቅዱስ ጴጥሮስ ታሪክ

በዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

የተከበራችሁ አንባቢያን ባለፈው እትማችን በዚህ ዓምድ ሥር ሐዋርያት የፈጸሙትን መልካም ተግባር ጠቅሰን ከዚህ እትም ጀምሮ የእያንዳንዳቸውን ታሪክ እንደምናቀርብ መግለ ጻችን ይታወሳል። በዚህ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የሐዋርያት አለቃ የሆነውን የቅዱስ ጴጥሮስን ታሪክ እናቀርባለን። ይህ ታሪክ ቅዱስ ጴጥሮስ ክትውልዱ እስከ እረፍቱ ያለውን መንፈሳዊ ሕይወቱን ያጠቃልላል።

## ትውልድና ደቀ መዝሙርነት

የቅዱስ ጴጥሮስ አገሩ በገሊላ ባሕር ዳር ከምትገኝ ቤተ ሳይዳ ከምትባል ሥፍራ ነው። (ዮሐ. ፩:፵፫) የአባቱ ስም ዮና ሲሆን ትውልዱም ከነገደ ሮቤል ነው። ዮናም ከዘብዴዎስ ጋራ የሥራ ባልንጀራ ሆኖ ዓሣ እያጠ መደ ይሸጥ ነበር። በኋላም ከነገደ ስምዖን የምትሆን አንዲት ሴት አግብቶ ቅዱስ ጴጥሮስን ወለደ። ቅዱስ ጴጥሮስ ከተወለደ በኋላ እንደ ሕገ ኦሪት ትዕዛዝ በስምን ተኛው ቀን ወደ ግዝረት ቤት አግብተው ስሙን በእናቱ ነገድ ስም ስምዖን ብለው ሰየሙት።

ዕድሜው ፭ዓመት ሲሆን እንደ አይሁድ ሥርዓት ሕገ ኦሪትን እየተማረ እንዲያድግ በቤተ ሳይዳ አጠገብ ወዳለችው ወደ ቅፍርናሆም ከተማ ተወሰደ። በዚ ያም ዘመን የቅፍርናሆም ከተማ ከባሕር ዳር በመመሥረቱ ለን ግድ ሥራ አማካይና የተመቸ ነበርና ብዙ አይሁዶች ይኖሩበት ነበር። በዚያም የሮም ጭፍሮች ስለነበሩ የነዚያ አለቃ ኢያኤሮስ የሚባለው አይሁድን ደስ ለማሰኘት ሲል በቅፍርናሆም እጅግ ያማረ ቤተ ጸሎትሠርቶላቸው ነበር። ነገር ግን ቅፍርናሆም በም ድር መናወጥ በጠፋች ጊዜ ጸሎት ቤቱ ፈርሶ ሕንፃው በመሬት ውስጥ ስለተቀበረ በአይሁድ ዘንድ ትልቅ ኀዘን ሆኖ ይኖሩ ነበር። (ማቴ ፲፩:፳፫፤ ሉቃ. ፯:፩-፲)

ከብዙ ምዕት ዓመት በኋላ ግን ላቲኖች መሬቱን ሲቆፍሩ ሕንፃውን አግኝተው አውጥተውት በዓለም የሚኖሩ አይሁድ ይህን ለማየት እየተሰበሰቡ ይመጡ ነበር። በዋጋም ለመግዛት እስ ከ 5ሚሊዮን ጊኒ እንስጥ ብለው ነበር። ነገር ግን ላቲኖች ለመ ሸጥ ስላልፈቀዱ ሃሳባቸው ሳይፈጸም ቀረ። ቅዱስ ጴጥሮስም በቅፍ ርናሆም ቤተ መቅደስ እየተማረ ካደገ በኋላ በዚያው ቤት ሠርቶ ኮንኮርዲያ (ጴርጴቱዋ) የምትባል ሚስት አግብቶ እንደ አባቱ እንደ ዮና ዓሣ እያጠመደና እየሸጠ ይኖር ጀመር።

ቅዱስ ጴጥሮስ እንድርያስ የተባለ ወንድም ነበረው። ሥራ ውም እንደ እሱ ዓሣ ማጥመድ ነበር። እንድርያስም አስቀድሞ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበርና ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር እያለ ሲናገር ሰምቶ ወደ ጌታችን ሄዶ ከተዋወቀ በኋላ ወንድሙን ቅዱስ ጴጥሮስንም ወስዶ አስተዋወቀው። (ዮሐ. ፩:፵፩-፵፫)

ጴጥሮስና እንድርያስም ዋና ሥራቸው ዓሣ ማጥመድ ስለነበር ለዚሁ ሥራቸው እንዲያመቻቸው አንድ ታንኳ ነበራቸ ው። አንድ ቀን ማታ ዓሣ ለማጥመድ በታንኳ ሆነው በባሕሩ ላይ መበባቸውን እየጣሉ ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ አድረው ምንም ሳያገኙ ተመለሱ። በማለዳ ግን ታንኳቸውን ሲያጥቡ የተበጠሰው መረባቸውንም ሲቀጥሉ ጌታችን መጥቶ በባሕሩ ዳር ቆመ ሕዝ ቡም ሁሉ ትምህርቱን ለመስማት ተሰብስበው ነበር። ጌታችንም የሕዝቡን ብዛት አይቶ ከሕዝቡ ጋር ፊት ለፊት እየተያየ ለማስተ ማር እንዲመቸው ወደ ጴጥሮስ ታንኳ ገብቶ በታንኳው ላይ ሆኖ ያስተምር ጀመር። ትምህርቱንም ከጨረሰ በኋላ ወደ ጴጥሮስ ዞር ብሎ "ስምዖን ሆይ መረብህን በባሕሩ ላይ ጣልና ዓሣ ያዝ " አለው። ጴጥሮስም "መምህር ሆይ ሌሊቱን ሁሉ ስንደ ክም አድረን ምንም አላገኘንም ነገር ግን አሁን በአንተ ቃል መበባችንን ወደ ባሕሩ እንጥላለን " ብሎ መረቡን በባሕሩ ላይ ለመጣል ተነሣ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ሌሊቱን ሁሉ ሲደክም አድሮ ዓሣ ሳያገኝ መቅረቱን እያወቀ ተስፋ ሳይቆርጥ የጌታንም ቃል ሳይጠራጠር እንደገና መረቡን በባሕሩ ላይ መጣሉ ትልቅ እምነት መሆኑን እናስተውል፤ ጌታችንም የሚያ ምን ሰው ሁሉን ማድረግ እንደ ሚችል ለማስረዳት ሲል በቅዱስ ጴጥሮስ መረብ ብዙ ዓሣ እን ዲገባ አደረገ፤ ከዓሣውም ብዛት የተነሳ መረቡን ለመጎተ ት የማይቻል ስለሆነ በሌላ ታንኳ ያሉትን ባልንጀሮቹን ጠርቶ እየጎተቱ አወጡለት።

ቅዱስ ጴጥሮስም በዚህ ነገር ድንጋጤ ስለያዘው ወደ ጌታችን ቀርቦ "አቤቱ ከዚህ እንድትሄድልን እለምንሃለሁ" ብሎ ተናገረ። ይህንንም ቃል መምህራን አባቶች በአንድምታ ሲተረጉሙት "በባሕሩ ውስጥ ያለውን እንደዚህ አድርጎ ካወቀ የእኔንም በልቤ ውስጥ ያለውን ኃጢአት አውቆ ይፈርድብኛል ብሎ ፈርቶ ነው" በማለት ያመሠ ጥሩታል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የጴጥሮስን ድንጋጤና ፍርሃት አይቶ "ስምዖን ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን እንድታ ጠምድ አደርግሃለሁና ምንም አትፍራ። ስለዚህ ሁለታችሁም ተከተሉኝ" አለው። ጴጥሮስና ወንዱሙም እንድርያስም ታንኳቸውን ወደ መሬት አስጠግ ተው ሁሉንም ትተው ተከትለውት ሄዱ። (ሉቃ. ፫:፩-፲፩)

## ቅዱስ ጴጥሮስ በባሕር ላይ ስለመሄዱ

ጌታችን አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አበርክቶ ፭ሺህ ሰዎች ባጠገበ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ትልቅ ደስታ አድርገው ነበርና "እንደዚህ ያለውን ጌታ ቢያነግሡት ቢራቡ ያበላል፣ ቢታመሙ ይፈውሳል፣ ቢሞቱ ያስነሣል" እያሉ እርስበርሳቸው ከተነጋገሩ በኋላ ለመንገሥም ፈቃዱ ባይሆን በግድ ይዘን እናነግሠዋለን ብለው አሳባቸውን ቆርጠው ነበር።

ጌታችን ግን በግድ ይዘው ለማንገሥ ማሰባቸውን ባወቀ ጊዜ የዚህን ዓለም ሥጋዊ መንግሥት ፈልጎ አልመጣም ነበርና ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እናንተ በመርከብ ሆናችሁ ወደ ማዶ ተሻግራችሁ ቆዩኝ ብሎ እርሱ ብቻውን ወደ ተራራ ላይ ወጥቶ ይጸልይ ጀመር።

ደቀ መዛሙርቱም እንደታዘዙ ወደ መርከብ ገብተው ሲሄዱ ብርቱ ነፋስ ስለተነሣ ባሕሩ ይናወጥ ጀመር። በአራተኛ ውም ሰዓተ ሌሊት ጌታችን ባሕሩን እየረገጠ መጥቶ ወደ መር ከቡ በቀረበ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ምትሐት (ጋኔን) መስሏቸው ደነገጡ፤ እርሱም "እኔ ነኝና አይዟችሁ አትደንግጡ" አላቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስም ጌታችን "እኔ ነኝና አይዟችሁ አትደንግጡ" ማለቱን በሰማ ጊዜ "አቤቱ አንተስ ከሆንክ ባሕሩን እየረገጥሁ ወደ አንተ እንድመጣ ፍቀድልኝ" አለው። ጌታችንም "ፈቅጄልሃ ለሁ ና" አለው። ቅዱስ ጴጥሮስም ከመርከብ ወርዶ ባሕሩን እየረገጠ ሲሄድ ከወደ ፊቱ ዓውሎ ነፋስ ሲመጣ ባየ ጊዜ እጅግ ፈራና ብቅ ጥልቅ ይል ጀመር። ሁኔታውም ስላስፈራው "ጌታ ሆይ አድነኝ" ብሎ ጮኸ። ጌታም እጁን ዘርግቶ ወደ መርከቡ አወጣው ወዲያውም "አንተ ሃይማኖተ ጎደሎ ለምን ትጠራጠ ራለህ" ብሎ ገሰጸው። ከዚያም በኋላ በመርከብ እንደሆኑ ወደ ማዶ ተሻገሩ። (ማቴ. ፲፬:፳፭-፴፩)

ቅዱስ ጴጥሮስ ከጌታ ትንሣኤ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እስኪታደስ ድረስ አንዳንድ ጊዜ ከባድ ፈተና ያገኘው ነበር በመጀመሪያ እምነቱን አጽንቶ አንተስ ከሆንክ ባሕሩን እየረገጥሁ እንድ መጣ ፍቀድልኝ ብሎ ከመርከብ ወርዶ ባሕሩን እየረገጠ ሄደ። በኋላ ዓውሎ ነፋስ ሲመጣ አይቶ በመፍራቱና በመጠራጠሩ በዚያ ገና በመንፈስ ቅዱስ ያልታደሰ እንደነበር ያስረዳል።

ብፁዕ ነህ መባሉና የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ስለ መመስከሩ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሊላን ባሕር አልፎ ሄዶ ቂሣርያ ከተማ በደረሰ ጊዜ "የሰውን ልጅ እኔን ሰዎች ማን ይሉኛል " ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። ደቀ መዛመርቱም "አንዳንድ ሰዎች ዮሐንስ መጥምቁ ነው፣ ሌሎችም ደግሞ ኤልያስ ነው፣ እኩሌቶቹ ኤርምያስ ነው፣ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል" ብለው መለሱለት። "እናንተስ ማነው ትሉኛላችሁ?" ብሎ ቢጠይቃቸው ቅዱስ ጴጥሮስ በመንፈሳዊ ድፍረትና በማያጠራጥር ሃሳብ ተነስቶ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ" ብሎ የክርስቶስን አምላክነት ገልጦ ተናገረ። ይህም የጌታችን ጥያቄ ደቀ መዛሙርቱ እስከዚህ ቀን ድረስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አለማወቃቸውን ያስረዳል።

ጌታችንም ቅዱስ ጴጥሮስ እውነተኛውን ነገር ገልጦ መናገሩን አይቶ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ይህን ነገር የሰማይ አባቴ ነው እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። አንተም ደንጊያ (ጴጥሮስ) እልሃለሁ። በዚህም ደንጊያ ላይ ቤተ ክርስቲ ያኔን እሠራለሁ። የገሃነምም ደጆች አይበረቱባትም" አለው።

ቅዱስ ጴጥሮስም ብፁዕ መባልንና ደንጊያ መባልን ማግ ኘቱ ብቻ ሳይሆን ይህን ነገር "የሰማዩ አባቴ ነው እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህም" ተብሎ በጌታችን አፍ የተነገረው ቃል ትልቅ ክብር የሚሰጠው ነው በመሆኑም "የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ " ብሎ የተናገረውን ቃል ሥጋዊ የሆነ መምህር ሳያስተምረው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ስለገለጠለት የክብሩን ትልቅነት ያስረዳናል። ጌታችንም በቂሣርያ "እኔን የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉኛል" ብሎ እስከ ጠየቀበት ጊዜ ድረስ የቅዱስ ጴጥሮስ ስሙ ስምዖን ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን በቂሣርያ አገር ከመሠከረ በኋላ ግን ስሙ በዕብራይስጥ ቋንቋ ኬፋ በጽርዕ ቋንቋግን ጴጥሮስ ተባለ። ትርጓሜውም በግዕዝ ኰኵሕ በአማርኛም ደንጊያ ጭንጫ (አለት) ማለት ነው።

ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ

ልዑለ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ "ቤተ ክርስቲያኔን በዚህ ደንጊያ ላይ እሠራለሁ" ብሎ ተናገረ። የዚህም ምሥጢሩ ሕዝ ብና አኅዛብ በአንተ ስብከት አምነው የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆኑ አደርጋለሁ ማለቱ ነው። ከዚህም ቀጥሎ በአንተ ላይ የተሠራችውን ቤተ ክርስቲያኔን ወአናቅጸ ሲዖል ኢይኄይልዋ (የገሃነም ደጆች አይበረታቱባትም) " ብሎታል። ትርጓሜውም በጭንጫ ድንጋይ ላይ ተመሥርቶ የተሠራው ቤት ዝናብ ቢዘንብ ጎርፍ ቢጎርፍ አያፈር ሰውም ነፋስም ቢነፍስ አይጥለውም ማለት ነው። ምሥጢሩ ግን በአንተ ስብከት ያመነችን ቤተክርስቲያን ከሀዲያንና መናፍቃን ተነ ስተው ሊያስቷትና ሊያጠፋት አይችሉም ማለት ነው።

ሁለተኛም ሃይማኖታችሁን ካዱ ለማየት ስገዱ የሚሉ አላውያን ነገሥታት በክርስቲያኖች ላይ ምንም መከራ ቢያጸኑባቸው ሃይማኖታቸውን አይክዱም ክርስቲያኖች አይጠፉም ማለት ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሮማ ከመሄዱ አስቀድሞ በኢየሩሳሌምና በሰ ማርያ፣ በልዳና በኢዮጴ፣ በአንጾኪያና በትንሿ እስያ፣ በጳንጦስና በቀጰዶቂያ፣ በገላቲያና በቢታንያ እነዚህንም በመሰሉ ሀገሮች እየዞረ አስተምሮ ሕዝብንና አኅዛብን በክርስቶስ አሳምኖ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንዲሠራ አድርጓል። የሮም ቤተክርስቲያን መሪዎቿ በኑፋቄ ትምህርቶቸው ተወግዘው ከመለየታቸው በፊት የሌሎች አገሮች አብያተ ክርስቲያናት ሰብሳቢ መሆኗ መንበሩ በዚያው እንዲሆን በጉባዔ ስለተወሰነ ነው እንጂ በአሁኑ የኑፋቄ አቋሟ አይደለም።

ከዚህ ቀጥሎ የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል ብሎ ለሥልጣኑ ኃይል የሚሆነውን ቃል ነግሮታል። እንደ ደንቡ ቢሆን መክፈቻ እሰጥሃለሁ ካለው የዘጋ ኸው የተዘጋ የከፈትኸው የተከፈተ ይሆናል ማለት ይመች ነበር። ነገር ግን በእስራኤል ዘመን የቤታቸው መዝጊያ እንደ ሰንሰለት በተያያዘ ብረት የሚቆለፍ ስለነበር መዝጊያውን ዝጋ ሲሉ እሰ ረው ከፈተው ሲሉ ፍታው ይሉ ነበርና ጌታችን በዚያው ልማድ ተናግሯል። ደግሞ ጌታችን በዚህ ደንጊያ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ስለማለቱ መክ ፈቻ እሰጥሃለሁ የሚል ቃል ጨመረበት እንጂ የምሥጢሩ ሃሳብ ግን ሕዝብንና አሕዛብን እያስተማርህ ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባበት ሥልጣን እሰጥሃለሁ ሲለው ነው።

የዚህ ዓለም ንጉሥ ወርቁና ብሩ ሌላውም የመንግሥቱ ዕቃ የሚቀመጥበትን የግምጃ ቤቱን መክፈቻ ፈጽሞ ለሚያምነው ሎሌው ይሰጥ እንጂ ለማያምነው ሌሎው አይሰጥምና ጌታችንም የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻ እሰጥሃለሁ ማለቱ ቅዱስ ጴጥሮስ በእርሱ ዘንድ እጅግ የታመነ መሆኑን ያስረዳል። ከዚህም በኋላ ጌታችን የእግዚአብሔር ልጅነቱን ብቻ ሳይሆን የሰውም ልጅነቱን ለደቀ መዛሙርቱ ለመግለጽና ለማስረዳት ፈቃዱ ስለሆነ የሰውም ልጅነቱን የመከራውንና የሞቱን ነገር እያነሣ ይነግራቸው ነበር። ቀደም ሲል ድውይ የፈወሰ፣ ሙት እያስነሳ፣ ጋኔን እያወ ጣ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ያሳያቸው ነበር እንጂ እጅግ የሚያስጨንቅ መከራና ኀዘን ወደፊት እንደሚያገኘው አልነገራቸውም ነበር። አሁን ይህን በነገራቸው ጊዜ እጅግ አዘኑ። ቅዱስ ጴጥሮስም አቤቱ ይህ ሊሆንብህ አይገባምና አያድርስብህ እያለ ይናገር ጀመር።

ጌታችን ግን ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም ለመምጣት የደረሰ በትዋና ሃሳቡ መከራ ተቀብሎና ሞቶ የሚያምኑበትን ሰዎች ሁሉ ለማዳን ስለሆነ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረው ነገር ደስ አላሰ ኘውምና ፊቱን ወደ ጴጥሮስ አዙሮ "አንተ ሰይጣን እንቅፋት ሆነህብኛልና የሰውንም እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብ ምና ከኋላዬ ሂድ" ብሎ የቁጣ ቃል ተናገረው። በአንፃረ በለስ ረግማ ለኃጢአት እንዳለው አሁንም በጴጥሮስ አንፃር ሰይጣንን ገሰጸው ማለት ነው። ለቅዱስ ጴጥሮስ ከላይ የተገለጹትን ማዕረጋ ት የማሰርና መፍታት ሥልጣን እስከ ሰማይ ድረስ እንደሚሆን ከበድ ያለ የተስፋ ቃል ነግሮት ነበርና ወዲያው በዚያው ቀን የመከራውንና የሞቱን ነገር ስለነገረው ቅዱስ ጴጥሮስ የተስፋው ቃል እንዳይቀርበት አስቦ "አቤቱ ይህ ባንተ ሊሆን አይገባምና አይድረስብህ ብሎ" ተናገረ። ጌታችንም የራሱን መከራና ሞት ብቻ ተናግሮ ዝም አላለም "ነገር ግን እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ሰውነቱን ይካድና መስቀሌን ተሸክሞ ይከተለኝ እያለ ደቀ መዛሙርቱ ወደፊት በመከራቸው እንዲበረቱ ገልጠ ነገራቸው።

ይህም የጌታችን አነጋገር ከዚህ ዓለም ንጉሥ አነጋገር ፈጽሞ የተለየ ነው። የዚህ ዓለም ንጉሥ ወደ ጦርነት ለመሄድ በሚነሳበት ጊዜ ለወታደሮቹ የጠላቱን ደካማነት የራሱን ብርታት እየገለጠ ድል አደርጋለሁ እያለ ይናገራል እንጂ ጠላቴ ይገድለ ኛል እናንተም ትሞታላችሁ ብሎ አይናገርም። ጌታችን ግን ሥራ ውን ሁሉ በእውነትና በግልጥ እየሠራ ያሳምን ነበር እንጂ በማታለልና በማባበል አልነበረምና ወደፊት የሚደርስ በትንና የሚደርስባቸውን መከራ ገልጦ ነገራቸው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን እጅግ የከበደ የመከራውን ነገር ቢሰሙም ጌታቸውን እየወደዱና እምነታቸውን እያጸኑ ከመሄዳቸው በቀር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ መከራ ተቀብሎ የሚሞት ከሆነ በእኛም መከ ራው የሚደርስብን ከሆነ ምን ያደርግልናል ብለው ጌታቸውን ለመክዳትና ተለይተው ለመሄድ አላሰቡም። ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ሆኖ ስለተሾመ እየዞረ እንዲያስተምሩ አድርጓል። (የሐ. ሥ. ፩:፲፫-፳፮)

በተጨማሪም ጌታችን በደብረ ታቦር ምሥጢረ መለኮቱን ከገለጸላቸው ደቀ መዛሙርት አንዱ ሲሆን "ሁሉን ትተን ተከተ ልንህ ዋጋችንስ ምንድነው? " ብሎ የጠየቀና መቃብሩን ሮጦ ሄዶ በማየት በእውነት መነሣቱን ያረጋገጠ፤ ከጌታም ትንሣኤ በኋላ ገሊላ ውስጥ ሲያስተምር በአንድ ቀን ስብከቱ አሳምኖ ሦስት ሺህ ሰዎችን ያጠመቀ፣ ብዙ ተአምራትን ያደረገ፣ የሐናን ያና የሰጲራን ድብቅ ሥራ የመረመረና ስምዖን



www.ethiopianorthodox.org

መሰሪ የተባለ ውን ጠንቋይ በትምህርተ መስቀል አማትቦ ያንኮታኮተ፣ በመጨ ረሻም በሮማ አደባባይ በ+ ዓ.ም ወንጌልን ሲሰብክ ቁልቁል ተሰቅ ሎ የሞተ ታላቅ ሐዋርያ ነው (የሐዋ. ፲፪:፩-፴፭፣የሐዋ. ፲፫፣የሐዋ. ፮:፩)

ሠለስቱ ምዕት በፍትሐ ነገሥት በአንቀጸ ሊቃነ ጳጳሳት ቅ/ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ እንደነበር በመንበሩም የሚቀ መጡ የሮማ ሊቀ ጳጳሳት የሌሎቹ ሊቃነ ጳጳሳት ሁሉ አለቃ ይሁን ብለ ዋል። ነገር ግን ከጉባዔ ኬልቄዶን በሃይማኖት ከተለያዩ ወዲህ የሠለስቱ ምዕት ቃል ቀርቶ ሁሉም የበላይ አለቃ ሳያደርጉ ለየራ ሳቸው የበላይ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነዋልና አሁን ከዚያ ወዲህ የሮማ ሊቀ ጳጳሳት የሌሎቹ ሊቃነ ጳጳሳት አለቃ አይደለም ቢባል የተገባ ነገር ይሆናል እንጂ ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ አልነበረም ማለት ትልቅ ስህተት ነው። ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ ፍቅሩን አሳይቶ እምነቱን በእርሱ ላይ አድርጎ የበጎቹ ጠባቂ እንዲሆን ከሾመው በኋላ ያሟሟቱንም ነገር በግልጥ እንዲህ ብሎ ነግሮታል።

እውነት እውነት እልሃለሁ ጎልማሳ በነበርህበት ጊዜ አንተ ወገብህን ታጥቀህ ወደ ምትወደው ትሄድ ነበር በሸመገልህ ጊዜ ግን እጅህን ታነሣለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደየማትወደውም ይወስድሃል አለው። እንዲህ ያለው በምን ሞት ሞቶ እግዚአ ብሔርን እንዲያመሰግን ሲያመለክተው ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እስቲለብስ ድረስ ወገብ ልቡናውን በፍርሃት ዝናር ታጥቆ እኔ የናዝሬቱን ኢየሱስን አላውቀውም ብሎ ክዶ ነበር። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከለበሰ በኋላ ግን ወገብ ልቡናውን በፍርሃት ዝናር መታጠቁ ቀርቶ ለመስቀል ሞት እጁን ዘርግቶ ስለሰጠ የልቡ ትዕግሥትና ብርታቱ ወደማይወደው ወደ ሞት ወስዶታልና በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱን ሲያመለክተው ሌላው ያስታጥቅሃል ብሎ ነገረው።

ጌታችን እኔ ቸር ጠባቂ ነኝ ቸር ጠባቂም ስለ በጎቹ ሕይወ ቱን ይለውጣል ብሎ እንደተናገረ። ሕይወቱን ስለ በጎቹ ለውጦ በመስቀል ተሰቅሎ ነበርና ቅዱስ ጴጥሮስም በጎቼን ጠብቅ ተብሎ ከተሾመ ገኋላ እንደ ቸር ጠባቂ በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱ በመከ ራው ሁሉ ጌታውን መምሰሉን ያስረዳናል። (ዮሐ. ፲:፲፩፤ ፪ጴጥ. ፩:፲፫-፲፬) ስለሆነም ቅዱስ ጴጥሮስ በልዳ፣ በኢዮጴ እየዞረ ወንጌል አስተምሮአል ጣቢታንም ከሞት አስነስቶአል። ቆርነሌዎስንም አሳምኖአል ይህም ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ጴጥሮስ ከሐዋርያት ጋር ሆኖ የመጀመሪያውን የሐዋር ያት ሲኖዶስ ፍርድ (ውሳኔ) ሰጥቶአል። (የሐዋ. ፲፭:፩) የጻፋቸ ውም መልእክታት ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያው መልእክቱን የጻፈው አይሁድ ለሚያሳድዱ አቸውና መከራ ላጸኑባቸው ለተመረጡና በስደት ለተበተኑ ክርስቲያኖች ነበር። ለተመረጡ ማለቱም አይሁድ እስጢፋኖስን በደንጊያ ወግረው በገደሉት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች መከራውን ፈርተው ከእውነተኛው ሃይማኖት ተናውጠው ነበርና እነዚህ በተሰደዱበት አገር መከራውን ታግሰው በሃይማኖታቸው ጸን ተው መቆየታቸው የተመረጡና የታደሉ መሆናቸውን የሚያ ስረዳ ስለሆነ ነው (፩ጴጥ. ፩:፩)

ሁለተኛው መልእክቱን የጻፈበት ምክንያት ደግሞ ኔሮን ቄሣር በክርስቲያኖች ላይ በጠላትነት ተነስቶ ክርስቲያኖች ሁሉ እየተያዙ እንዲፈረድባቸው አዋጅ ነግሮ ነበርና ቅዱስ ጴጥሮስም በእስያና በሌሎችም እስከ ባቢሎን ወሰን ባሉት አገሮች እየዞረ ሲያስተምር በእስያም የሚኖሩ ክርስቲያኖች በዚሁ በኔሮን ቄሣር አዋጅ ምክንያት ዕለት ዕለት ልዩ ልዩ መከራ እየመጣባቸው ተጨ ንቀው ሳሉ በዚህ ላይ ደግሞ የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ጊዜ ስለተመቻቸላቸው ክርስቲያኖች በሚኖሩበት መንደር እየገቡ በሐሰት ትምህርታ ቸው የክርስቲያኖችን ልብ ያስጨንቁ ጀመሩ። ዋና ዋና ትምህርቶቻቸውም እነዚህ ነበሩ።

፩. ሠራዒ መጋቢ የለም (እግዚአብሔር የለም) ፍጥረትም ሁሉ በልማድ ይኖራል።

፪. ትንሣኤ ሙታን የለም የሰው ዘር እንዲሁ በምድር ተዳፍኖ ይቀራል

፫. ሕልፈተ ሰማይ ወምድር የለም ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይተካል ሰማይና ምድር ግን ለሰለዓለም ይኖራሉ እንጂ ማለፍ የለባቸውም ማለት ነው።

፬. አንድ ጊዜ ካመኑና ከተጠመቁ በኋላ ምግባር ትሩፋት አያስፈልግም የሚሉ ነበሩ። በመጨረሻም አክርጶስና አስታብዮስ የሚባሉ የሮም መኳንንቶች ሊያስገድሉት በመከሩበት ጊዜ ከሮም ወጥቶ ሲሸሽ ጌታችን በዕለተ ዓርብ መስቀሉን እንደተሸከመ ሆኖ በከተማው በር ላይ ተገለጸለት ቅዱስ ጴጥሮስም ጌታ ሆይ በኢየሩሳሌም አይሁድ እንደሰቀሉህ በሮም ም እንደዚያው ልትሰቀል መጣህን? ብሎ ቢጠይቀው በእኔ ፋንታ የሚሰቀልልኝ ካላገኘሁ እሰቀላለሁ እንጂ ምን አደር ጋለሁ ብሎ ስለመለሰለት አትፍራ ተሰቀል ሲለኝ ነው እንጂ ብሎ ተመልሶ ወደ ከተማ ገብቶ ያስተምር ጀመር። ስለዚህ በሞት ተለይቼ የምሄድበት ወቅት መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮኛል አለ ብለው አባቶች ተርጉመውታል። (ገድለ ሐዋ. ተመልከት)

ጌታችን መስቀሉን ተሸክሞ በአንቀጸ ሮም ለቅዱስ ጴጥሮስ ተገለጠለት የተባለውን ቃል አንዳንድ መምህራን በዓይነ ሥጋ ታይቶታል ብለው ይናገራሉ ነገር ግን እውነ ተኛው ራዕይ ከሆነ በዓይን እንደመታየት ያህል ይቆጠራልና ልዩነቱ ጥቂት ነው። ከዚህም በኋላ እንደ ዘመናችን ሐሰተኞች መምህራን በተንኮልና በሐሰት ጥበብ ሳይሆን የክርስቶስን ኃይሉንና ክብሩን እንዲሁም የባሕርይ አምላክነቱን በደብረ ታቦር በዓይኑ ያየ አብም የምወ ደው ልጀ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክር በጆሮው የሰማ መሆኑን ይነግራቸዋል። (፪ጴጥ. ፩:፲፮-፲፯) ይህንንም ቃል ሊያስረዳ የፈለገው ለትምክህትና ለኩራት ሳይሆን በጆሮ ሰማን ከሚሉ ምስክሮች ቃል ይልቅ በዓይን አየን የሚሉ ምስክሮች ቃል የሚታመን መሆኑን ለማስረዳት ብሎ ነው።

ከዚህም አያይዞ የሐሰት መምህራን በመካከላቸው እንደገ ቡባቸው ማወቁን ገልጦ ጽፎላቸዋል እነዚህንም የመሰሉ የሐሰት መምህራን ቀድሞም በነቢያት ዘመን እንደነበሩ አስረድቶአቸዋ ል። (፪ጴጥ. ፪:፩-፫)በኤልያስ ጊዜ ፰፻፶ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት በአሞፅ ጊዜ አሜስያስ፣ ካህነ ቤቴል፣ በኤርምያስ ጊዜ እንጳስኮር ፣ በሚክያስ ጊዜ ሴዴቅያስ ወልደ ካህናን ነበሩ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል የነቢያት ቃል የታመነ መሆኑ ተመሰከረ እንጂ የነዚያ ሐሰተኞች ነቢያት ቃል የታመነ መሆኑ አልተመሰከ ረም።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ለበደሉ መላእክት፣ ለሰብአ ትካትና ለሰብአ ሰዶም ወገሞራ እንኳን አልራራም እያለ አብራርቶ ጻፈላቸው። (፪ጴጥ. ፪:፬) ከዚህም ቀጥሎ እግዚአብሔር ኖኅን ከማየ አይኅ፣ ሎጥን ከእሳት ማዳኑን እየተረከ ነግሮአቸዋል። ሐሰተኞቹ መምህራን ለጻድቃ ቃጋ ለኃጥእ ፍዳ የሚሰጥ ሠራዒ መጋቢ እግዚአብሔር የለ ብለው አስተምረው ነበርና ሠራዒ መጋቢ እግዚአብሔር ከሌለማ ሰብአ ትካትና ሰብአ ሰዶም ሲጠፉ ኖኅና ሎጥ ድነው የለምን በማለት ሠራዒ መጋቢ መሆኑን አስረድቶአቸዋል።

ደግሞ ሕልፈተ ሰማይ ወምድር የለም ብለው አስተምረው ነበርና ከዚህ አያይዞ ሰማይና ምድር እንዲያልፉ ጽፎላቸዋል። ስለ ዘመኑም መዘግየት እንዳይጠራጠሩ በእግዚአብሔር ዘንድ አንዲቱ ቀን እንደ አንድ ሺህ ዓመት ናት ብሎ ሰማይና ምድር የሚያስፉት ባልታወቀ ሰዓት በድንገት መደረጉን አስረድ ቶአቸዋል። ደግሞም ሰማይና ምድር ካለፉ በምን ሥፍራ እንደ ምንስ ሆነን እንኖራለን የማለት ሀሳብ እንዳ ይነሳባቸው አዲሱን ሰማይና አዲሲቱን ምድር እንወርሳለን የሚል ቃል ጨምሮ ጽፎላ ቸዋል። (2ጴጥ. ፫:፫-፲፫) ከዚህም በኋላ ወዳጆቼ ሆይ በሰነ ፎች ትምህርት ተመርታችሁ ከጽኑ ሃይማኖታችሁ እንዳትወድቁ ተጠ ንቀቁ ብሎ ከልብ የመነጨ ምክሩንና ትምህርቱን ጽፎ ልኮላቸዋል።

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስ በታናሺ እስያ እየዞረ በቃሉ እያስተማረ በመልዕክትም እየጻፈ ምዕመናን በሃይማኖት እንዲጸኑ በመከራም እንዲታገሱ እየመከረ ካጽናናቸው በኋላ በሮሜ ለክርስቶስ መስክሮ እግዚአብሔርን የሚያመሰ ግንበት ዘመኑ ሲደርስ በ፷ (፷፮) ዓ.ም ወደ ሮሜ ገብቶ ያስተምር ጀመረ።

ኔሮን ቄሣርም በዚያ ዘመን በክርስቲያን ላይ የሚቃጠለው የቁ ጣው እሳት ገና አልበረደለትም ነበርና ቅዱስ ጴጥሮስን አሲዞ አሰረው። ቅዱስ ጴጥሮስ ግን በምሴተ ሐሙስ ጌታው በተያዘ ጊዜ ስለደ ረሰበት ፈተና ጌታውን አላውቀውም ብሎ መካዱ ብቻ ዘወትር ትዝ እያለው ያዝን ነበር እንጂ በመታሰሩ አላዘነም ነበር። ይህንም በምሳሌ ለማስረዳት ይቻላል። አንድ ሎሌ በጌታው ላይ ክፉ ሥራ ከሠራ በኋላ ምንም ጌታው ቢታረቀውና ይቅርታ ቢያደርግለት የጌታውን ፊት በሚያይበት ጊዜ ሁሉ ማፈሩና መደንገጡ አይቀርም።

ቅዱስ ጴጥሮስም በመከራ ቀን ጌታውን አላውቀውም ብሎ ስለመካዱ ምንም ንስሐ ቢገባ ንስሐም በመግባቱ ይቅርታ አግኝ ቶ ምንም ረአይኬ አባግዕየ ተብሎ ቢሾም እስኪሞት ድረስ ጸጸቱና ኀዘኑ አልወጣለትም ነበር መባሉ ስለዚህ ነው። ኔሮን ቄሣርም ቅዱስ ጴጥሮስን አሲዞ ካሰረው በኋላ ወደ አካይያ ዘምቶ ነበርና በዘመቻው ድል አድርጎና ደስ ብሎት ወደ ሮሜ ሲመለስ አረማውያን የሆኑ መኳንንቱን ደስ ለማሰኘትና አማልክቱን ለማክበር ሲል የቅዱስ ጴጥሮስም ሞት በመስቀል እንዲሆን ታዘዘ።

ሐዋርያው በመስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት መፈረዱን በሰማ ጊዜ ጌታችን በአመሰ ልሕቀ ባዕድ ያቀንተከ ሐቌከ ወይ ወስደከ ኀበ ኢፈቀድከ ብሎ የነገረው ቃል ትዝ አለውና አላውቀውም ብዬ መካዴን ሳያስብብኝ በዚህ ፍጹም ይቅርታ ያደርግ ልኛል በማለት እጅግ ደስ አለው። የሚሰቀልበትም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ከግዞት ቤት አውጥተው ሲወስዱት ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ እኩል እንዳልሆን ራሴን ወደ ታች ዘቅዝቃችሁ ሰቀሉኝ ብሎ ለመነ።

በሮማውያን ሥርዓት ቅጣት የተፈረደበት ወንጀለኛ የሮሜ ተወላጅ የሆነ እንደሆነ የወንጀሉ ትልቅነት እየታየ ግርፋት ወይም ሞት ይፈረድበታል እንጂ ባንድ ወንጀል ሁለት ቅጣት አይፈረድበትም። የውጭ አገር ወንጀለኛ የሆነ እንደሆነ ግን ቅጣቱ ግርፋት እንደሆነ ገርፈው አስራት ይጨምሩበታል ቅጣቱ ሞት እንደሆነ ግን አስቀድመው ገርፈው በኋላ በመስቀል ወይም በሌላ መሣሪያ ይገድሉታል።

ሰቅለው ገደሉት። የተሰቀለውም ሐምሌ ፭ቀን ነው። ይህንን ዕለት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን በታላቅ መንፈሳዊ የጸሎት ሥነሥርዓት ታከብረዋለች።

ይህም ቅዱስ አባት ከሞተም በኋላ መርቄሎስ የሚባለው ደቀ መዝሙሩ ከመስቀል አውርዶ እንደ አገሩ ልማድ ሬሳውን በወተ ትና በወይን አጥቦ ሽቱ ቀብቶ በነጭ ልብስ ገንዞ ማር በተመላ ሣጥን ውስጥ አግብቶ አሁን ዛሬ ቫቲካን በሚባለው ሥፍራ ቀበረው።

በአጠቃላይ የሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ታሪክ ከረጅሙ በአጭሩ ከላይ ተዘር ዝሮአል። አንድ ጊዜ ባጠፋው ጥፋት ሁል ጊዜ እየተጸጸተ የጌታውን ይቅር ባይነት ተስፋ ሳይ ቆርጥ በመረረ እንባእ ንስሐው ይቅርታን ያገኘ ለዘመኑ ተነሣሀያን (ንስሐ ለሚገቡ) ጥሩ ምሳሌ በመሆኑ ብፁዕ ነህ ተብሎአል።

ነቢዩ ዳዊትም "ብፁዕ ብእሲ ዘአኅለቁ ሎቱ እግዚአብሔር ኃጢአቶ" (መዝ. ፴፩:፩-፪) መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱ የተከደነችለት በደሉን የማይ ቆጥርበት ሰው ምስጉን ነው እንዳለው እስከሞት ድረስ ፍቅሩን በመግለጽ ሰማዕትነ ትን በሮማ አደባባይ እስከተቀበለበት ጊዜ ድረስ የአይሁ ድን ዱላ ፈርቶ በቀላሉ አላውቀ ውም ብሎ ለካደው አምላክ በቆራጥነትና በታማኝነት ቁልቁል እስከመሰቀል የደረሰ ታላቅ ሐዋርያ ነው።


ጸሎቱና በረከቱ በእኛ በሕዝበ ክርስቲያኖች ላይ አድሮ ይኑር አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓምድ ቅዱሳን ተብለው ገድል የተፃፈላቸውና በስንክሳር ታሪካቸው የሚገኘው አባቶች በየዘመናቸው የሠሩት ተጋድሎና ያገኙት ጸጋ ከተሰጣቸው ቃልኪዳን ጋር ይተረካል።

# ዜና ሐዋርያት



## የቅዱስ እንድርያስ ታሪክ

በዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

የተከበራችሁ አንባብያን ባለፈው እትማችን የቅዱስ ጴጥሮስን ታሪክ፤ ከትውልዱ እስከ መመረጡና በሰማዕትነት እስካረፈበት ድረስ ያለውን ባጭሩ ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ ስለ ቅዱስ እንድርያስ ታሪክ ይዘን ቀርበናል። ከሁሉም በላይ ለእርሱ ለፈጣሪያችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይግባውና ሐዋርያትን በአጽናፈ ዓለም ያጸና አምላክ እኛንም ያጸናን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከሆነ በኋላ በ፴ዓመቱ ደቀመዛሙርቱን ስለመረጣቸው እስኪሞት ድረስ ፍቅሩን እየገለጠ፣ ተአምራቱን እያሳየ ያኖራቸው ነበር። ከሞተም በኋላ መከራውን ታግሰው ወንጌልን እያስተማሩ ሕዝቡን ስላሳመኑለት፤ ክብራቸው እንዲበዛላቸው እርሱ በተጠራበት ስም ሁሉ እንዲጠሩ አደረገ። ምንም እንኳን የእርሱ ክብር የባሕርይ፣ የእነርሱ ክብር የጸጋ ቢሆን በስሙ መጠራታቸው ብቻ ትልቅ ክብር ነው።

የቅዱሳን ሁሉ መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ (ኢሳ . ፶፮:፬-፮፤ ፩ቆሮ. ፫:፲፩) የማይጠፋ ስምን ሰጣቸው።

ጌታችንም ሐዋርያትና ክርስቲያን ሁሉ በስሙ እንዲጠሩ ማድረጉ፤ ቸርነቱና ደግነቱ ከዚህ ዓለም ንጉሥ ቸርነትና ደግነት ልዩ መሆኑን ያስረዳናል። የዚህ ዓለም ንጉሥ ምንም ቸርና ደግ ቢሆን ላገለገለው ሉሌው ርስት ይተክለዋል፣ ገንዘብ ይሰጠዋል እንጂ እንደእኔ ንጉሥ ተብለህ ተጠራ ብሎ አይፈቅድለትም። እገሌ የእገሌ ወገን ነውና መንግሥት ይገባዋል ብሎ ያነግሣል እንጂ፤ ከተራውና ከተናቀው ሕዝብ መካከል መርጦ አያነግሥም።

ጌታችን መድኃኔዓለም ክርስቶስ ግን አይሁዳዊ ፣ አሕዛብ ነው፣ ቀይ ፣ ጥቁር ነው፣ ጌታ ፣ ባርያ ነው፣ እያለ ሳይለያይና ሳያደላ፤ በስሙ አምነው በመንፈሳዊ መንግሥቱ የሚኖሩት ክርስቲያኖች ሁሉም እንዲነግሡና ነገሥታት ተብለው እንዲጠሩ አደረገ። በቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ መከራና ሞት ከኢየሩሳሌም የተሰደዱ ምዕመናን ሁሉ ወደ ፊንቄና ወደ ቆጵሮስ፣ ወደ አንጾኪያም ደርሰው አይሁድን ብቻ ያስተምሩ ነበር። ግማሾቹ ግን ወደ አንጾኪያ ደርሰው አረማውያንንም አስተምረው በክርስቶስ አሳመኑ። በአንጾኪያም ክርስቲያን ተብለው እስኪጠሩ ድረስ ሐዋርያት አርድዕት፣ ቢጽ ኀሩያን፤ ምዕመናን፤ እየተባሉ ሲጠሩ ይኖሩ ነበር።

ከዚያ ወዲህ ግን በክርስቶስ ያመኑ ምዕመናን ሁሉ፤ ክርስቲያን ተብለው እንዲጠሩ ሥርዓት ሆነ። መሰብሰቢያቸውም ቤተክርስቲያን ተባለ። የቤተክርስቲያን አዕማድ ሐዋርያት ከተባሉትና የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት በመደበኛነት ካዩትና ከተማሩት ልዑላን ቃል ሐዋርያት መካከል አንዱ ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ነው።

የቤተሳይዳው ተወላጅ ቅዱስ እንድርያስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ ማለትም በማርቆስና በሐዋርያት ሥራ አራተኛው ተራ፣ በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌል ደግሞ በሁለተኛው ተራ፤ ስሙ ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን ከሌሎች ሐዋርያት መጠራት አስቀድሞ የተጠራ ሐዋርያ ነው። በዚህም ምክንያት ፕሮቶክሊቶስ እየተባለ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይጠራ ነበር።

ይህ ሐዋርያ የትውልድ ቦታው እንደ ወንድሙ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተሳይዳ ሲሆን፣ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋራ ዓሣ እያጠመደ በቅፍርናሆም ኖረ። ቅዱስ ጴጥሮስንም በመጀመሪያ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀረበው (ያስተዋወቀው) እሱ ነው። ቅዱስ እንድርያስ ይህን ብቻ ሳይሆን ከግሪክ ሀገር መጥተው የነበሩትን ሰዎች፤ ከፊልጶስ ጋር ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አቅርቧል። (ዮሐ. ፲፪:፳-፳፪) በዚህም የሕዝብ ወዳጅ ሐዋርያ ይባላል። በመጀመሪያ ግን ቅዱስ እንድርያስ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር እንደነበር እናነባለን። (ዮሐ. ፩:፴፭-፵፪) ወንጌላዊው ማርቆስ ደግሞ፤ ከወንድሙ ከጴጥሮስ ጋር ዓሣ ሲያጠምድ አግኝቶት እንደጠራው ጽፏል። (ማር. ፩:፲፮-፳) ቅዱስ እንድርያስ ስለ ነገረ ምጽአት ጥያቄ ካቀረቡት ደቀመዛሙርት ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ በጸሎት ከሚተጉት ጋር የተቆጠረ ነው። (የሐዋ. ፩:፲፬)

ሐዋርያት ሀገረ ስብከት ሲከፋፈሉ ለቅዱስ እንድርያስ ቢታንያ፣ መቄዶንያና አካያይ እንደደረሰው ታሪኩ ይናገራል። በገድለ ሐዋርያትም ተጽፎ እንደምናገኘው እስካትያ፣ አርጣያናስና ሉቅስ በተባሉ የከፉዎች አላውያን አገሮች ሳይፈራና ሳያፍር እስከ ሞት ድረስ የወደደውንና ፍቅሩን በገለጸለት "ፈጣሪ ወገባሬ ኩሉ አምላክ" በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስተምሯል፤ አላውያን ነገሥታትና አሕዛብ በእነርሱ ፍልስፍናና አምልኮ ጣዖት ውስጥ ነግሦ የሚኖር ሰይጣን ከሚያሳያቸው ከንቱ እውቀት ውጪ የሆነ አዲስ የሕይወት ትምህርትና ተአምራት ማድረጉን ቀጠለ።

ሂዱና አሕዛብን አስተምሩ በአብ በወልድ በመ ንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ ብሎ አጽናኝ መን ፈስ ቅዱስንና ከፍርሃት ነፃ የሚያደርጋቸውን ኃይልና ጸጋ የተጎናጸፈው ክቡር ሐዋርያ፣ የአሕዛብን ልቦና በሚስብና በተረዳ ሁኔታ በኃያላን ነገሥታት ፊት መሰከረ።

### የሐዋርያው ትምህርትና ያደረጋቸው ተአምራት :-

ቅዱስ እንድርያስ በመንፈስ ቅዱስ በታደለ እንደበቱ በሚሰጠው ትምህርትና በሚያሳየው ተአምራት፤ የሀገሩ ሰዎች ልባቸው ስለተነካ ከበፊቱ ክፋት ተመልሰው ወደ ፍጹም ሰብዓዊ ርኅራኄ፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ በአሕዛብ ዘንድ ጎልቶ ከሚታይ ምቀኝነትና ቅንዓት ወደ መንፈሳዊ ቅንዓት፣ ከሕገ ጣዖት ወደ አማናዊት ሕገ ወንጌል፣ ከሰይጣን ቁራኛነትና ግዞት ወደ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ለውጦና በክፋትና በኃጢአት መራራነታቸውን በትምህርት አጣፍጦ፤ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የመዳን ምሥጢር ሊደረግላቸው እንደሚችል አሳመናቸው። ከዚህ በኋላ በሰይጣን ታውሮ የነበረው ዓይናቸው ተከፈተ።

ቅዱስ እንድርያስንም በፍጹም ፍቅር ተቀበሉት በወንጌልም አመኑ። በእርሱና በፈጣሪያቸው ላይ ያደረሱትን በደል አስበው ንስሐ ገቡ። "ከጠላት ሰይጣን አድነንን፣ ወደ ፈጣሪህም

ጸልይልን፤ አንተም ከዚህ ሀገር አትሂድብን" እያሉ ተማ ጸኑት።

ከሀድያን ግን ይህ ሐዋርያ በሚሰጠው ትምህርትና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሚያደርገው ተአምራት፤ ብዙዎችን ደቀመዛሙርት በማድረጉ፤ ሰይጣናዊ ቅንዓት አደረ ባቸው። ቅዱስ እንድርያስንም ካለበትና የሰላምን ወንጌል ከሚያ ስተምርበት ቦታ ሄደው እርሱንና ደቀመዛሙርቱን በእሳት ለማቃጠል ከማሰባቸውም በላይ፤ ቅዱሱን " ትምህርት አቁም ልን እንቢ ካልክ ግን በእሳት እናቃጥልሃለን ከሀገራችንም ውጣልን" ብለው አመጹበት።

ሐዋርያውም ሳይፈራና ሳያፍር እንዲህ ሲል ተናገረ። "እናንተ ሰይጣን ያደረባችሁ አመጸኞች፤ ከኃጢአታችሁ ተመ ለሱ። ጣዖታትን አጥፉ። በሰማይም በምድርም ከጌታችን ከኢየ ሱስ ክርስ ቶስ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም" በማለት ያስተም ር ነበር። በዚህ ጊዜ የክርስቶስን ስም በድፍረት መሳደብ በመ ጀመራቸው፤ ቅዱስ እንድርያስ እጅግ በጣም ተቆጥቶና አዝኖ "ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ልመናዬን ስማኝ፤ እነዚህን ቅዱስ ስምህን የሚሳደቡ ክፉዎችና አመጸኞች ሰዎች እሳት ከሰ ማይ ወርዳ ታቃጥላቸው" ብሎ ሲጸልይ እሳት ከሰማይ ወርዶ ፈጃቸው።(ማር.፲፮:፲፬-፲፰፤የሐዋ. ፲፫:፰-፲፪)

ይህ ተአምር በየሀገሩ ስለተሰማ ለጊዜው የሐዋርያው ትምህርት ተሰሚነትና ክብርን አገኘ። ይሁንና ለክፋትና ምቀኛ ነት የማይታገሱ አሕዛብ ተቃውሟቸውን ቀጠሉ። እነዚህም ከእ ሳት የተረፉ የሦስቱም አገሮች ሰዎች የክፋትና የሐሰት ሁሉ አባት የሆነው ሰይጣን በልባቸው አድሮ ዓይናቸው ስለታወረ፤ ቅዱሱንና የሰላምና የአንድነቱን ሐዋርያ "እርስ በእርሳችን ለያየን ሰላም ነሳን" ሲሉ በከንቱ ከሰሱት። አብዝተውም ከደበ ደቡት በኋላ በምን ዓይነት አገዳደል እንደሚገድሉት ምክረ ሞት እስከሚጨርሱ ድረስ፤ ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው እስር ቤት በማቆየት ብዙ መከራን አደረሱበት። በተለይም ፓትረንስ በተባለች ሀገር ሲያስተምር አስሮት የነበረውን አገረ ገዢውን ከደዌው ፈውሶት ነበር። ሆኖም ከእርሱ ቀጥሎ በነበ ረው ኢግያስ በተባለው አገረ ገዥ ትእዛዝ በ ፳ ዓ.ም ታኅሳስ ፬ ቀን የቁልቁሊት ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ ሞቷል።

በእስር ቤት እያለ ከእረፍቱ በፊት ወደ ፈጣሪው ጸለየ። የጸለየውም ጸሎት " ስምንቱ ቤተ አይሁድ በውስጣቸው አንድነት ሳይኖር ጌታዬን ለመቃወምና ለመስቀል በከንቱ የሕ ይወትን እራስ የመዳናችንን ቁር ክርስቶስን በመክሰስ ሕብረት እንደፈጠሩ ሁሉ፤ እነዚህን ከሦስቱ አህጉር ተውጣጥተው እኔም ከዚህች ምድር በከንቱ ሕይወቴን አጥፍተው ደሚን ለማፍሰስ የሚቅበዘበዙትን ከሀድያን ስምህም ይፈራ ዘንድ ከዚህ በፊት በኤልያስ ዘመን፣ ከዚያም በእኔ ልመና በዚህች አገር ተፈጽሞ የነበረው ቅጣት አሁንም ይደገም። እሳትም ከሰ ማይ መጥቷ ትብላቸው" ሲል ጸለየ። በዚህ ጊዜ ጌታችን መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ "የምወድህ ደቀመዝሙሬ ቅዱስ እንድርያስ ሆይ በእነዚህ ክፉ ሰዎች አትማረር ስለስሜ መራብህን፣ መጠማትህን፣ መታሰርህን፣ መንከራተትህን ተመለከትሁ፤ ደስ ይበልህ ሩጫኽን ፈጽመሃል። በዚህ ቦታ ሰማዕትነትን በመቀበል ያዘጋጀሁልህን የክብር አክሊል ተቀ ዳጅተህ እንደ አንተ ከሚወዱኝ ጻድቃንና ቅዱሳን ጋር መን ግሥተ ሰማያትን ትወርሳለህ" ብሎ ቃልኪዳኑን ሲነግረው እጅግ ተደሰተ።

ቀሪውን ሌሊትም በጸሎት አነጋ። በሦስተኛው ቀንም ከእስር ቤት አውጥተው ለመስቀል ሞት አበቁት። የተሰቀለ ውም እንደ ጌታ ዓይነት መስቀል ላይ ሳይሆን በራሱ ፈቃድና ጥያቄ ቁልቁል ሰቀሉኝ በማለት ጠየቀ። እነርሱም በነገራቸው ዓይነት ሰቀሉት። ይኸውም ከጌታ ጋር መተካከልን ስላልወደደ ለትህትና ነው። ስለ ርትእት ሃይማኖቱ ክብርት ነፍሱን ለወጠ፤ ያስተማረው የወንጌል ብርሃን ግን በዓለም ሲነገር ይኖራል።

በአጠቃላይ ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታ የነበረውና በሐዋርያት ዘንድ እንደ አስተባ ባሪ የሚቆጠር ነበር። የጌታችንን ማደሪያ ካየ በኋላ ተመልሶ ለወንድሙ ለቅዱስ ጴጥሮስ በመንገሩና የምሥራቹን ለቤተሰቡ በማብሠሩ "የቤተሰብ ሐዋርያ" እየተባለ የሚጠራ ሲሆን፤ ከጌታችን ሥር ቁጭ ብሎ ከጠዋት እስከማታ ሲማር ለቆየው ሕዝብ የሚሆን ምግብ ጌታ አምጡ ባለ ጊዜና ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ለዚህ ሁሉ የሚበቃ የለም ብሎ በመለሰ ጊዜ፤ ቅዱስ እንድርያስ ግን አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘውን ጎበዝ (ወጣት) ወደ ጌታ በማቅረብ አስባርኮታል። (ዮሐ. ፮:፰-፱) በዚህም ምክንያት የወጣቶች ሐዋርያ እየተባለ ይጠራል።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ እንደገ ለጠው ቅዱስ እንድርያስ ጥንት ስኩቴስ ዛሬ ሩሲያ በተባለው ቦታ ወንጌልን ሰብኳል። የቁስጥንጥንያ የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ መሆኑንም ቅዱስ ማርቆስና የእስክንድርያ ትምህርት ቤት በሚለውና የቅዱሳን መዝገበ ቃላት ውስጥ በእንግሊዝኛው ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል።

ከላይ በታሪኩ እንደገለጽነው፤ ግሪክ ውስጥ በአካያይ አውራጃ ጳጥሪስ በተባለች ቦታ በዚያው ቀበሩት። በመጨረሻም በ፫፻፶፯ ዓ.ም ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የዚህን ሐዋርያ አጽም ከተ ቀበረበት ከጳጥሪስ ወደ ቁስጥንጥንያ አስመጣው በ፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ሬጉሎስ የተባለ መነኩሴ የቀኝ እጁን ጣቶች ወደ ስኮትላንድ ወሰዳቸው። የጳጥሪስ ከተማ ነዋሪዎች ደግሞ በ፲፪፻፲ዓ.ም ከአስለብ ሕዝቦች ወረራ ሙከራ ጀምሮ ቅዱስ እንድርያስን ተራዳኢ ሐዋርያቸው አድርገው ይማ ጸኑበታል።

የጥንት ቤዛንታውያን የቁስጥንጥንያን መንበር ሊቀ ጵጵስና ሲያትቱ (ሲተርኩ) ከቅዱስ እንድርያስ ጋር ያያይዙ ታል። እነሱ እንደሚሉት ቅዱስ እንድርያስ የመጀመሪያዎቹን የአቮታሂስ ጳጳሳት ስለሾመ ቁስጥንጥንያ ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባሕል አላት። የደቡብ ኢጣሊያ ሰዎች ቁስጥን ጥንያ ውስጥ ይገኝ የነበረው የቅዱስ እንድርያስን አጽም ወደ ሀገራቸው ወስደውት ነበር። ጳጥሪስ ይገኝ የነበረው የሐዋር ያው የቅዱስ እንድርያስ ራስ ፩ሺ፬፻፷፪ ዓ.ም በቱርክ ኢስማን ወረራ ጊዜ በመጨረሻው የቤዛንታይን ቄሣር ቶማስ ፓሎንሎ ጉስ ወንድም አማካይነት ወደ ሮም ተልኮ እንዲጠበቅ ተደር ጓል። ይኸም ለ፭፻፪ ዓ.ም ያህል ሲኖር መስከረም ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ.ም በሮምና በግሪክ መካከል ለተደረገው መቀራረብ ምልክት ይሆን ዘንድ ለስፓትራስ ከተማ ተመልሶ ተሰጥቷል።

ሐዋርያትን በትድስናው የቀደሰ በመከራቸው ያጸና አምላክ እኛንም ከክፉ መከራ ይሰውረን የዚህ ቅዱስ ሐዋርያ በረከት ይደርብን አሜን።


<u>ምንጭ</u>:- ገድለ ሐዋርያት

ዜና ሐዋርያት

መጽሐፈ ስንክሳር

የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት

ቤተክርስቲያንህን እወቅ

## ቅዱስ ያዕቆብ

"ከመደሞኪቶሙ ጋር ቃል ኪዳኔን ሰደደማሁ" (መዝ. ፹፰:፫)

የተከበራችሁ አንባብያን የቅዱሳን ሐዋርያትን ክብር፣ ታሪክ ገድልና በዓላቶቻቸው መቼ እንደሚ ከበሩ በየተራ በምናወጣበት በዚህ ዓምድ የቅዱስ ጴጥሮስንና የቅዱስ እንድርያስን ታሪክ ባለፉት እትማችን አቅርበናል። በተለይም እነዚህ ሐዋር ያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተጎናጽ ፈው የምሥራች የወንጌልን ቃል በማስተማር ያሳለፉትን ዜና ሕይወታ ቸውንና ዕረፍታቸውን መግለጻችን ይታወሳል።

በዚህ እትማችን ደግሞ የእ ግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ የሆነው ንና በቃል ኪዳን የከበረውን የዮ ሐንስን ወንድም የያዕቆብን ታሪክ እንመለከታለን።

በዚህ ጽሑፍ የምንገል ጸው አምላክ ሕያዋን መድኃኒ ታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ(ማቴ.፳፪:፴፪) ስለ ወንጌልና ስለ ክቡር ስሙ በብዙ መከራ የሥጋ ሞት የተቀበሉትን ሐዋርያት እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ. ፳፰:፳) በማለት ክብራቸው በምድር ላይ የሚቀር ሳይሆን በሰ ማይ እጽፍ ድርብ እንደሚሆንና በ፲፪ቱ ወንበር ተቀምጠው ለምስ ክርነት እንደሚቀርቡ ስለተ ነገረላቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ታሪክ ነው። (ማቴ. ፲፱:፳፯) ስለዚህ አሁንም የስብከታቸው ድምፅ በልባችን ሰሌዳ ተጽፎ ለበጎ ምግባር እንዲያነሳሳንና በተዋህዶ ሃይማኖታችን እንዲያጸናን ጸሎታቸውና አማላጅነታቸው አይለየን።

በነቢያት ተነግሮ የነበረውን ነገረ ድኅነት ካስተማሩትና እንደ በግ ከታረዱት ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ያዕቆብ ነው። በዚህ ስም የሚ ጠሩ ቅዱሳን ብዙዎች ሲሆኑ በመጽ ሐፍ ቅዱስና በቤተክርስቲይን ታሪክ ገድላቸው ከተጻፈላቸው ጥቂቶቹ

ሀ) የአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት ያዕቆብ(ዘፍ. ፴፭:፳፫)

ለ) ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ (ወልደ ቀለዮጳ)


ሐ) የአረጋዊው የዮሴፍ ልጅ የያዕቆብን መልዕክት የጻፈው(ማቴ. ፲፫:፶፬ -፶፰)

መ) በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ማተብ (ማዕተብ) በአንገት ላይ ማድረግን ያስጀመረው የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ደቀ መዝሙር የነበረው ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ ናቸው።

ያዕቆብ ማለት የስሙ ትርጉም ተረከዝን ይይዛል ማለት ነው ይህ ትርጉም የተሰጠው የአሥራሁለቱ ነገድ አባት ለነበረው የብሉይ ኪዳኑ ያዕቆብ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ የመጀመሪያ ሥራው ከአባቱ ጋር ዓሣ ማጥመድ ነበር። በገሊላ ባሕር አጠገብ ከአባታቸው ጋር ዓሣ ሲያጠምዱ ከወንድሙ ከዮሐንስ ጋር ከነቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥለው ተጠሩ ወዲያውም አባታቸውንና መረባቸውን ትተው ጌታን ተከተሉት እርሱና ወንድሙ ዮሐንስ ፍላጎታቸውና ሥራቸው ታላቅና ኃይል የተሞላው ስለነበር(ሉቃ.፱:፲፱፣፶፬፤ማር.፲:፴፺) ቦኤኔርጌስ (የነጎድጓድ ልጆች) ተብለዋል። ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ በሐዋርያት ስም ዝርዝር ውስጥ ከቀዳሚዎች ጋራ ይጠራል (ማቴ.፲:፰፤ሉቃ.፮:፲፫፤የሐዋ.፩:፲፫) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን፣በቤተ ኢያኤሮስ ተአምራትን፣በጌቴሴማኒ ምሥጢረ ጸሎትን ሲገ ልጽ አብሮ ነበር። ሚያዝያ ፲፯ ቀን የዘብዴዎስን በዓለ ዕረፍት በሚያወሳው በስንክሣር ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ የ፲፪ ነገድ ቋንቋና እንዲሁም የእንስሳትን የአራዊትን ቋንቋ ይረዳ እንደነበር፤እንዲሁም ሐዋርያው ያዕቆብ ለምዕመናን በየአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ይተጋና መልካሙን እምነታቸውን ሲያይ በአብ በወልድ በመ ንፈስ ቅዱስ ስም ያጠምቃቸው እንደነበር ተገልጿል።ከ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በስ ማዕትነት ከማረፉ በፊት እስፔይን ውስጥ እንደሰበከም የሚናገሩ አንዳንድ መዛግብት ተገኝ ተዋል።

ሄሌኒዝም ከጥንቱ የግሪክ ፍልስፍናና ከምሥራቃውያን ሕዝቦች ባህል ጋር የተቀላቀለ አዲስ ባህልና ልማድን የያዘ የሥልጣኔ ዓይነት ነበር። ስለዚህ ነው ሄሮድስ




አግሪጳ ከሌሎች ባህል ወስዶ ወንጀለኞችን ከጨዋታ ቦታ እንዲታገሉ ያደርግና የሰዎ ችን ስቃይ እንደ መዝናኛ ይቆ ጥር የነበረው። በስንክሣርም እንደተጻፈው አግሪጳ አይሁ ድን ደስ ለማሰኘትና ከፈሪሳ ውያን ድጋፍ ለማግኘት በማ ሰብ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎ ስን በ፵፬ ዓ.ም አንገቱን እን ዲሰየፍ ሲያደርግ ቅዱስ ጴጥ ሮስንም አሳሰሮት ነበር።

የፍልስጥኤሙ ተወላጅና ታዋቂው የቤተክ ርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳ ብዮስ ዘቂሳርያ ስለ ቅዱስ ያዕቆብ ሞት ሲጽፍ ያዕቆብን የማረከው አይሁዳዊ በሐዋርያው ትምህርትና የእምነት ጽናት በመማረኩ እርሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ማመኑን ስለመሰከረ ሁለቱም ወደ ፍርድ ሸንጎ ተወሰዱ። በጉዞ ላይ እንዳሉ አይሁዳዊው ሐዋርያውን በቀድሞው በደሉ ይቅርታ ለምኖ ክርስቲያን ሆነ ይላል። ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ የኖረውና ያረፈውም በኢየሩሳሌም ከተማ ነው። ከእርሱ ሞት በኋላ የጌታ ወንድም (ስምዖን) በእግሩ ተተካ። በቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ሞት የተጀመረው ስደት ሄሮድስ አግሪጳ እንደሞተ ወዲያው አቆመ።

ሄሮድስ አግሪጳ የሞተው በመቅሰፍት ነው።የታሪክ ጸሐፊ ሉቃስና ዮሴፍ አግ ሪጳ ከቴአትር ቤት እራሱን እንደ አምላክ አድርጎ ስለ አስከበረ በዚሁ ምክንያት ተቀ ሰፈ። ሲሉ ጽፈዋል። እሱም የሞተው ይህ ጉዳይ በሆነ በ፫ ቀኑ ነበር።( የሐዋ. ፳: ፳፫)

### ቅዱስ ያዕቆብ ሁለቱን ጠንቋዮች እንዳሳመነ

ፊሊጦስ የተባለው ጠንቋይ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ማመኑን ለጓደኛው ለሄሮሞጌኒስ ነገረው ሄሮሞጌኒስም የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ሲል ፊሊጦስን እጅ እግሩን በአስማት አሰረው። ፊሊጦስም የደረሰበትን ሁሉ ዘርዝሮ ለያዕቆብ ላከበት። ይህን የሰማው ሄሮሞጌኒስ ቅዱስ ያዕቆብን አስረው እንዲያመጡለት በአስማት አጋንንትን ላካቸው። የተላኩት አጋንንት ግን በቅዱስ ያዕቆብ ላይ ኃይል ስላልነበራቸው የተላኩበትን መፈጸም አልቻሉም። (ማር. ፲፮:፲፯) እንዲያውም ቅዱስ ያዕቆብ መልሶ ሄሮሞጌኒስን እንዲያመጡት አዘዛቸው። እነርሱም እጅ እግሩን ጠፍረው ይዘውት መጡ። ፊሊጦስ ክርስቲያን ሆኖአልና ቅዱስ ያዕቆብ ከእስራቱ እንደፈታው። ለሄሮሞጌኒስ ምሕረት ለመነለት። ቅዱስ ያዕቆብም እኛ ክፉን በክፉ ስለማንቃወም በሰይጣናት እየተሰቃየህ እንዳትኖር ከክርስቶስ ምሕረትን እለምንልሃለሁ በማለት ሄሮሞጌስን ከታሰረበት እንዲፈታ አደረገ። አስማተኛው ሄሮሞጌኒስ የክርስቲያኖችን ኃይል፣ ርኅራኄና ቸርነት አይቶ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት አመነ። ወደ ቤቱም ተመልሶ የጥንቆላ መጻሕፍቱንና ዕቃዎቹን ሁሉ ሰብስቦ በማምጣት በቅዱስ ያዕቆብ እግር ሥር በእሳት አቃጠላቸው። እኛም ለዘመኑም ጠንቋዮች ልብ ይስጣቸው

www.ethiopianorthodox.org

እያልን ከመጸለይ ቸል አንበል። ብዙ በጎችን ከቀናው የነያዕቆብ ጎዳና ያደናቅፍብናልና። በአጠቃላይ ይህ ሐዋርያ ከዚህም በላይ ሰፋ ያለ ገድልና ተአምራት ያደረገ ነው። እንደ አበው አባባል ቅዱስ ያዕቆብ በዕድሜ ገፍቶ ስለነበር እንደሌሎች ሐዋርያት ብዙ አልተዘዋወረም። መቀመጫውም በኢየሩሳሌም ከተማ ነበረ።ቅዱስ ያዕቆብ ከሐዋርያት መካከል ሰማዕትነቱ በሐዲስ ኪዳን የተጻፈለት ብቸኛ ሐዋርያ ነው። ከሐዋርያት መካከል መጀመሪያ የሰማዕትነትን አክሊል የተቀዳጀ እርሱ ነው። (የሐዋ. ፲፪:፪) በአጠቃላይ ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተክርስቲያን ቀዳማውያን አበው ስለ ቅድስት ቤተክርስቲያን የተሰው፣ ሕይወታቸውን ለቤተክርስቲያን የሰጡ በመሆናቸው ቤተክርስቲያንም በልዩ ልዩ መንገድ ታከብራቸዋለች።

የሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስም ቃል ኪዳን በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም ለዘለዓለም የጸና በመሆኑ በአማላጅነቱ ይርዳን።


<u>ምንጭ</u>

ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፪፻፶ - ፪፻፶፯

ቤተክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ ገጽ ፶፯ - ፷

Dictronary of sains.P.8

የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት በስርግው ሐብለ ሥላሴ የተዘጋጀ።


## ንጽሕት ኪለላችን

እ ውነተኛ እናት ሰማያዊ መና
መ ለኮትን ያቀፍሽ ፍኅፍኒተ ህሊናፗ
ብ ጽዕናሽ ህያው ልብሰሽ ንጽሕና።
ር ግብዩ ማርያም አለሽ ቅድስና
ሐ መልማለ ቢና የድህነት ፋና።
ን ጹሕ መሰበ ወርቅ ድንግል አንቺ ነሽ
እ ግዚአብሔር ለቃሉ ማደሪያ ያረገሽ፤
መ ንገደ ሰማያት ለያዕቆብ ታየሽ።
ብ ርሃንን የወለድሽ ለአዳም ዘር መዳኛ
ሬ ህብን አስወጋጅ መና ሆነ ለኛ
ሒ ረገወይን ድንግል የሁሉ እመቤት
ት ጽሕተ ንጽሐን አዛኝ ለፍጥረት።

ታደሰ ጌታቸው
ቅ/ማ/ሰ/ት/ቤት
ሻኪሶ

# ቅዱስ ዮሐንስ

ቅዱስ ዮሐንስ ሀገሩ በገሊላ አውራጃ ሲሆን፤ከወንድሙ ከቅዱስ ያዕቆብና ከአባቱ ከዘብዴዎስ ጋር ዓሣ እያጠመደ ይኖር ነበር።የቤተክርስቲያን ትውፊት እናቱ ማርያም ባውፍልያ እንደምትባልና ከ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ እንደነበረች ይገልጣል።(ማቴ. ፳፯:፶፮)

የስሙ ትርጉም በአይሁድ ልማድና ህግ መሠረት ህፃን ልጅተወልዶ ስም ሲወጣለት ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከት መሆኑን የሚገልጽ ስም ይወጣለታል። ስለዚህ ዮሐንስ የሚለው ስም ዮሐናን ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ማለት ነው።

ይህ ሐዋርያ ጌታን በመከራው ሰዓት ሳይሸሸ እስከ እግረ መስቀሉ ተከሎታል።በዕለተ ዓርብም የጌታ መከራ ትዝ እያለው ተረፈ ዕድሜውን የፈጸመው በዕንባ ነው። የተጠራ ውም ገና በወጣትነት ዕድሜው ሲሆን በዚህ ምድር ላይ የኖረው ለ፺፱ ዓመታት ያህል ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስ ብዙ ስሞች አሉት። እነርሱም:-

፩. <u>ጌታ ይወደው የነበረ (ፍቁረ እግዚእ)፤</u> በሕይወቱና በኑሮው ጌታን ለመምሰል ይጥር ስለነበር ጌታ ይወደው ነበር። በቤተክርስቲያን ትውፊት እንደሚነገረውም አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መታጠቂያውን ፈትቶ ባስቀመጠበት ወቅት አንስቶ በመታጠቁ ፍትወት ሥጋዊ ወደማዊ ጠፍቶለት ኑሮው እንደ መላእክት ሆኖለታል።

፪. <u>ወልደ ዘብዴዎስ፤</u> የታላቁ ያዕቆብ ታናሽ ወንድም ስለሆነና አባቱም ዘብዴዎስ ስለሚባል ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ተብሎ ይጠራል።

፫. <u>ወልደ ነጎድጓድ፤</u> ለአምልኮተ እግዚአብሔር ባለው መንፈሳዊ ቅንዓትና ከወንድሙ ጋር ሆነው ባሳዩት የኃይል ሥራ ጌታችን ወልደ ነጎድጓድ ብሎታል። (ማር. ፫:፲፯፤ ሉቃ. ፱:፶፱-፶፭) በተጨማሪም የትምህርቱ ጥልቀት ኃይልና መስተጻርር፣ መስተቃርን የሌለው፤ መናፍቃን ሁሉ የሚረቱበት ነው። ከነዚህም መካከል ቀዳሚሁ ቃል የሚለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና ቅድመ ዓለም የነበረና ከባሕርይ አባቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ሁሉ በእርሱ የሆነ ሲሆን ራሱን አዋርዶ ቃል ሥጋ ሆነ የሚለውን ምሥጢር በመግለጡ ወልደ ነጎድጓድ ተብሎአል።

፬. <u>ነባቤ መለኮት (ታኦሎጎስ)፤</u> ነገረ መለኮትን ከሌሎች በበለጠ አስፍቶ በማስተማሩ ነባቤ መለኮት ተሰኝቷል።

፭. <u>አቡቀለምሲስ፤</u> የግሪክ ቃል ሲሆን (ባለ ራዕይ) ማለት ነው። ኃላፍያትንና መጻዕያትን በራዕዩ ስለገለጠ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ (Appocalypsus) ተብሎአል።

፮. <u>ቁጽረ ገጽ (ፊቱ በኀዘን የተቋጠረ)፤</u> በዕለተ ዓርብ በእግረ መስቀሉ ተገኝቶ የጌታችንን ጸዋትወ መከራ በማየቱ ከዚያች ዕለት ጀምሮ ፊቱ በኀዘን ተቋጥሮ ይኖር ስለነበር ይህ ስም ተሰጥቶታል።

## ሁለቱ ባለአደራዎች

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁሉ የተለየ ፍቅር ስለነበረው፤ ጌታችንን እስከ እግረ መስቀሉ በመከተሉ መላውን የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ወክሎ የእመቤታችንን እናትነት ከጌታ ተቀብሎአል። (ዮሐ. ፲፱:፳፭-፳፯) እርሱም በዚያች የመከራና የኑዛዜ ሰዓት የተገኘ የቁርጥ ቀን ወዳጅ በመሆኑ፤ በአደራ መልክ እነሆ እናትህ የተባለ ሐዋርያ ነው። በተጨማሪም ለእመቤታችንም ልዩ አክብሮትና ፍቅር ስለነበረው በእናትነት ተቀብሎ ወደቤቱ ከወሰዳት በኋላ፤ አደራውን አክብሮ በመጠበቅና በማጽናናት ፲፭ ዓመት ሙሉ ሲታዘዛት ኖሯል።

## ለጌታ ሥዕል ምንጭ ከሆኑት አንዱ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ዘመን የሮማ ንጉሥ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር ፲፬-፴፯ ዓ.ም ልጁ በሽተኛ ስለነበር፤የጌታን የማዳን ሥራ እየሰማ እንጲላጦስ የጻፉትንም ደብዳቤ እየተመለከተ ከዚያ ደግ ሰው መቃብር ልጁን ወስዶ ማን ባሳለመልኝ እያለ ይመኝ ነበር።በመጨረሻም ልጁን ወስደው በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ከሕመሙ ስለተፈወሰለት ለጌታ ያለውን ፍቅር ለመግለጥ የጌታን ሥዕል የሚሥልለት ሰው ሲያፈላ ልግ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ተገኘና ልክ በዕለተ ዓርብ እንዳየው አድርጎ ሥሎ ሰጥቶ ታል።

ዮሐንስ ወንጌላዊ እመቤታችን ካረፈች በኋላ ወደ ታናሿ እስያ ሄዶ አስተምሮአል። ዋና መንበሩን በኤፌሶን አድርጎ በተለይ በዚያ ዘመን ከአውሮፓ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚወስደው መንገድ ዳር በተቆረቆሩት ከተሞች አብያተ ክርስቲያናትን በማስ ተከል ጳጳሳትን በመሾም የወንጌልን ብርሃን አብርቶላቸዋል። ያስተማረበትም ቋንቋ በዮናኒ (በፅርዕ ቋንቋ) ነው።

"ወንጌል ብሂል በልሣነ ፅርዕ ወትርጓሜሁ ስብከት" እንዲል ዲያብሎስ እንደ ተሻረ ወልደ እግዚአብሔር እንደነገሠ፣ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ፣ የምትናገር



www.ethiopianorthodox.org

ሕገ ወንጌልን የምሥራችንነት ለሕዝብና ለአሕዛብ አብሥሮአቸዋል።ከክፉ መንገድ ርቀው ለፍቅር ሕግ ተገዢዎች እንዲሆኑም፤እርስበርሳችሁ ተዋደዱ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ናትና እያለ እስከ እርጅና ዘመኑ ድረስ ያስተምር እንደነበር ታሪኩ ይነግረናል። በመጨረሻም በጭካኔው በሚታወቀው ንጉሥ ድምጥያኖስ ዘመን ፹፩-፺፮ ዓ.ም ወንጌልን በማስተማሩ የተነሣ በጣዖት አምላኪዎች ተከሶ ለፍርድ ከቀረበ በኋላ በፍል ውኃ ተሰቃይቶ በፍጥሞ ደሴት ግዞት ተፈ ረደበት። ራዕዩን ያየውና የጻፈውም በዚያ ቦታ ነው። ድምጥያኖስ በ፺፮ ዓ.ም ሲገደል ቅዱስ ዮሐንስ ከግዞቱ ተመልሶ ሦስቱን መልዕክታቱንና ወንጌሉን እንደጻፈ ይነገራል።

አስቀድሞ ጌታ በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት(ዮሐ.፳፩:፳፪) ዮሐ ንስ ሞትን አልቀመሰም። ነገር ግን እንደነ ኤልያስና ሄኖክ ሞትን እንዳ ያይ እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያ ዋን ወስዶታል። ከሐዋርያት ሁሉ ይልቅ ረዥም ዕድሜ ወደ ፻፱ ዓመ ታት በምድር ላይ የቆየ ሐዋርያ ነው ከሐዋርያት ቀድሞ ያረፈው ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ታላቅ ወንድሙ ቅዱስ ያዕቆብ ሲሆን ከሐዋርያት መጨረሻ ከዚህ ምድር የተለየው የቅዱስ ያዕቆብ ወንድም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

## ወንጌላዊውና ቀማኛው የሽፍቶች አለቃ

አንድ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ከኤፌሶን ከተማ ተነስቶ ክርስቲያኖችን ለማስተማር ሲዘዋወር ወደ አንድ ትልቅ ከተማ ገባ። በዚያች ከተማ የሚገኙት ምዕመናን ጊልስ የተባለውን ወጣት ይወዱት ነበርና እናትና አባቱ በመሞታቸው፤ የሚንከባከበው የሚያስተምረው ካጣ ሊበላሽ ይችላል ብለው ስለፈሩ፤ ለቅዱስ ዮሐንስ ታሪኩን አጫወቱት።

ቅዱስ ዮሐንስ ይህንን ሲሰማ ወጣቱ ጊልስን ወደ ከተማዋ ጳጳስ ወሰደውና"እንደ ልጅህ ተንከባከበው እውነተኛ ክርስቲያን አድርገው ብሎ ሰጠው። የከተማዋ ጳጳስም ደግ ስለነበረ ጊልስን በደስታ ተበለው።ዘወትርም ያስተምረው፤ይንከባከበው ነበር

በመጨረሻም ጊልስ የአካባቢው ምዕመናን የተሰበሰቡበት ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ ግን ነገሮች መቀየር ጀመሩ። ይህ አባት ሥራ በጣም ስለበዛበት ጊልስ መቼም ተጠምቋል ብሎ እንደ በፊቱ መቆጣጠሩንና ማስተማሩን ተወው ጊልስም የለመደውን የአባትነት ፍቅር ሲያጣ ወደ ከተማ ወጣ ብሎ ከእኩዮች ጋር መቀራረብ ጀመረ። ጓደኞቹም መልካም አልነበሩም ጠጪዎች፣ ቁማርተኞችና ተደባዳቢዎች ነበሩ።

አንድ ቀን ማታ በአንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ጊልስና ጓደኞቹ ሲጠጡ አመሹ። ሁሉም ሰክረው በያ ሉበት ሲወድቁ ጊልስ ብቻ ቀረ። በመጨረሻም የሁሉንም የመጠጥ ሂሳብ ከፍሎ ያለውን ገንዘብ ጨረሰ። በነጋ ታው ጊልስ ጓደኞቹን ስለእናንተ ስል ገንዘቤን ሁሉ አባከንኩ አሁን ባዶ ኪስ ሆኛለሁ ብሎ ነገራቸው። ሁሉም ሳቁ በትና ጅሉ ጊልስ እኛ ገንዘብ ከየት የምናገኝ ይመስልሃል የምታገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅመህ ስረቅ አሉት።

በዚህ መሠረት ጊልስና ሁለቱ ጓደኞቹ የአንድ ሰው ቤት ሰብረው ገብተው ገንዘቡንና ጌጣጌጡን ዘረፉ። በዚህም የተነሳ ጊልስ መስረቅ ማለት ቀላል ሥራ ነው ብሎ አመነ። ከዚያ በኋላ ጊልስና ጓደኞቹ የታወቁ ዘራፊዎች ሆኑ። እነርሱ ባሉበት መንገድ ማንም በጤናው ማለፍ አይችልም ነበር። አንድ ቀን ሰው ሲደበድቡ ነፍሱ በእጃቸው ስለጠፋች ጊልስና ጓደኞቹ ከተማዋን ጥለው ጠፉ።ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጊልስ ስም በአካባቢው ገነነ።ሰው ሁሉ ይፈራው ጀመር።እርሱና ግብረ አበሮቹ አላፊ አግዳ ሚውን አላስቀምጥ አሉ። መንገደኞች ሁሉ በሰላም መጓዝ ነጋድያንም በጤና መነገድ አልቻሉም ጊልስ አለቃቸው ነበር መግደልና መዝረፍ የዘወትር ኑሮአቸው ሆነ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ዮሐንስ ወንጌላዊው ዳግም ወደዚህች ከተማ መጣ። ጳጳሱን ስለወጣቱ ጊልስ ጠየቀው እርሱም ያዘዘኸኝን አልፈጸምሁም ጊልስ ዛሬ ሰው ሁሉ የሚፈራው ወንበዴ ሆኗል። ዛሬ አላፊ አግዳሚውን አያስቀምጥም ይህ ሁሉ የእኔ ስህተት ነው። በማለት በፊቱ አለቀሱ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ይህን ሲሰማ በእጅጉ አዘነ። ወዲያው ጊልስ ያለበትን ጠየቀና በፈረስ እየጋለበ ተጓዘ። የአካባቢው ምዕመናንም "ጨካኞች ናቸው ይገድሉሃል " ቢሉትም አልተመለሰም። በተባለው ቦታ ሊደርስ ሲል ሁለት ሽፍቶች አገኙት ወዲያው ጩቤ አቸውን መዝዘው ከፊቱ ቆሙ። ቅዱስ ዮሐንስም የፍቅር መምህር ነውና ፍቅር በተሞ ላው አንደበቱ "ከመግደላችሁ በፊት እባካችሁ ወደ አለቃችሁ ውሰዱኝ ለእኔ እርሱ የዱሮ ጓደኛዬ ነው" አላቸው።

ሽፍቶቹም እየሳቁ ወደአለቃቸው ዘንድ ወሰዱት፣ ጊልስ ሲመጣ ዮሐንስ በፈ ገገታና በፍቅር ተመለከተው። ጊልስም አወቀውና ደነገጠ። ዘወር ብሎም መሮጥ ጀመረ ያን ታላቁን ሰው ዮሐንስን ፈራ። "ልጄ ለምን ትሸሻለህ እኔ አባትህ ምንም የሚ ጎዳ መሣ ሪያ አልያዝኩም" አለው።ያ ጨካኝ የሽፍቶች አለቃም ምርር ብሎ አለቀሰ፣ መሣሪያውን ሁሉ አምዘግዝጎ ጣለና ጓደኞቹን"ደህና ሁኑ እኔ ወደ ጌታዬ መመለሴ ነውና" አለና ከቅዱስ ዮሐንስ ኋላ ተፈናጥጦ ወደ ጥንቱ ቦታው ተመለሰ።ትቷት ሄዶ በነበረችይቱ እናት ቤተክርስቲያንም ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን እያገለገለ ኖረ። የዘመኑ ማጅራት መችዎችም ከዚህ የተቀደሰ ትምህርት ሊማሩና ሊመለሱ ይገባል።

## የቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍት

ቅዱስ ዮሐንስ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አምስት ወጻሕፍት አሉት እነዚህም አንድ ወንጌል ሦስት መልእክታትና አንድ ራዕየ ዮሐንስ ናቸው። ከቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎ ለሐዲስ ኪዳን ብዙ መጻሕፍት በማበርከት ሁለተኛ ነው። ወንጌሉን የጻፈው ከፍጥሞ ደሴት ግዞት ሲመለስ በ፺፮ ዓ.ም አካባቢ ነው። ከሌሎች ወንጌሎች የተለየ ነገረ መለኮታዊ ሲሆን የተጻፈውም ከሦስቱ በመጨረሻ ነው። በቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው በኤጅያን ባሕር ሆኖ ነበር። በዚያን ዘመን የእነ ሄራቅሊጠስ (፭፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት) የሎጎስ አመለካከት ጋር ቀላቅለው የሚያስተምሩ ኢስጦኢኮች በታናሿ እስያ ነበሩ። ቅዱስ ዮሐንስ የሎጎስ "ቃል እውነተኛ ትርጓሜ ቃለ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር ነው" እያለ ምሥጢረ መለኮትን አልቆ አምጥቆ ሊያስረዳ ፈልጎ በተመሰጦ እያለ መልአክ እግዚአብሔር የኤጅታንን ባሕር በእንቁላል ቅርፊት ውኃውን እየቀዳ ወደ ደረቁ ምድር ሲገለብጥ ቅዱስ ዮሐንስ ተመለከተ "እንዴት ይህን ባሕር በእንቁላል ቅርፊት ቀድተህ ለመጨረስ ትችላለህ" ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ ቢጠይቀው "እኔስ ፍጡርን ነው። አንተ ተመራምሮ የማይደረስበትን ባሕርየ መለኮት እመረምራለሁ ብለህ ትለፋ የለምን?" ብሎ መለሰለት። ያን ጊዜም ቅዱስ ዮሐንስ የሥላሴን ምሥጢርን ጠልቆ መተንተኑን አቁሞ "ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ" ብሎ ወደ ተከታዩ ጽሑፍ አመራ። ሎጎስ ማለትም በግሪክ ቋንቋ ቃል ማለት ሲሆን ይህንን ቃል ለአካላዊ ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ መጠቀም የጀመረው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ፪:፱ ከሐዋርያት ውስጥ ከምሰሶዎቹ አንዱ ይለዋል። የላቲን የቤክርስቲተያን አባት ናሄሬምናስ ዮሐንስ ለረጅም ጊዜ በሕይወት እንደኖረና በስተመጨረሻ "ልጆች ሆይ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ" በሚል ምክር ምእምናንን ያጽናና እንደነበር ጽፏል። ቅዱስ ዮሐንስ በድምጥያኖስ ትዕዛዝ መታሰሩን ያዩት መናፍቃን ትንሣኤ ሙታን የለም፤በነቢብ (በመናገር) በገቢር (በሥራ የሚሠራውን እንጂ በኃልዮ (በሀሳብ) የሚሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር አያውቀውም፤ ከጥምቀት በኋላ ምግባር መሥራት ጥቅም የለውም እያሉ የክህደት

ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ሁለቱ ቅዱሳን . . .

ከገጽ ፲፭ የዞረ ትምህርታቸውን በታናሿ እስያ ስለነዙት ቅዱስ ዮሐንስ ከፍጥሞ ደሴት ግዞቱ ሲወጣ ለመናፍቃኑ የክህደት ትምህርት መልስ ይሆን ዘንድ የመጀመሪያዋ መል እክቱን በ፺፮ ዓ.ም አካባቢ ጻፈላቸው።

ሁለተኛዋ መልእክቱን በመና ፍቃን የክህደት ትምህርት የተነሳ በሮ ምና ቤት ያለው የክርስቲያኖች ጉባኤ መከፋፈል ስለደረሰበት ጠብ ክርክር ተነስቶ ስለነበር ሮምና ለተባለች በፊት ጣዖት አምላኪ የነበረችና በኋላም በዮሐ ንስና በደቀመዛሙሩ አብሮኮሮስ ትምህርትና ተአምራት ለተመለሰች ሴት የማጽናኛ መልዕክት ጻፈላት። ሦስተኛ ውን መልእክቱን ጋዩስ የተባለ ሰው በስደት ምክንያት የሚንከራተቱትን ክር ስቲያኖች እየተቀበለ የሚያስተናግድ ደግ ሰው ስለነበር ይህን ደግነቱን በመስ ማቱ በዚያ የመከራ ዘመን እንዲህ ያለ ሰው በመገኘቱ እያመሰገነ እያበረታታ ጽፎለታል።

ሦስቱ የዮሐንስ መልዕክታት በአጻጻፋቸውም ሆነ በመሰረተ ሃሳባ ቸው ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ጥብቅ ዝምድና አላቸው። እራእዩ ሰባት እራእዮችን በማከታተል በምእድረ እስራኤል ለሚ ገኙ ሰባት አብያተክርስቲያናት ነው የጻፈው። ኤሬኒዩስ የተባለው የቤተክርስ ቲያን አባት መጽሐፉን የጻፈው ዮሐንስ እራሱ መሆኑን ጠቅሷል።

ራዕዩንም ሲጽፍ"በጌ ታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ"በማለት ክርስቲያኖች የሚኖሩ ትን ከዓለም የተለየ ነገር ግን በዓለም ውስጥ የሆነ ኑሮ አሳይቷል በፍጥሞ ደሴት ታስሮ ሲሰቃዩ ደግሞም መንፈሳዊ ነውና በመንፈሳዊው ዓለም ከቅዱሳን ጋር ነበር።

ለዚህ ነው ዛሬም ቦታ ድንበር ባላት አጥቢያ ቤተክርስቲያን እያለን በሰ ማያዊ ዜማ፣ ሥርዓት፣ እምነትና አም ልኮ ከጻድቃን፣ ከሰማዕታትና ከቅዱሳን መላእክት ጋር አንድ የምንሆነው። በአ ጠቃላይ ዮሐንስ ወንጌላዊ የሰማያት ምሥጢራት ሰማይ ተከፈቶለት ያየ ከመ ሆኑም በላይ ለእመቤታችንም ልዩ ፍቅር ስለነበረው የጌታችንን እናት እስከሬን በዕፀ ሕይወት ሥር መቀመጡን ለሐዋ ርያት ያበሰረ ታላቅ ሐዋርያ ነው።

<u>ምንጭ</u>

የቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮ ጵያ ገጽ ፩፻፲፭-፩፻፲፯

ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፩፻፹፱-፪፻፲፬

ትንሣኤ ጥቅምት ፱፻፸፩/፸፫ ገጽ ፱

ቤተክርስቲያንህን እወቅ በማኅ በረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም

የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት በሥ/ሐ/ሥ

Dictionary of Saints P ፩፻፹፱



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



## ሐዋርያው ቅ/በርተሎሜዎስ

በዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

ዕድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍስሐ ለሰጠን ለፈጣሪያችን ክብር ምስጋና ይግባውና በዚህ እትም የቅዱስ በርተሎሚዎስን ታሪክ ይዘን ቀርበናል።

ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሚዎስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን (ማቴ.፲፥፫) በርተሎሚዎስ ማለት የተሉ ሚዎስ ልጅ ማለት ነው ። የትውልድ ሐረጉም ከነገደ ንፍታሌም ነው ።

ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ያስተምሩ ዘንድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጣቸው መመሪያ መሰረት አህጉራትን ዕጣ ሲጣጣሉ፤ ለቅዱስ በርተሎሚዎስ የደረሰው አልዋሕ በምትባል ሀገር ነበር። ይህቺም ሀገር በአርመንያ አካባቢ የምትገኝ ናት። ይህ ቅዱስ ሐዋርያ ዕጣው ከደረሰው በኋላ አገሩን ባለማወቁ፤ አንተ ውሰደኝና ተመለስ በማለት ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን ጠየቀው። እርሱም ከፈጣሪው በተሰጠው አደራ ይህን ክቡር የሚሆን ሐዋርያ ወደተመደበበት ቦታ ሀገረ አልዋሕ ለማድረስ ተዘጋጀ ።

ከዚህ በኋላ ተነስተው ወደዚያች ሀገር ለመድረስ ሰዎችን በመጠየቅ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። በጉዞ ላይ እያሉም ፤ ግመሎችን ጭና ከአንድ አገር ወደሌላ ሀገር እየተዘዋወረ የሚነግድ አንድ ሢራራ ነጋዴ አገኙ። ወደ ነጋዴውም ከቀረቡና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ የት ድረስ እንደሚሄድ ነጋዴውን ሲጠይቀው አልዋሕ ወደምትባል ሀገር እንደሚሄድ ነገረው። በዚህ ጊዜ "እኛም ወደዚህች ሀገር ነው የምንሄደውና እባክህ አድርሰን" በማለት ጠየቁው። ነጋዴውም " የምትሸጡትና የምትለውጡት ነገር ሣትይዙና ምንም ገንዘብ ሣይኖራችሁ ወደ ዚያች ሃገር ለመሄድ ለምን አሰባችሁ? ከየትስ መጣሁ ቸ?" ብሎ ሲጠይቃቸው፤ ቅዱስ ጴጥሮስ መልሶ "እኛ የምንሸጠው፣ የምንለውጠው ገንዘብ የለንም። ነገር ግን የዓለሙ ሁሉ ቤዛ ከሆነው ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ከሐዋርያት ውስጥ የምንቀጠር ነን። የተጣለብንም አደራ በዓለም ዙሪያ ዞረን፣ ሕገ ወንጌል ሰብከን፣ አህዛብን ከኃጢአት ወለማ በማውጣት ከፍጹም ክህደት ወደ ፍጹም እምነት፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከማይጠቅም ትዕቢት ወደትህትና በመመለስ፤ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትና የአማናዊት ህገ ወንጌል ታዛዦች በማድረግ በደዌ ሥጋ የተያዙትን በተዓምራት በደዌ ነፍስ የተሰቃዩትን በትምህርት እንድንፈውስ ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶናል። ከእርሱ ለራቁትና ለተበተኑት ተስፋም ለቀረቡት ተስፋ መስቀልን፣ ለነፍስም ለሥጋም ሕይወትን የሚሰጥ ህገ.ወንጌልን አስተምረን፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀን፣ የሥላሴን የፀጋ ልጅነት ካሰጠን በኋላ የመንግሥቱ ወራሾች ይሆኑ ዘንድ ማዘጋጀት ነው ሥራችን አለው ።" ነጋዴውም "እናንተ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ከሆናችሁ ማ፤ ሰው ብቻውን ካልኖረ አይፀድቅም እያላችሁ ሚስትን ከባሏ የምትለያዩ ናችሁ ይባላል፤ ይህንን ትምህርት በዚያች ሃገር ገብታችሁ ካስተማራችሁ ደግሞ፤ ሚስቴ በእናንተ ስብከት ተመርታ ጥላኝ እንድትሄድ ነው የምወስዳችሁ? ምኔ ሞኝ ነው "በማለት እምቢታውን ገለጸላቸውና ትቷቸው ሄደ ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስና ሐዋርያው በርተሎሚዎስ፤ ሌላ ነጋዴ ሲመጣ ጠብቀው በተለየ ዘዴ ወደዚያች ሀገር መግባት የሚችሉበትን ሁኔታ ተመካከሩ። አንድ ነጋዴ ሲመጣም ቅዱስ ጴጥሮስ "ይህንን ባሪያዬን አልዋሕ በምትባል አገር ሸጨው ልመለስ ፈልጌአለሁና እባክህ ወደ ሀገርህ ውሰደኝ" ሲል ጠየቀው። ያም ነጋዴ "ለብዙ ጊዜ ከአገሬ ወጥቼ የምኖር በመሆኔ ለቤቴ አገልጋይ የሚሆን ሰው አጥቼ እኖር ነበር። ዛሬ አገኘሁ። ለመሆኑ ሙያው ምንድነው?" ብሎ ጠየቃቸው ቅዱስ ጴጥሮስም ቀለል አድርጎ "ወይን ጠባቂ ነው" አለው። ያ ነጋዴም እጅግ በጣም ብዙት ያለው ወይን ስለነበረው በ፴ እስታቴር በርተሎሚዎስን ገዛው (እስታቴር የሮሚ መንግስት ብር ምንዛሪ ሲሆን አንድ እስታቴር አራት ዲናሮች ያህል ነው። አንድ ዲናር ሃምሣ የኢትዮጵያ ብር ሣንቲም ያህል ሲሆን እስታቴር ግን ሁለት የኢትዮጵያ ብር ያህል ነው።) (ማቴ ፲፯÷፳፬፤፳፯) ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ከነጋዴው ከተቀበለ በኋላ "አደራ ለሌላ ጌታ እንዳትሸጠው፣ ከባድ ሸክም እንዳታሸክመው ስቃይና መከራ እንዳታዛብት፣ ሲል ነጋዴውን ተናገረው።" ባለፀጋውም የግመሎቹን ሸክም ሲያስተካክል ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ደብቆ ለበርተሎሚዎስ በመስጠት "ለድሆች መድ ውተው " አለውና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

### ያደረጋቸው ተዓምራት

ሀ. ነጋዴውና ሐዋርያው በርተሎሚዎስ በበረሃው ውስጥ ረዥሙን ርቀት መንገድ እንደ ተያያዙት፤ መንገድ ስተው ምንም ዓይነት ውሃና እንዳችም የሚቀመስ ምግብ ከሌለበት ፍጹም በረሃ ላይ ደረሱ። እነርሱም ውሃ ጥሙና ችግሩ ጠናባቸው፣ ግመሉቹም በረሀብ አለቁ። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ወደ ፈጣሪው እንዲህ ሲል ጸለየ ።

" አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ሰማይና ምድርን በውስጥዋም ያሉትን ፈጥረህ የምትገዛ፣ አባቶቻችን በበረሃ ሲሰደዱ አብረህ የምትሰደድ፣ ለቅዱሣንህ ኃይልንና በረ ከትን የምትሰጥ፣ ከዓለት ላይ ውሃን አፍልቀህ ለወዳጆችህ ሕዝበ እስራኤልን እንዳሰጣሀቸው፤ እኛም በዚህ ቦታ ረግፈን እንቅር፣ እነዚህ የሞቱ ግመሎችም ይነሱ፣ ተአምራትህን በበረታች ክንድህ አሣይና ይመኑብህ ብሉ ግመሉቹ ላይ ሲጸልይ በምድር ላይ የረገፋት ግመሉች ተነሱ። ብርታቱን ሰጥቶአቸው እንደተጫኑ ወደ አልዋሕ የሚወስደውን መንገድ አግኝተውም በሰላም ደረሱ።

ለ. ነጋዴውም በርተሎሚዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ ሾመው። ወይኑንም እያስጠበቀ እየኮተኮተ እና እየተከለ ለ፵ ቀናት ያህል በሥራ ተጠምዶ ተቀመጠ። በዚህ የአርባ ቀን ቆይታውም ብዙ ተአምራትን በሚያስደንቅ ሁኔታ ያሣይ ነበር። ለምሣሌ ያህል ሶስት የወይን ግንዶችን (አጽቆችን) ቆርጦ በሌላ ዛፍ ላይ ቢሰቅለው ወዲያውኑ ለምልሞ፣ አብቦ ፍሬ አፈራ። እያችሁ እንባብያን የቅዱሣንን የበረከት ፍሬ!

ሐ. ሐዋርያው በዚህ ብቻ አልተወሰነም ሌላም ቀን የወይኑ ባለ ቤት ሊጎበኝ ሲመጣ፤ እባብ ከጉድጓድ ወጥቶ ነደፈው። መርዙም ኃይለኛ ስለነበር በመላው አካላቱ ተሰራጭቶ ለሞት አበቃው። ወዳጅ ዘመዶቹም ለለቅሶና ለቀብር ተሰበሰቡ። በርተሎሚዎስ ግን ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። ሰዎቹም "አንተ ዉካኝ አሽከር ጌታህ ሲሞት እንደማልቀስ አፍጥጠህ ታየናለህ?" እያሉ ጮኹበት።

በርተሎሚዎስ ግን ጸሎቱን እስከሚፈጽም ድረስ ታገሣቸውና ያን ባለፀጋ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አፈፍ ብሉ እንዲነሣ አደረገው። የተነሣውም ባለፀጋ ለዚህ ያበቃው ቅዱስ በርተሎሚዎስ መሆኑን መሰከረ። በዚህም የተነሣ በጉዞ ላይ እያሉ ጀምሮ ብዙ ተዓምራትን ያየው ባለፀጋና የሰበሰበው ሕዝብ ባደረገው ተዓምራት ተደነቁ እምነታቸውም ጸና። በእግሩ ሥር ወድቀውም በአክብሮት ሰገዱለት። "በምድር ላይ ይህን ታላላቅ ድንቅ ሥራ የምትሰራ ከአማልክት ውስጥ አንተ ማን ህ? ምን እንድናደርግልህስ ትወዳለህ?" በማለት ጠየቁት። ሐዋርያውም እናንተ እንደምታስቡት በስህተት እንደምታመልኳቸው ጣዖታት ሣልሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ። እርሱም የሰማይና የምድሩ፣ የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ፤ ሰው ሆኖም በከበረ ደሙ ፈሳሽነት የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ፤ የሰይጣንን ተንኮል በረቀቀ ጥበቡ ድል ያደረገና የዓለሙ ሁሉ ቤዛ የሚሆን ፈጣሪን እምናለሁ። በስሙም ሙታንን እናነሣለን፣ ጠላቶቻችንን እናሣፍራቸዋለን። በማለት የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አምልቶና አስፍቶ አስተማራቸው። ሕዝቡም ከአምላክ በርተሎሚዎስ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም አሉ። ከአምልኮተ ጣዖት ተላቀው የሥላሴን የፀጋ ልጅነት በጥምቀት አገኙ። ከሞት የተነሣውም ባለፀጋ "ምንተ እግበር " ምን ላድርግ ብሉ ሲጠይቀው ቤተ ክርስቲያን እንዲያንጽ አዘዘው። ቤተ ክርስቲያኑንም አሰርቶ ሲጨርስ በቅስና ማዕረግ ሾመው፣ ሌሎችንም ዲያቆናት አገልጋዮችን ሾመላቸው። ከዚህ በኋላ ትምህርቱ በሁሉ ዘንድ እንደተዳረሰ ከተረዳና የወንጌልን



www.ethiopianorthodox.org

ፍሬ ከአፈራ፤ ብዙዎችንም ከጾዊአቸው ከፈወሰና በልዩ ልዩ እኩያን አጋንንት የተያዙትን ካዳነ በኋላ ንኢንዶስ ወደተባለች ሀገር እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ አዘዘው። በዚያች ሀገር እንደደረሱም አን ቀጾ ብፁዓን የተባለውንና ጌታችን በተራራው ስብ ከቱ ያስተማረውን(ማቴ.፭÷፩-፲፪) አብራርቶ አስተ ማራቸው እንዲህ እያለ "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና፤ ስለ ጽድቅ የሚራ ቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና። የሚ ምሩ ብፁዓን ናቸው ይማራሉና፤ የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፉአችሁና ሲያሣድ ዱአችሁ፤ በክርስቶስም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና።" እያለ ሲያስተምር እግዚ አብሔር የሰዎቹን ልቦና እንዲያስተውል ከፈተላ ቸው። በመንፈሣዊ ጥበብም በለፀጉ፤ በንስሐ ወደ ፈጣሪአቸው ተመለሱ። በህገ ወንጌልም ፍጹም አመኑ ቅዱሱን ሐዋርያም አከበሩት ።

ከዚህ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ባርቢርያን ሀገር ባርበር ወደምትባል ከተማ እንዲሄድ አመለከተው። ቅዱስ እንድርያስንም እንዲረዳው ወደ እርሱ ላከለት። ሕዝቡም በባዕድ አምልኮ የተጠመዱ ስለነበር ባይቀ በሏቸውም፤ እግዚአብሔር ከመካከላቸው አንዱን ሰው የሐዋርያትን ትምህርትእንዲቀበልና ያዘዙትን ሁሉ እንዲያደርግ አዘዘው። ስሙም ካኒበልስ ይባል ነበር ።

ወደ ከተማው አብረው በሄዱ ጊዜ የከተ ማው ሕዝብ ሐዋርያትን እንዲበሉአቸው አውሬዎ ችን ላኩባቸው። ካኒባልስ ግን አውሬዎቹን ሁሉ ማጥፋቱንና መግደሉን በማየታቸው፤ በከተማው ካለው ሕዝብ መካከል ብዙውን ሰው ወዲያውኑ በሀሳባቸው ተስማምተው በኢየሱስ ክርስቶስ አምላ ክነት አመኑ። ከመካከላቸውም ካህናትን መርጠው ቤተክርስቲያን ሰርተዋል። ሐዋርያው በርተሎሚ ዎስ በባህር ዳርቻ ወዳለች ከተማ ሄዶ ወንጌልን ያስተማረ ከመሆኑም በላይ፤ በኢትዮጵያም ወንጌ ልን ተዘዋውሮ እንዳስተማረ ሩፊኖስና ሶቅራጥስ የተባሉ ታሪክ ፀሐፊዎች መስክረዋል። የሀገራችን ሊቃውንትም በኢትዮጵያ ወንጌልን ከሰበኩት ሐዋ ርያት ውስጥ አንዱ መሆኑንና ሕዝቡን ያጠመቀባ ቸው ወንዞች አስከዛሬ ጽረስ (ብረት) እና ሉሚ (ውሃ) እየተባሉ እንደሚጠሩ ታውቋል ።

## የ መጨረሻ እረፍት

ይህ ቅዱስ ሐዋርያ ከጌታው የተሳከበ ትን ዓላማ ከግቡ አድርሶአል። በተሰጠው ጸጋም ብዙ ህሙማንን ፈውሶአል፤ አይነ ስውራንን አብ ርቶአል፤ የሞተውን አስነስቶአል። እግዚአብሔርም በዚህ ቅዱስ አባት ላይ አድሮ ድንቅ ሥራውን ለሕ ዝቡ አሣይቶአል፤ ክብሩንም ገልጦአል፤ ብዙዎቹ አሕዛብም ተገስጸዋል(ደንግጠዋል) ። የናቁትና ያቃ ለሉትም ተዋርደዋል። በዘመናችንም ይህን ያህል ኃይልና ሥልጣን ባለቤቱ ያጎናጸፋቸውን ቅዱሣን ክብር የሚያንኳስሱና ለዘለዓለም በማይሻር ጸጋና በረከት ያደላቸውን፤ የክብር አክሊልን ያቀዳጃቸ ውን ቅዱሣን ሕዝቦቹን የሚያጥላሉ ደፋሮች እየ ተበራከቱ መጥተዋል። ሃይማኖትን ከፍልስፍና ጋር በማገናኘት ብዙዎች በነቢያትና ሐዋርያት መሰረት ላይ ከታነፀቸውና በክርስቶስ ደም ከተቀደሰቸው የተዋሕዶ ሃይማኖት በጊዜአዊ ጥቅም ማንነታቸ ውን ለውጠው፤ ታሪካቸውን አጥተው፤ የብዙኃን እናት፤ የታሪክ እመቤት፤ የኪነጥበባት አክሊል፤ የሆነቸና ታሪክን ከነቅርሱ፤ ሐይማኖትን ከምግባር አጣምራ የያዘቸውን ቤተ ክርስቲያን እንደ እንጀራ እናት የጎሪጥ የሚያይዋት ብዙዎች ናቸው።

ስለዚህ እኛ የተዋህዶ ልጆች ሣይታወቁ ገድላቸው ተቀብሮ ያለውን ቅዱሣን ከመጻሕፍት ፈልፍለን በማውጣት ማስተማር ተቀዳሚ አላማችን ነው። በዚህች ቅድስት ሀገረ እግዚአብሔርና በቅዱሣኖቿ ላይ የሚደረገውን ወረራ በእምነት ሰይፍ እየመከትን" በድፍረትና በትዕቢት በመና ቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።" መዝ ፴÷፲፰ እንዳለ ክቡር ዳዊት ቅዱሳንን የሚሣደብን እንደበት የዚህ ቅዱስ ሐዋ ርያ ጸሎትና አማላጅነት ይዝጋልን። እያልን የሐዋ ርያውን ዜና ዕረፍት እንናገራለን። ከላይ እንደገ ለጽነው በመጨረሻ ቅዱስ በርተሎሜዎስ ጊስሚ ፈንና ጊኢንዶስ ወደተባሉ ሀገሮች አመራ። እነዚ ህን ሀገሮች የሚገዛው የንጉሥ አክርጳ ሚስት እን ኳን እስክትለወጥ ድረስ ብዙ ክርስቲያኖችን አፍሮ ቶአል። መኳንንቱና መሣፍንቱ የሕዝቡን መለወ ጥ፤ የአምልኮ ጣዖታቸውን መቅረት፤ ሕዝቡም ከእነርሱ ይልቅ ለሐዋርያው በርተሎሜዎስ ቃል መታዘዙን ተመልክተው በቅንዓት ተነሱበት። ተከ ሶም ወደ ንጉሥ አክርጳ ፍርድ ቤት ቀረበ ። በዚ ያም የሞት ፍርድ ተፈርዶበት መስከረም ፩ ቀን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከትተው ከነሕይወቱ ባሕር ውስጥ ወረወሩትና ዐረፈ። በነጋታውም ምዕ መናን ከባሕር አውጥተው በክብር ቀበሩት።

አምላክ በርተሎሜዎስ ፀሎቱንና በረከ ቱን በእኛ በልጆቹ ፍቅሩንም በልባችን ያሳድርብን አሜን ።

<u>ምንጭ</u>

፩ኛ. ትንሣኤ ፳/፸፭ ገጽ ፮፫

፪ኛ. ስንክሣር መስከረም ፩ ቀን


፫ኛ. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት በሥር ግው ኃብለ ሥላሴ የተዘጋጀ (ሕይወት በቤተ ክርስቲያን) ገጽ ፩፻፴፱

፬ኛ. ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሣን የት/ክፍል የተዘጋጀ ገጽ ፹፯

፭ኛ. የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ገጽ ፩፻፳

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



# ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ

በዲ/ን ኃይለሚካኤል ጌታሁን

ቶማስ በአራማይክ ቋንቋ ዲዲሞስ ሲባል፤ በግሪክ ቋንቋ ግን ቶማስ ማለት መንታ ማለት ነው። በኢትዮጵያም የወንጌልን ብርሃን በትምህርቱ ስለአበራ"ብርሃና ሙ ለኢትዮጵያ" ይለዋል ወይም ብርሃን ተብሎ ይጠራል።ከቅዱሣን ሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ናትናኤል፣ ቅዱስ በርተሎ ሜዎስና ቅዱስ ቶማስ፤ በናብያና በኢትዮ ጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ቅዱስ ወንጌ ልን እንደሰበኩ የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ዎች አነ ሩፊኖ ስና አነስቅራጥስ መስክረዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የትውልድ ሐረጉ ከነገደ አሴር ሲሆን፤ትንሣኤ ሙታን የለም" ብለው ያምኑ ከነበሩ ሰዱቃውያን ወገን እንደነበረ ይነገራል። (ማቴ.፳፪÷፳፭) በዚህም ምክንያት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ተጠራጥሮ ነበር።ጌታችን ከሙታን ከተነሣ በኋላ፤ ለሐ ዋርያት በተገለጠበት ጊዜ ቶማስ አልነበረም። የጌታ መከራ መስቀልን ተቀብሎ ለሰው ልጆች ሲል መሞቱ እጅግ አሳዝኖት ለብቻው ከቆየበት ቦታ ሲመለስ፤ ጌታን አየነው ቢሉት ባላይ አላምንም አላቸው። ጌታችንም እንደገና ለሁሉም ተገለጠላቸው በዚያን ጊዜ ቶማስ በጣቱ የጌታን የተወጋ ጎኑን፣ የተቸነከሩትን ቅዱሳት እጆቹንና እግሮቹን ዳሰሰ አይቶም አመነ። (ዮሐ.፳÷፲፱ - ፳፰)

ይህም ታሪክ የተፈጸመው ጌታችን ሙስና መቃብርን በኃይሉ ድል አድርጎ በተነሣ በስምንተኛው ቀን በዳግማዊ ትንሣኤ ነው። በአውነት መነሳቱን ለሁለተኛ ጊዜ የተገለጠ በትና ዳግማዊ ትንሣኤ የተባለበት በዚህ ምክንያት ነው።

መድኃኒት ክርስቶስ ለእኛ የዘለዓለም ሕይወት መሠረትና ለምዕመናን ሁሉ ተስፋ የሆነውን የተቀደሰ ትንሣኤውን ያሣየው ደቀመዛሙርቱ በጸሎት እየተጉ የተስጣቸውን ተስፋ እየተጠባበቁና የትንሣኤውን ነገር እያ ደነቁ ባሉበት በዝግ ቤት ውስጥ እንደተሰ በሰቡ ነበር በመካከላቸው ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ያላቸው።

የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል በማ ለት ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረለት 'እውነተኛ የባሕርይ አምላክ፤ በጥርጣሬ ታውኮና ሰላም አጥቶ የነበረውን የቶማስን ልብ ከጥርጣሬ ማዕበል ከመታወክ ሊገላግለው ፈለገ።

"ዘክልኤ ልቡ ህውክ ውእቱ" እንዳለ መጽሐፍ ቶማስም ተነስቶ ይሆንን ወይስ አይሁድ እንደሚያወሩት አልተነሳም? በማለት ይጨነቅ ይታወክ ነበር። ጌታችንም ገና ከመሞቱም በፊት በመዋዕለ ስብከቱ ልባ ችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእ ኔም ደግሞ እመኑ በአባቴ ቤት ብዙ መና ሪያ አለ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም አወስዳችኋለሁ።ወደምሄድበትም ታው ቃላችሁ መንገዱንም ታውቃላችሁ ሲል ቶማ ስም"ጌታ ሆይ ወደምትሄድበት አናውቅም እንዴትስ ፤መንገዱን እናውቃለን?" በማለት ጠይቆት ነበር። (ዮሐ. ፲፬÷-፭)

ገና አስቀድሞ "ልባችሁ አይታወክ" በማለት ያስተማራቸው፤ የልብ መታወክ ጠቅላላ አካልንና መንፈስን የሚጎዳ ከመሆ ኑም በላይ፤ በተለይ የዓለሙ ሁሉ ቤዛ የሆ ነውን የመድኃኔዓለም ክርስቶስን የባህርይ አምላክነት ባለማመናቸው ነበር። ቶማስም ዓለም ሳይፈጠር የነበረና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ፤ በሕልውና፣ በአገዛዝ በመሣሰሉት የሚተካከል (አንድ የሚሆን)፤ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፤ በስጋ ተገልጦ፣ ስለ ሰው ልጆች ውርደትና መከራን ተቀብሎ፣ ዓለምን በክቡረ ደሙ ፈሣሽነት ቀድሶና አከ ብሮ ለቅዱሣን ሐዋርያት ክብርን እንደሚ ያቀዳጅ ባለማመኑ፤ አይቶና ዳስሶ እንዲያ ምን በማድረግ ከጥርጣሬ ገላግሎታል።

የቅዱስ ቶማስ ችግር ዛሬም የዓ ለሙ ችግር ነው። በውኑ እግዚአብሔር ከክፉ መከራ ከሰይጣን ሴራ ያድናልን? እያሉ የሚጠራጠሩ ብዙዎች ናቸው።ዳሩ ግን የሰይ ጣን ፍላፃ የሚሰበረውና በዓለም ላይ በልዩ ልዩ ቦታ የሚካሄደው ጦርነትና እልቂት፤ የሰ ላምም መታጣት ቀጥ ሊልና ሰላማችን ሊረጋ ገጥ የሚችለው፤ በእግዚአብሔር አምነን፣ ተጠምቀን፣ በንስሐ ወደ እርሱ ስንቀርብ ነው።

ቅዱስ ቶማስ የነበረበትን ያለማመን ችግር ለማስወገድ ሲል ወደ እርሱ ቀርቦና ዳስሶ እጁ እሳት ውስጥ እንደተጣለ ጅማት ኩምትር ብላለች። በዚህን ጊዜ መለኮታዊ ኃይሉ ተገልጾለት በፍጥነት "እግዚእየ ወአምላኪየ" "ጌታዬ አምላኬም" ብሎ መስክ ሯል። እኛም በዓለም ላይ ነፉ ያለ ው መለያየትና ጦርነት፣ የሰላም መደፍረስና የረሃብ፣ የእርዛት፤ የበ ሽታ እሳት፤ እያኮማተረ ሣይጨር ስንና ከንቱ ሣያስቀረን፤ እንደ ቅዱስ ቶማስ አምላክነቱን በማመን ፈጥነን ወደ እርሱ መመለስ ይገ ባናል። ሕይወታችን በመምህረ ንስሐ ተዳስሶ ከጎኑ የፈሰሰውን ደሙንና የተቆረሰውን ስጋውን በመ ብላት ከሞተ ኃጢአት እንነሣ።

## ቅዱስ ቶማስና የእመቤታችን ትንሣኤ

ይህ ቅዱስ ሐዋርያ ከሌሎች ሐዋርያት ለየት የሚያደርገው የአመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ትንሣኤና ዕርገት በመጀመሪያ በማየቱ ነው።

አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማር ያም ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲተላለፍ በመጣው ትውፊት በተገለጠው መሠረት፤በ፷፬ ዓመት ዕድሜዋ፤ በ፵፱ ዓ.ም አካባቢ፣ በጥር ፳፩ አርፋለች። መላእክትም ሥጋዋን አሣርገው በገ ነት በዕፀ ሕይወት ሥር አኖ ሩት። በዚያው ዓመት ሥጋዋ እስከ ነሐሴ ፲፬ ቀን በገነት ከቆየ በኋላ፤ ነሐሴ ፲፬ ቀን መላእክት አምጥተው ለሐዋርያት ሰጡአቸውና በጌቴ ሴማኒ ቀበሩ አት። በሦስተኛው ቀን ነሐሴ ፲፮ ተነሥታ በክብር ወደሰማያት ስታርግ፤ ቅዱስ ቶማስ ከነበረበት ሀ/ሥብከት በደመና ፈረስነት ሲጓዝ መንገድ ላይ አመቤታችንን አግኝቶአታል። ባገኛትም ጊዜ "ከዚህ በፊት ወንድሞቼ ሐዋርያት የልጅሽን ትንሣኤ አይተው ጌታ ተነሥቶአል ቢሉኝ፤ አላምን ብዬ በኋላ ዳስሼ አመንኩ። አሁን ደግሞ ያንቺን ትንሣኤ ሌሎቹ ደቀመዛሙርት በክብር አይተው እኔ ብቻ ተለይቼ ልቅር?" በማለት አዝኖ ከደመናው ላይ ለመውደቅ ቃጣው።

በዚህ ጊዜ ግን አመቤታችን አይዞህ ብላ በማረጋጋት፤ ለትንሣኤዋ እውነተኛ ምስክር ይሆን ዘንድ ሰበኗን (መግነዟን) ሰጥ ታው፤ በፍጹም መንፈሣዊ ደስታ ለሐዋርያት የመጀመሪያ አብሣሪ ሆኗል። እነሱም ቶማስ ትንሣኤዋን አይቶ እኛ እንዴት ይቅርብን በማለት ሱባዔ አድርገው አይተዋል።

## የቅዱስ ቶማስ ትምህርትና ያደረጋቸው ተአምራት በሕንድ ማላባር ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

ይህች ጥንታዊትና ሐዋርያዊት ቤተክ ርስቲያን የተቋቋመችው፤በ፶፪÷ዓ።ም አካባቢ በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ስብከት እንደሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታወቃል።

ሐዋርያው ቶማስ ይህችን ቤተክርስ ቲያን ለማቋቋም፤ ለ፳ ዓመታት ያህል በመ ኖር፤ የሕንዶችን ጥንታዊና ባህላዊ አምነታ ቸውን ወደ ክርስትና አምነት በመለወጥ ከፍተኛ ተጋድሎዎችን አከናውኖ አል።

በተለይም በታክሻሲላ ከተማ የነበ ረው ንጉሥ ጎንዶፓረስ በኢየሩሳሌም ስለ ነበረው የሰሎሞን ቤተ መንግሥት ዝና እየ ሰማ እርሱም በግዛቱ ለማሠራት ይፈልግ ነበር። በዚህም ምክንያት ነጋዴዎች በየሀገሩ ሲጓዙ የታወቀ ግንበኛ እንዲያመጡለት አዘዛቸ ው።

ይህን መልእክት ከሰሙት ነጋዴዎች መካከል አንዱ ወደ ፐርሺያ ወረደ። ቅዱስ ቶማስ ወደ ሕንድ ተጉዞ ወንጌልን ለመስበክ መንገድ ሲፈልግ ከዚያ ነጋዴ ጋር ተገናኘ። ነጋዴው የቶማስን ከኢየሩሳሌም መምጣት ሲሰማ የግንበኝነት ሙያ ይችል እንደሆነ ጠየቀው። ቶማስም በኢየሩሳሌም በነበረበት ጊዜ ሕንፃ በማነፅ ኑሮውን ይገፋ እንደነበር ለነጋዴው መለሰለት።



www.ethiopianorthodox.org

ነጋዴው በዚህ አጋጣሚ በጣም ተደስቶ ቶማስን ወደ ሕንድ ማላባር ወሰደው። ንጉሡም የቶማስን ሙያ ሲሰማ እጅግ ደስ አለው። ከታክሻሲላ ከተማ አጠገብ ወደሚገኘው ሜዳ ቶማስን ወሰደውና በጫካ የተሞላውን ሜዳ እያሳየ ቤተመንግሥቱ የሚተከልበትን ቦታ አመለከተው። ቅዱስ ቶማስ የቤተ መንግሥቱን አሠራር(ዕቅድ)ሲነግረው ንጉሥ ጎንዶፓረስ ተሠርቶ እስከሚያየው ቸኮለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንጉሡ (ለሠራተኛ መቅጠሪያ፤ ለድንጋይና ዕብነ በረድ፤ ለብርና ወርቅ፤ ለብረትና እንጨት መግዣ) እያለ ለቅዱስ ቶማስ ያለ የሌለውን ገንዘብ ይልክለት ጀመር።

ቅዱስ ቶማስ ግን ገንዘቡን ሲያገኝ የተጓዘው ወደ ገበያ ወይም ሠራተኛ ፍለጋ ሳይሆን ወደ ድሆች መንደር ነው። በዚያም ለተራቡት ምግብ፤ ለታረዙት ልብስ በየበረንዳው ለወደቁት መጠለያ እየገዛ ማደል ጀመረ። ድውያንን እየፈወሰና የተቸገሩትን እያፅናና ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን መስበክ ያዘ።

ንጉሥ ጎንደፓርስ ገንዘብ በላክ ቁጥር የሚገነባው ቤተመንግሥት ሳይሆን፤ የድሆችና የደካሞች ቤት ነበር። ለቤት መሥሪያ የመደበው ገንዘብና ጊዜ እንደተጠናቀቀ፤ ቤተመንግሥቱን ሊጎበኝ ወጣ። ጫካው አልተካም፣ ያሰበው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ቀርቶ፤ የወደቀ ድንጋይ፣ የተቆፈረ መሬት የለም። ንጉሡ በዚያ በኩል የሚያልፍ አንድን መንገደኛ ጠራና "ቶማስ የታለ?" ሲል አፈጠጠበት።

"ቅዱስ ቶማስ የተራቡትን እያበላ፣ የተጠሙትን እያጠጣ፣ የታረዙትን እያለበሰ፣ ሕሙማኑን እየፈወሰና እያፅናና በድሆች መንደር ይገኛል"ሲል መንገደኛው መለሰለት። እርሱ ባልከፋ ታዲያ የሠራልኝ ቤተመግሥት የታለ?" ንጉሡ መንገደኛው ላይ አንዳፈጠጠ ጠየቀው።

"በድንጋይ የተሠራ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ ጌታዬ፤ ነገር ግን በሕዝብዎ ገጽታ ላይ ደስታና ፈገግታ ማንበብ ይችላሉ። አለው" መንገደኛው።

በዚህ ጊዜ ንጉሡ ያ ሁሉ ገንዘቡ እንደባከነበት መጠርጠር ጀመረ። ወዲያው ወታደሮቹ ቶማስን ፍለጋ አካባቢውን አጥለቀለቁት። ቅዱስ ቶማስ ተይዞ እንደመጣ "ቤተ መንግሥቴን ለምን አልሠራህልኝም" "የታለ ጫካው እንኳን መቼ ተነሣ?" "እርግጥ በምድር ላይ የድንጋይ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ፤ እኔ ግን በሰማይ ላይ ቤተ መንግሥት ሠርቼልዎታለሁ።" አለው ቶማስ ለንጉሡ።

ያን ጊዜ ንጉሡ ተቆጣ ቶማስን እጅ እግሩን እየቆራረጡ እንዲያሰቃዩት አዘዘ ወህኒ አወረደው።

በዚያች ሌሊት የንጉሡ ወንድም የሆነው ልዑል ጋድ በድንገተኛ በሽታ መጣ ደፋ ጀመረ። ሊነጋጋ ሲልም ነፍሱ ከሥጋው ተለየች። የጋድ ነፍስ በመላእክት ታጅባ ወደ ሰማያት ወጣች ካጀቧት ቅዱሳን መላእክት አንዱ ብዙ አብያተ መንግሥታትን እያሳያት ትኖሪበት ዘንድ ደስ ያለሽን ምረጪ" አላት። የጋድ ነፍስም በአብያተ መንግሥቱ መካከል የሚታየውን የሚያምር ቤተ መንግሥት መረጠች። "ይህ ቤተመንግሥት ያንቺ አይደለም፤ ቶማስ ለንጉሥ ጉንዶፓርስ ቤት የሠራለት ሰማያዊ ቤተ መንግሥት ነው።" አላት በዚያች ሰዓት ነውና አምላከ ቅዱሳን የልዑል ጋድ ነፍስ ከሥጋው ጋር ተዋሐደች።

ጋድ ሊቀብሩት በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሰው ተንቀሳቀሰ። ከዚያም አፈፍ ብሎ ተነሣ። ልዑል ጋድ በዚያች ቅጽበት የተመለከተውን ሁሉ ለን ጉሥ ጎንዶፓረስና ለተሰበሰቡት ሁሉ ነገራ ቸው።

ንጉሡ ይህን ሲሰማ በቶማስ ላይ በሠራው ግፍ ሁሉ አዘነ፣ ተፀፀተም። ያሰበው ቤተ መንግሥት መሠራቱን ሲሰማ፤ ቶማስን ከወህኒ አወጣው። እርሱና ቤተሰቡም በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው ተጠመቁ። ጎንዶፓረስም ሌላም ቤተ መንግሥት ሥራልኝ" እያለ ያለውን ሁሉ ገንዘብ ለቅዱስ ቶማስ ይሰጠው ጀመር። የማላባር ባለፀጎችም አሠረፍኖ ቱን ተከተሉ።

ይህ ቅዱስ ሐዋርያ ከማላባር ጀምሮ እስከ ቻይና በመዝለቅ ወንጌልን አስተምሮአል፣ ድውያንን ፈውሶአል። አምስት ዓመት ሙሉ በእኩያን አጋንንት ተይዛ ትሰቃይ የነበረችን ሴት፤ ከአጋንንቱ ቁራኝነት በማላቃቅ አድኗታል። እናም በጸሎቱና በምልጃው በልዩ ልዩ ዓለማዊ ምኞት ጠላት ሰይጣን እርስ በእርሳችን ሊያለያየንና ሊያጠፋን ያገሣልና በአማላጅነቱ ይጠብቀን።

የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት ካለቻችሁ ተራራ ታፈርሳላችሁ፣ ዛፍ ትነቅላላችሁ፤ በስሜ ላመኑ ሰዎች ይህች ተአም ራት ቀጥላ፣ ቀጥላ ትደረግላቸዋለች። በእኔ ያመነ እኔ የማደርገውን ተአምራት ያደርጋል ከዚያም የበለጠ ያደርጋል (ሉቃ.፲፯÷፮፣ ዮሐ.፲፬÷፲፪) ባለው መሠረት፤ ይህን ለማድ ረግ የበቃው ቅዱስ ቶማስ ገድሉ እንደሚ ናገረው ምንም እንኳን ዓለም ቢቃወመው በክርስቶስ ስም ከተሳለ ስለት ከነደደ እሳት ገብ ተው የሞቱትን ቅዱሣን ክብር የሚያቀዳጃቸው ክብር ምስጋና ይድረስውና እውነተኛ ተጋድሎውን ፈጽሞ የክብር አክሊልን አቀዳጅቶታል።

## የመጨረሻ እረፍት

ቅዱስ ቶማስ (ዲዲሞስ) ያደረጋቸውን ተዓምራት ከላይ በገለጽነው ብቻ በአ ጭሩ ተዘርዝሮ አያልቅም ገድለ ሐዋርያትና ስንክሣሩ እንደሚናገረው ብዙ ሙታንን አስነስቶአል፣ ሕሙማንን ከደዌያቸው አላቆ አል ይልቁንም ለጎንዶፓረስ ሰማያዊ ቤታችን የሚገነባበትንና እግዚአብሔር ከሁሉ አብ ልጦ የሚደሰትበትን ነገር አፍቅሮ ምንዱባንን (ችግረኞችን መውደድና መርዳት) የመሳሰለውን የትሩፋት ሥራ በሚገባ አስተምሮታል። ከዚህ ታሪክ የምንማረው ብዙ ቁምነገር አለ ይኸውም በየጎዳናው እንደ ቅጠል እየረገፈ በረሃብ ሰቆቃ ፍዳውን እያየ ፊቱ በችግር ብዛት አመድ መስሎ፤ የወገን ያለህ፣ የት ልግባ እያለ እኛ ግን ከሱ የተሻለ ኑሮ እየኖ ርን አይናችን ታውሮ ዝም ብለን ልንመለከት አይገባም። ጌታ በመጨረሻዋ ቀን ለፍርድ ሲመጣ የሁሉም ሰው ሥራው በየግንባሩ ላይ ሲነበብ ብራብ አላበላችሁኝም፣ ብታረዝ አላለበሳችሁኝምና ከእኔ ወግዱ ከመባል የም ንድነው ሐዋርያው ከምንም በላይ አጉልቶ ያስተማረውንና በሥራም ጭምር ያሳየውን ትምህርት ስንፈጽም ነው።

ቅዱስ ቶማስ ይህን ሁሉ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት በመስጠቱና ብዙ ተዓምራትን ስለሠራ፤ ለአማንያን እድናቆትና በረከትን አጎናጽፏል፣ ለአሕዛብ መደናገጥን አስከትሏል። በመጨረሻም በ፸፪ ዓ.ም በሚላፖር ከተማ የሚጉኙ ጣዖት አምላኪዎች፤ ቆዳ ውን ገፈው ስልቻ በመሥራት፣ በሰውነቱ ጨው ነሥንሰው በማሰቃየት ግንቦት ፳፮ ቀን ለሞት አብቅተውታል።

እስካሁን ድረስ ቆዳው (አፅሙ) በሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተቀምጦ ይቀደስበታል። በስሙ በሚጠራው ተራራ ማድራስ ይባል በነበረው ቦታ ላይ፤ ከፍተኛ ሰማዕትነትን ተቀብሎአል። በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አፅሙ ወደ ኤዴሳ መጥቶ በክብር አርፎአል። ጸሎቱና በረከቱ በእኛ በልጆቹ አድሮ ይኑር።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ምንጭ -

የኢ፡ኦ፡ተ፡ቤ/ክ እምነት ሥርዓት አምልኮትና የውጭ ግንኙነት

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ታሪክ ኩለሌ መልአኩ አ.አ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ገጽ ፷፭- ፸፲፰

ገድለ ሐዋርያት ፪፻፷፩- ፪፻፹፯

ኮከበ ሃይማኖት

ስንክሣር

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ ገጽ ፹፱-፺፫ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

## እናት ዓለም
## ቤተክርስቲያን


ከሕይወት ቃልሽ መግበሽኝ
በቀጥተኛው መንገድ መርተሽኝ
በተዋሕዶ እምነት አጸናሽኝ
ወንጌልንም በውስጤ ዘራሽልኝ
ምሕረት እንዳይቀር በእኛ ኃጢአት ብዛት
ደካሞች በመሆናችን በምንሠራው ስህተት
ለነፍሳችን ትተን ለሥጋ ስሸንዋትት
አንቺ ጠብቂን ከሚመጣው መዓት
ጥሪሽን እሰሚ ላልሰማ
የሕይወት ቃል ወንጌልን ለተጠማ
ኑ ልጆቼ ብለሽ ጠርተሻቸው
የነፍስ ምግብ ሥጋወደሙን መግቢያቸው
እንመጣም ቢሉ ቃልሽን ሰምተው
ክብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደው
ከመዳን ይልቅ ሞትን መርጠው
እናት ዓለም አስተምሪያቸው
አሁንም ደግመሽ ጥሪያቸው
ጥሪሽን በእውነት እሰሚያቸው
እጆችሽን ዘርግተሽ ኑ ልጆቼ በያቸው
በጥቅማ ጥቅም ከተታለሉ ከተደለሉ
እንሰማም ብለው ቃልሽን ካቃለሉ
እነሱ ቢረሱሽ እኔ ላልረሳሽ
እነሱ ቢጠሉሽ እኔ ላልጠላሽ
እስከ መጨረሻው ላልከዳሽ
ቃል እገባለሁ ላልለይሽ

ከሥዩም ቱሉ
መ/ዓ/ሰ/ት/ቤት
ሞያሌ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



## ሐዋርያው (ወንጌላዊው) ቅዱስ ማቴዎስ

በዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

የዘመናት ጌታ እግዚአብሔር ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን መርር የነበረውን የሰው ልጅ ሕይወት በክቡር ደሙ ፈሳሽነት ቀደሰ፡ ከዲያብሎስ ባርነትና ከዘለዓለም ሞት እኛን ልጆቹን ለማዳን ሲል ስፍር ቁጥር የሌለው ጸዋትወ መከራን በመቀበል ዓለምን በማሸነፉ፤ ቅዱሳን ሐዋርያትንም በብዙ መከራ እየተፈተኑ እንዲያልፉና የክብር አክሊልን እንዲቀዳጁ የፈቀደ፡ ይህንን ያደረገ አምላካችን የተመሰገነ ይሁንና፤ የተመረጠና የከበረ፣ የድል አክሊልንም የተቀዳጀ የቅዱስ ማቴዎስን ታሪክና የሠራቸውን ትሩፋት እንደሚከተለው ስናቀርብ እናንተም በጥሞና እንድትከታተሉን መንፈስ እግዚአብሔር ይርዳችሁ፡፡

ሐዋርያና ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ከአራቱ ወንጌላውያንና ከ፲፪ቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን፤ "ማቴዎስ" ማለት በዕብራይስጥ "የእግዚአብሔር ስጦታ" ማለት ነው፡፡

ለሐዋርያነትና ለወንጌላዊነት ከመጠራቱ በፊት ሌዊ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ወንጌላዊው ማርቆስ ስለማቴዎስ የመጀመሪያ ስም፣ "በባሕር አጠገብ ሲያልፍ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን አየና ተከተለኝ አለው፡፡" በማለት ሌዊ በሚል ስም መጠራቱንና የአባቱም ስም እልፍዮስ መሆኑን ገልጾአል፡ (ማር. ፪÷፲፬)፡

ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት ግን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ ትውልዱ ከካህናት ወገን ሣይሆን እንዳልቀረ፤ ሌዊ የሚለው የስሙ አጠራር ያስረዳል፡ ይህ ቅዱስ አባት ትውልዱ ወይም ነገዱ ከነገደ ይሳኮር፣ ናዝሬት በሚባል አገር ሲሆን፤ የእናቱም ስም ካሩትያስ እንደምትባል ታሪክ ጸሐፍያን ይተባበራሉ፡፡ ቅዱስ ሉቃስም በበኩሉ ስለማቴዎስ ሲጽፍና ከ፲፪ቱም ሐዋርያት አንዱ መሆኑን ሲገልጽ፤ "ሌዊ የሚባል ቀራጭ በመቀመጫው ተቀምጦ ተመለከተና ተከተለኝ አለው፣ ተነስቶም ተከተለው፤ ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፡፡" ሲል ስሙንና ሥራውን ጨምሮ ይገልጻል፡ (ሉቃ. ፭÷፳፯) በራሱ ወንጌል ግን ስሙን ሁለት ጊዜ ሲጠራ ማቴዎስ በሚል ይጠራዋል እንጂ፤ ሌዊ የሚለውን አያወሳም፡፡(ማቴ.፱÷፱፣ ፲÷፫)

ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት የመንግሥት ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር፡ በተለይም በዚያን ዘመን ፍልስጥኤም የሮማውያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች፤ ከሮማውያን ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሁሉ እንደ ኃጢአተኛና እንደበደለኛ ይቆጠሩ ነበር፡ በእስራኤልና በይሁዳ ኅብረተሰብ ሁሉ የተጠሉና የተናቁ ነበሩ፡፡ ስለዚህም ነው ጌታ "ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ ይበላል አብሮ ይጠጣል፡፡" ተብሎ የተከሰሰው፡፡ (ማቴ. ፱÷፲፬)

ወንጌሉን የጻፈው የአይሁድን እምነት ሲከተሉ ለነበሩ ክርስቲያኖች ሲሆን ያስተማረበትም ቋንቋ ዕብራይስጥ ነው፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላውያን ሁሉ ለየት ብሎ በነቢያት የተጻፈውን አይሁድ የሚቀበሉትን ማስረጃ ሁሉ በሰፊው ይገልጻል፡ ስለዚህ በተለይም ከብሉይ ወደ ሐዲስ መሸጋገሪያም ይባላል፡ ስለምሥራቅ የጥበብ ሰዎች /ሰብአ ሰገል/ የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው፡፡ (ማቴ. ፪÷፩ ፲፩) ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈውም የማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ዘመን በኋላ ወደ አራማይክና ወደ ግሪክኛ ቀጥሎም ወደ ግዕዝና ላቲን ተተርጉሟል፡፡

### ወንጌሉን የጻፈበት ዘመንና የጻፈበት ቋንቋ

ይህ ወንጌል በሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የተጻፈውም ጌታ ባረገ በስምንት ተፈጸሞ ዘጠነኛው ሲጀመር፤ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ነው ይላል መቅድመ ወንጌል፡

ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት፤ እግዚአብሔር ወንጌሉን እንዲጽፉ ሁለቱን ከአርድዕት፣ (ለክብረ አርድዕት) ሁለቱን ከሐዋርያት ሲመርጥ፤ ከሐዋርያት ከተመረጡት አንዱ ማቴዎስ ነው፡፡ ያስተማራቸው፣ ያሳመናቸውና ያጠመቃቸው ከአይሁድ ወገን የሚሆኑ ብዙ ምዕመናን ተሰብስበው፤ በቃል ያለ ይረሣል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳልና ብለው፤ ያስተማራቸውን በዕብራይስጥ ቋንቋ በመጽሐፍ ጽፎ ይሰጣቸው ዘንድ ጸፍልን ባሉት ጊዜ ጻፈላቸው፡፡

በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ እስጢፋኖስን በደንጊያ ወግረው ከገደሉ በኋላ፤ እስጢፋኖስ ነበር እንጂ ባፍና በመጣፍ የማይቻል የቀሩትንስ ሐዋርያት መበተን አይሳነንም እያሉ፤ በክርስቲያኖች ላይ በምቀኝነት ተነሱባቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከአይሁድ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ካልጻፉችሁልን እንደምን ይሆናል ብለዋቸው ነበርና ወንጌሉን ጽፏል፡፡

በተጨማሪም ያላመኑት አይሁድ ያመኑትን "ክርስቶስን የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ነው ትሉታላችሁ እንጂ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ መሆኑን እስኪ ሰፍራችሁ ቆጥራችሁ አስረዱን" ብለዋቸዋል፡ እነርሱም በእውቀት ፍጹማን አይደሉምና ዝርዝር የዘር ሐረጉን ማስረዳት ቢሳናቸው ለቅዱስ ማቴዎስ ላኩበትና ካለበት ቦታ መጥቶ ጻፈላቸው፡፡ ወንጌሉን የጻፈውም ስለ አምስት ምክንያቶች ነው፡፡ እነርሱም

ሀ/ ክፍለ ዘመንን ለመናገር፣

ለ/ ክርስቶስን በዘር በሩካቤ ተወለደ ብለውት ነበርና፤ ያለዘርዓ ብዕሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም፣ በመንፈስ ቅዱስ ግብር መወለዱን ለማስተማር ማለትም፤ "ዘእንበለ ይትቃረቡ ተረክበት ፅንሰት እመንፈስ ቅዱስ" ለማለት፣

ሐ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዮሐንስ መጥምቅ ይበልጠዋል ብለውት ነበርና፤ የጫማውን ማሠሪያ ልሸከም የማይገባኝ ለማለት፣

መ/ ጌታችንን በብዔል ዜቡል አጋንንትን ያወጣቸዋል ይሉት ነበርና፤ በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን ያወጣቸዋል ለማለት፣

ሠ/ ጌታን ከነቢያት አንዱ ነው ይሉት ነበርና፤ አምላከ ነቢያት (የነቢያት ጌታ) መሆኑን ለማስተማር አስቦ ነው፡፡

### የወንጌሉ ዋና ዋና መልእክቶች

ማቴዎስ በሕይወቱ ብዙ ልምድ ያለው ሐዋርያ በመሆኑ፤ ጌታ በምሳሌ ያስተማረውን ትምህርት በሰፊው



www.ethiopianorthodox.org

አትቶ ጽፎታል። ይህንም ወንጌል እንደሚከተለው ከፍሎ መናገር ይቻላል።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ አመጣጥና ስለ ሕፃንነቱ፣ (ማቴ. ፩÷፩፣፳፫)፡

በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ስለመጠመቁ፣ (፫÷፩ - ፲፯)፡

በምድረ በዳ ስለመፈተኑ፣ (፬÷፩ - ፲፩)

ወደ ገሊላ ስለመሄዱና በዚያም የመጀመሪያዎቹን ሐዋርያት ስለመጥራቱ፣ (፬÷፲፪ - ፳፭)

ስለ ተራራው ስብከት፣(ምዕ.፭ እና ፯)

ሐዋርያትን መርጦ ስለመላኩ፣ (፱÷፴፫፣ ፲፩፣ ፩)

ጌታ ኢየሱስ ማስተማር ስለመጀመሩ፣(፲፩÷፪-፲፪፣፶)

ስለመንግሥተ ሰማያት ያስተማረው ትምህርት፣ (፲፫÷፩ - ፶፫)

ስለማኅበረ ቤተክርስቲያን ትምህርት፣(፲፰÷፩- ፴፭)

በይሁዳና በኢየሩሳሌም ስለአደረገው ሥራ፣ (፲፱÷፩ - ፴፭፣፶፯)

የጸሐፍት ፈሪሳውያን፣ የሊቀ ካህናቱን የአይሁድ ተቃውሞ እየበረታ ስለመሄዱና ጌታ ኢየሱስም እነርሱን ስለመቃወሙ፣ (፳፩÷፩ - ፳፫)

ስለኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መፍረስና ስለሐሳዊ መሲህ መነሳት፣ ስለህልፈተ ዓለም ስለአሥሩ ቆነጃጅትና ስለፍርድ ቀን፣ (ማቴ. ፳፬÷፩ - ፳፭)

የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸዋትወ መከራን ስለመቀበሉ፣ (ማቴ. ፳፮÷፩ - ፳፯፣ ፳፰)

ከሙታን ተለይቶ በድል አድራጊነት ስለ መነሳቱና የማስተማርና የማጥመቅ ሥልጣነ ክህነት ስለመስጠቱ፣ (ማቴ. ፳፰÷፩ - ፳) ይናገራል።

በአጠቃላይ የማቴዎስ ወንጌል በሰፊው የተጻፈና የተብራራ መሆኑን፤ የቤተክርስቲያን አባቶች በየጊዜው መስክረዋል። በተለይም በሚያምኑና በማያምኑ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የተራራው ስብከት፤ ለምግባረ ሠናይና ለማኅበራዊ ኑሮ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህም በተራራው ስብከት "ወርቃማው ሕግ" በመባል የሚታወቀው፤ "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ፣ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" የሚለው ኃይለ ቃል የማቴዎስን ወንጌል ታላቅነትና ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ያስረዳል።

## ቅዱስ ማቴዎስ

## የኢትዮጵያውያን ባለውለታ

ሐዋርያት ዕጣ ሲጣጣሉ ለቅዱስ ማቴዎስ ፍልስጥ ኤም ደርሶት ነበርና ወንጌል ማስተማሩን በፍልስጥኤም ጀምሮ በሕንድ ፈጽሞአል። የጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች አውሳብዮስ ዘቂሣርያ፣ ሩፊኖስና ሶቅራጥስ፤ በኢትዮጵያ እንዳስተማረና ወንጌልን እንደሰበከ የክርስትና እምነትንም እንዳስፋፋ እርግጠኛ ሊያደርገው የሚችለው ለነገደ ሴም ሐዋርያ በመሆኑ ነው።

እንዲሁም የፍልስጥኤም፣ የፋርስ ባቢሎንና ያኢትዮጵያ ሕዝቦች የተቀራረበ የታሪክ ግንኙነት እንዳላቸው የታወቀ ነው። በተለይም በአይሁድ እምነት ለነበሩ ሁሉ የማቴዎስ ትምህርት ወደ ክርስትና ሃይማኖት ሊመልሳቸው ችሎአል በማለት ጽፈዋል።

የቤተክርስቲያን ታሪክም በሰፊው እንደሚገልጸው ሐዋርያው ማቴዎስ ፳፫ ዓመታት ሙሉ በኢትዮጵያ አስተምሮአል፣ ብዙዎችንም ወደ ክርስትና ሃይማኖት መልሶአቸዋል። እርሱም ባደረገው ስብከት አጊጺስ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ከመላው ቤተሰቡ ጋር ወደ ክርስትና እምነት ተመልሶአል። እጅግ በጣም ቆንጆ የነበረችው ኤፍጊንያ ተብላ የምትጠራው የንጉሡ ልጅ፤ ማቴዎስ ከአባቷ ጋር በተገናኘ ጊዜ ታማ ሞተች። ማቴዎስም በክርስቶስ ስም ከሞት እንድትነሣ አደረጋት። ከዚህም አስደናቂ ተአምር የተነሣ ከላይ እንደተገለጠው መላው የንጉሡ ቤተሰብ አምኖ ተጠምቆአል።

## የጻድቃን ተጋድሎ ምንድነው?

ተጋድሎ ስንል በገድሉ ላይ የተጻፈለትና ሕገ ወንጌልን በቅንነት እየተንከራተተ ሲያስተምር በከሐዲያን ነቀፋ እንደ ደረሰበትና ጭንቀቱን ስቃዩን መራቡን መሰደዱን፣ መታሰሩንና መጋደሉን ማስታወስ ነው።

መቼም የክርስትና ሕይወት የመከራ ሕይወት ፈተና የበዛበት ጠመዝማዛ መንገድ መሆኑ ለሁላችን ግልጽ ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉ ደስታቸውና ክብራቸው በሰማይ እንጂ በምድር አይደለም። ለዚህም ነው እርሱን የሚከተሉ ሁሉ መስቀል (መከራ)የሚፈራረቅባቸው።

በቅዱሳን ታሪክ ውስጥ አንድም ቅዱስ (ቅድስት) በተድላ ፣ በደስታ እየተቀናጡ ኖሩ የሚል የለም። በምድር ላይ፣ በሰይፍ ተሰየፉ፣ ለአራዊት ተሰጡ፣ በእስራት ተሰቃዩ፣ በእሳት ተፈተኑ እንጂ። የሕይወትና የሰላም ባለቤት ራሱን አዋርዶ በሥጋ ማርያም ሲገለጽና የቤዛነቱን ሥራ ሲሠራ በክብር ያልተቀበለው ዓለም፤ እነርሱንም እንደ ማይቀበላቸው፤ " ዓለም ቢጠላችሁ ከናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ" "ለሚጠፉት የወንጌል ቃል የተከደነ ነው። ለእግዚአብሔር ልጆች ግን የተረዳ ነው።" "እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁና እናንተም አሸንፉት" "እኔም ሁልጊዜ ለዘለ ዓለም ከእናንተ ጋር ነኝ።" ስላላችውና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሥጋዊ ሐሳብ ጠፍቶላቸዋል።

ቅዱስ ማቴዎስም ገድሉ እንደሚናገረው፤ በግሪክ (አጵሎን) የተባለ ጣዖት ይመለክበት በነበረ ቦታ በፍልስጥኤም ሲያስተምር፤ በአይሁድና በአረማውያን ላይ ያደሩ አጋንንትን ሲያወጣ በማየታቸው፤ የሀገሩ ሰዎች ወደ እስር ቤት ጣሉት። በእሥር ቤት ውስጥ እያለ አንድ እሥረኛ አጋጠመው። እሥረኛው ዘወትር ሐዘንና ትካዜ ያበዛ ነበርና ሐዋርያው ማቴዎስ አንድ ቀን ጠጋ ብሎ አጽናናው። ለምን እንደሚያዝንና እንደ ሚተክዝ ጠየቀው "ጌታዬ ባለ ጸጋ ነው፤ እኔም በመርከቡ እየተ መላለስኩ እነግድለት ነበር፤ ባለፈው ሰሞን ግን ከንግዱ ስመለስ አልቀናኝም። ማዕበል ተነስቶ መርከቢ ከነዕቃዋ ሰጠመች፤ ገንዘቤን ባሕር በላው። እኔም በስንት መከራ ተርፌ መጣሁና ለጌታዬ የሆነውን ሁሉ ነገርኩት። እርሱ ግን በደረሰብኝ ከማዘን ይልቅ መርከቡን በማስጠሜ ተበሳጭቶ አሰረኝ" አለው። ቅዱስ ማቴዎስ አይዞህ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይፈታሃል በማለት ማንም ተናግሮት እርሱም አስቦት የማያውቀውን ነገር ተናገረው። "ጌታህ ሊቀጣህ ይመጣል፤ በዚህ ጊዜ እባክህ መርከብህ ከባሕር ወጥቶአልና ላምጣው በለው። ወደ ባሕሩ ስትወርድ መርከብህን ታገኘዋለህ" በማለት አጽናናው።

ቅዱስ ማቴዎስ የተናገረው አልቀረም፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ያ ባለጸጋ ሊቀጣው አገልጋዩን ጠራው። እርሱም እንዲታገሰውና ጊዜ እንዲሰጠው ለመነው። አገልጋዩ ወደ ባሕር በወረደ ጊዜ፤ መርከቧ በባሕሩ ላይ ከነሙሉ ሀብቷ ትንሳፈፋለች። እየቀዘፈ አምጥቶ ለባለጸጋው የነገደውን ሁሉ አስረከበው። ባለጸጋውም የሆነውን ሁሉ እንዲነግረው አገልጋዩን ሲጠይቀው አገልጋዩም "የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር የሆነ ማቴዎስ መርከቤን እንደማገኝ ነገረኝና እንዳለውም አገኘሁ" ሲል መለሰለት። ለመሆኑ የት ይገኛል አለ ባለጸጋው በእሥር ቤቱ ውስጥ ወንጌልን እየሰበከ ይገኛል አለው አገልጋዩም።

ያ ባለጸጋም ማቴዎስን አስጠርቶ ክርስትናን በመማር አምኖ ተጠመቀ ቤተሰቡም ተከተሉት። ኤርሚስ የሚባል ካህነ ጣዖት የነበረ ሰው የእግዚአብሔርን ኃይል ያልተረዳ፣ በጣዖቱ በአጵሎን የሚታመን ነበር። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮ ድንቅ ሥራውን እንደሚሠራ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

አልተረዳም ነበርና ሐዋርያው ማቴዎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚያደርገው ተአምራትና የሚያድለው በረከት የማይታመንና ውሸት ስለመሰለው እስኪ በአምላክህ ስም፤ ተአምራት አሳየኝ ስትጠራውም አቤት ይበልህ የማመልከው አምላክ የዓለም ብርሃን፤ ጨለማ የማይቀርበው፤ የዕውራን መብራታቸው ንጉሠ ነገሥት ነው የምትለኝን አምላክ ኃይሉን አሳየኝ አለው።

እርሱም "ጌታዬ አምላኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ምህረ ትህ በእኔ ላይ ትድረስ ጸሎቴን ስማ ብርሃንና ጽድቅህን ላክልኝ።" በማለት አይኖቹን ወደሰማይ በማንሳት ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ ታላቅ ብርሃን በኤርሚስና በማቴዎስ ላይ በራ ኤርሚስም ይህን ብርሃን ሲያይ መሬት ላይ በፊቱ ወደቀ። በዚያች ሀገርም ታላቅ መደነቅና ፍርሃት ሆነ ብርሃኑም ምድር ላይ እንደ ጎርፍ ሆነ። በክርስቶስ ብርሃን አጵሎን የተባለውን ጣዖት በምኩራቡ እንደተቀመጠ ከነአሽንክታቡ ተደመሰሰ።

ሐዋርያውም ኤርሚስን እስቲ እንግዲህ የምታመልከው አጵሎን ጆሮ ካለው ይስማ፤ ኃይል ካለውም ራሱን ያድን አለው። ኤርሚስም በሰው እጅ ተቀጥቅጦና ተጠርቦ የተሠራ ጣዖት ማዳን እንደማይችል ተረድቶ፤ በኃጢአቱ ተጸጽቶ፤ ንስሐ ገብቶ ሐዋርያውን ተከተለ። የአጵሎንና ሌሎች የጣዖት ምስሎች በቅዱስ ማቴዎስ ጸሎት በየወደቁበት ሆነው "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም" በማለት በአፋቸው ተደፍተው መሰከሩ አጵሎንና ሌሎች ጣዖታትም ለቅዱስ ማቴዎስ በተዘጋጀው እሳት ተቃጠሉ ከጣዖት አምልኮ ተመልሰው ሐዋርያውን የተከተሉትም ፰ሺ ያህል ነበሩ። ብዙ ሙታንን በማስነሣት ብዙ ተአምራት በማድረግ ጣዖታቸውን በመደምሰስ በህገ ወንጌል ስለአበራና የእግዚአብሔርን ታላቅነት፤ የሐዋርያውን ክቡርነት፤ የጣዖታቱን ከንቱነት ሕዝቡ ስለተረዳ አብያተ ጣዖታት ተዘግተው በምትኩ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ ሕዝቡም ጭምር በመጠየቁ ቤተክርስቲያን ታነጸላቸው ሐዋርያውም በዚያው ቤተመቅደስ በመቀደስ ሕዝቡን ባረካቸው ኤርሚስ የተባለውን ካህነ ጣዖትም አስተምሮ አጥምቆት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን (ኢጲስ ቆጳስ) ሾመው ሌሎችንም ቀሳውስትና ዲያቆናት ሾመላቸው እምነታቸው እስኪጸና እና በመንፈሳዊ እውቀት እስከሚጎለምሱ አብሮአቸው ተቀመጠ። ይህን ሁሉ በጎ ነገር ማድረጉም በከተማው ሁሉ ተዳረሰ። ይህንን የሰሙት መኳንንትም ማቴዎስን ለንጉሡ ከሰሱት። ንጉሡም በመኳንንቱ ተመርቶ በማቴዎስ ላይ ሞትን ፈርዶበት ጥቅምት ፲፪ ቀን አንገቱን ተሠይፎ ዐረፈ። ባለጸጋውም በድብቅ ወስዶ ቀበረው ከእስር ቤት ያዳነውም በሐዋርያው ሞት እያዘነ በአሥራ አምስተኛው ቀን አረፈ።

በአሁኑ ጊዜ የቅዱሱ አጽም ሰሊርኖ በተባለው ቦታ በኒአኙል ውስጥ በኢጣልያ አገር ይገኛል።


በዚህ ቅዱስ ሐዋርያ ጸሎትና አማላጅነት ፈጣሪያችን ደዌ ሥጋችንን በተአምራት ደዌ ነፍሳችንን በትምህርት ያርቅልን። ቀ

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር አሜን

ምንጭ - ገድለ ሐዋርያት ገጽ 101-118
የቤ/ክ መዝገበ ታላት
volume 10 ገጽ 199 - 204
ቤ/ክ እወቅ ገጽ 96

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



# የእልፍዮስ ልጅ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ

በዲ/ ኃይለሚካኤል ጌታሁን

አምላከ ቅዱሳን በሕይወት ጠብቆ፣ አክብሮና በቸርነቱ ይቅር ብሎ፤ ከኃጢአት ባርነት፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ አውጥቶናል። የማያንቀላፋው ኄር ኖላዊ ( ቸር ጠባቂያ ችን) ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውናና፤ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሚሆን፣ የእልፍዮስ ልጅ የቅዱስ ያዕቆብን ታሪክ በአጭሩ ስንተርክ፤ እናንተም ከቀረበው ታሪክ በቂ ግንዛቤ እንደምታገኙ ተስፋ አለን።

በመጀመሪያ "ሐዋርያ" ማለት የተላከ፣ መልእክተኛ የሚል ትርጉም ሲኖረው፤ በላኪው በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚመረጥ፤ ሥልጣንን ተቀብሎ ትእዛዙን የሚፈጽም፣ የአደራውን ቃል በክብር የሚጠብቅ ነው። እንዲሁም ሃይማኖትን ከምግባር አጣምሮ ለምእመናን ሕይወት ጠቃሚ የሆነውን ሕገ ወንጌል በማስተማር፤ ጨለማውን ዓለም ብርሃን ሊያጎናጽፍ የሚችል፣ የቀች የተዋህዶ ሃይማኖት አርበኛ የሆነና የመልካም ሥነ ምግባር አርአያ ነው።

ለክርስቲያናዊ ትምህርትና ሥነ ምግባር አስፈላጊ የሆኑ መልእክቶች ሁሉ በሐዋርያት ለቤተክርስቲያን ተሰጥቶአል። ይህም የሐዋርያት ትምህርት የሚገኘው በ፴፩ቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለሆነ፤ ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ እንደመሠረት አድርጋ ተቀብላቸዋለች።

ቅዱስ ያዕቆብ ከነዚህ ቅዱሳን ውስጥ አንዱ ነው። ያዕቆብ ማለት አዕቃጺ፣ አኃዚ ማለት ነው። የቀደመው ያዕቆብ ሰኮና ኤሳውን ይዞ እንደተወለደ፤ እሱም ሰኮና ወንጌልን ይዞ ሲያስተምር ይሞታልና። ሰኮና ኤሳውን እንዳሰናከለ፤ እሱም የመናፍቃንን ትምህርት ያሰናክላልና።

ይህ ሐዋርያ ትውልዱ ከነገደ ጋድ ሲሆን፤ የአባቱ ስም እልፍዮስ ይባላል። ቁጥሩም የጌታ ትንሣኤ የዓይን ምስክሮች ከሆኑት ውስጥ ነው፤ በሐዋርያት ዝርዝርም ዘጠነኛውን ይዞ ይገኛል። (ማቴ. ፲÷፫፣ ማር. ፫÷፲፰፣ ሉቃ. ፮÷፲፭፣ የሐዋ. ሥራ ፩÷፲፫)

በዕረፍቱ መታሰቢያ ዕለት የካቲት ፲ ቀን በሚነበበው ስንክሳርና በገድለ ሐዋርያት ታሪኩ ከዚህ እንደሚከተለው ተጽፎ ይገኛል።

ይህ ቅዱስ ሐዋርያ በብዙ ሀገሮች ቅዱስ ወንጌልን ካስተማረ በኋላ፤ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ወደ አይሁድ ምኩራብም ገብቶ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሃይማኖትን ነገር በግልጽ ሰበከ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ እውነተኛ የባሕርይ ልጅ፣ ፍጥረት ከመፈጠሩ በፊት ከአብ ጋር ያለ፣ በአብ ህልው የሆነ፣ የአብ ቃል መሆኑን ገልጾ አስተማረ።

ሰውን በአርአያችን በምሳሌያችን እንፍጠር ያለው እርሱ ነው። እርሱም ሱራፌልና ኪሩቤል በተሸከሙት ሰማያዊ መንኮራኩር (መንበር) በልዕልና ያለ ነው። ኪሩቤልና ሱራፌልም የሚያመሰ ግኑት፤ በሰማያት በልዕልና፣ በጌትነት ክብር፣ በአብ እሪና ያለ ነው። በድንግል ማርያም ማኅፀን የኖረ እርሱ ነው። እርሱም ሰው የሆነ አምላክ ነው።

ይህም ቃል ሐዋርያው አንድም ሰው ሳይፈራ በተሰበሰበው ጉባኤ መካከል ያስተማረው ነው። ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር የባህርይ ልጁ የኢየሱስ ክርስቶስን፤ ቀዳማዊና ደሃራዊ ልደቱን ማንንም ሳይፈራ መሰከረለት።

ይህ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር አብ አንድ ልጁ እንደሞተ፣ እንደተነሣ፣ በልዕልና ወደ አለ ወደ አባቱም እንደ ዐረገ መሰከረለት። በክርስቶስ ማመንን እንዲህ አድርጎ በዚያ ለተሰበሰቡት ሁሉ አስተማረ።

ይህን ምስክርነቱን በሰሙ ጊዜ በዚያ የተሰበሰቡት የአይሁድ ሸንጎ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ላይ ከአባታቸው ከሰይጣን ባገኙት ታላቅ ቁጣ ተቆጡ። ደሙን በከንቱ ለማፍሰስ በመነሳሳታቸው፤ ይህን ሐዋርያ ከመካከላቸው ነጥቀው ወስደው የደሙ ፍዳ በነሱ ላይ እንዲሆን አደረጉ። በሮም ነግሦ በነበረው ቄሳር ፈንታ ያን ጊዜ ቀላውዴዎስ ቄሳር ነግሦ ነበርና፤ እሱን ይዘው በቄሳር ፊት አቆሙት፣ በንጉሡ ፊትም አሳጡት። ይህ ደቀመዝሙር ከቄሳር ሌላ ንጉሥ አለ ብሎ አስተምሯል፣ የንጉሥ ተቃዋሚ ነው በማለት ከሰሱት።

ንጉሡ ይህን በሰማ ጊዜ በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት አላቸው። በዚህን ጊዜ ፈጥነው ድንጋይ፣ ድንጋያቸውን ይዘው ወገሩት፤ እርሱም በፍቅር በሰላም የካቲት ፲ ቀን አረፈ። በመንግስተሰማያት የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። ምእመናንም ሥጋውን ወሰዱ እንደሥርዓቱ ገንዘው፤ በቤተመቅደስ ቀበሩት። ቅድስት የምትሆን በረከቱ በወዳጆቹ በክርስቲያን ላይ አድሮ ይኑር። በዚህ ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ለዘለአለሙ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ለሐዋርያሁ ወሰማዕቱ፣
ለክርስቶስ ዘኮነ በውስተ ዓለም አስተርዕዮቱ፣
ፈጺሞ ሕይወት እንተ ተውህበት ሎቱ፣
ሶበ አልጸቀ ትድሜሁ ወተጸደቀ ዕለቱ፣
በውግረተ ዕብን ኮነ ለያዕቆብ ሞቱ።

## ትርጉም

መገለጡ በዓለም ውስጥ የሆነ የክርስቶስ ምስክርና ሐዋርያ ቅዱስ ያዕቆብን ሰላም እላለሁ። ለእርሱ የተሰጠችውን የሕይወት ዘመን ፈጽሞ ቀኑ በደረሰ ጊዜ የያዕቆብ ሞት በድንጋይ መወገር ሆነ ማለት ነው።

የተወደዳችሁ አንባብያን፤ እንዲህ ያሉ መልካም መዓዛ ያላቸው ቅዱሳንን፤ ከሐዲያን መዘንጋታቸው የሚያሳዝን መሆኑን አስተውሉ። የቤተክርስቲያን ታሪክ ሲነሣ ታላቁን ቦታ የሚይዘው የቅዱሳን ልጆቿ ገድል መሆኑን ልብ ይሏል።

የቤተክርስቲያን ጉዞ ማለት የቅዱሳን ተጋድሎ ነው። ያለ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን፣ ያለ ቅዱሳንም ቤተክርስቲያን አይኖሩም። ቤተክርስቲያን በዓላውያን ነገሥታት፣ በአረማውያን መኳንንትና መሣፍንት ስትገፋ፣ በመናፍቃን ሤራ ስትፈተን ብትኖርና ብትመነምንም እንኳ ሳትበጠስ ለዚህ ትውልድ እንድትደርስ ያደረጋት ልዑል እግዚአብሔር የመረጣቸው የቅዱሳን ልጆቿ ሰማዕትነትና ዘመን የማይሽረው ትምህርታቸው ነው። በመሆኑም ቅዱሳንን ስናከብርና በነሱ አሰረ ፍኖት መጓዝ ስንችል፤ የቅዱሳን ክብራቸው መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከእኛ ጋር ይሆናል። እርሱ ከእኛ ጋር ከሆነም ሐዋርያት በተጋደሉላት ሃይማኖት እንኖራለን። አምላከ ቅዱሳን የቅዱስ ያዕቆብን በረከትና አማላጅነት በልባችን ያሳድርብን አሜን።

ምንጭ -
ስንክሣር የካቲት ፲ ቀን የሚነበበው
ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፪፻፹፫ - ፪፻፹፬

## ሰው ሆይ ልብ በል


ዓለም፣ ዓለም ሲሉሽ ስምሽ ደስ ያሰኛል
ለክርስቲያኖች ግን ምን ይዘሽ መጥተሻል
ምንም አትጠቅሚን በደንብ ላስተዋለሽ
አንቺ የተረገምሽ ፍጹም አታላይ ነሽ።
ታይተሽ የምትጠፊ እንደ ጠዋት ጤዛ
ላታዛልቂ ነገር አታርጊን ፈዛዛ
ከእንግዲህ ይግባን ዳግም አንጠቃ
ዓለም ስለሆነች የዲያቢሎስ ጠበቃ
ትኑረው ብቻዋን ቁርጧን ሁሉ አውቃ።

ከመዘምር ሲሳይ ተረፈ
ሻምቡ መ/ቅ/ሚ/ሰ/ት/ቤት



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



## ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ (ልብድዮስ)

በዲ/ ኃይለ ሚካኤል ጌታሁን

ከሁሉ አስቀድመን ለአምላከ ቅዱሳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን እያልን፤ የእርሱ ባለሟልና እውነተኛ አገልጋይ ተለአኪ የሚሆን የቅዱስ ታዴዎስን ታሪክ በአጭሩ እናቀርባለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ ትውልዱ ከነገደ ዮሴፍ ሲሆን፤ ቁጥሩ እንዲስ ብኩናን፣ ድውያንን እንዲፈውሱ፣ አጋንንትን እንዲያወጡ ሥልጣንን ሰጥቶ ከላካቸው ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው። ይህ ሐዋርያ በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌል ታዴዎስበዕብራዊ(አራማይክ) ልብድዮስ ብለው ሲጠሩት(ማቴ. ፲÷፫፤ማር.፫÷፲፰) በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል የያዕቆብ ይሁዳ፣ በሐዋርያት ሥራ ላይ ባለው ዝርዝር ደግሞ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ተብሎ ተጽፏል፤ ከአስቆሮቱ ይሁዳ የተለየ መሆኑንም ተገልጾአል።(ሉቃ.፮÷፲፮፤የሐዋ.፩÷፲፫፤ዮሐ.፲፬÷፳፪)

ታዴዎስ ማለት ልብደ ሠሪ፣ ዓሣ ወጋሪ ወይም ዘር ወማዕረር ማለት ነው። አሪትን እንደዘር፣ ወንጌልን እንደ መከር አድርጎ አስተምሮአልና። እንዲሁም ስንዴ ዘርቶ ዕለቱን ለመስዋዕት አድርሶአልና።

በቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት የቅዱስ ታዴዎስ ሀገረ ስብከቱ ከኢየሩሳሌም ፩፻፱ ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከምትገኝ ከተማ ሶርያ ነው። በተጨማሪም በፍልስጥኤም፣ በአርመን በመስጴጦሚያና በፋርስ አስተምሯል። ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ ሦስት ታላላቅ ተአምራት እንዳደረገ ገድሉ ይናገራል። እነዚህም፤

### ፩ኛ. ወጺያው ዘርቶ ለፍሬ ማድረስ

ዕጣው እንደወጣ ወደ ሶርያ ሄዶ ለማስተማር ዝግጅት ላይ እያለ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከ መልካም ጎልማሳ ተመስሎ ተገልጾለት። "ወዳጄ ታዴዎስ አይዞህ ምንጊዜም ከአንተ ጋር ነኝ። በሚደርስብህ መከራ ጽና።" በማለት ባርኮትና አጽናኝቶት በክብር በምስጋና ወደሰማይ አርጓል። ከዚህ በኋላ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር እየተጓዙ እንዳለ፤ አንድ ሽማግሌ ሲያርሱ አገኟቸውና ቅዱስ ጴጥሮስ ጠጋ ብሎ "እባክዎ የምንበላው ነገር ይስጡን" በማለት ሲጠይቃቸው፤ ሽማግሌው ደግና ለተራበ የሚያዝኑ ስለነበሩ"ከቤቴ እስከማመጣላችሁ ድረስ በሬዎቼን ጠብቁልኝ" ብለው ወደ ቤታቸው ገቡ። ሁለቱም ሐዋርያት የገበሬውን ደግነት ተመልክተው፤ የመከሩን ጌታ በጸሎት ከጠየቁ በኋላ ታዴዎስ የተጠመዱትን በሮች ሲያርስ ቅዱስ ጴጥሮስ መዝራት ጀመረ።

ታዲዎስ ቀነተ ከመ ይሕርስ ገራህተ
ወጺጥርስ ዘርዐ ፴ አትልምተ
በቁለ ሶቢሃ ወፈረየ ሰዊተ
ሰበአ ሀገር አንክሩ አስመርአዩ ዘንተ

እንዳለ ባለቅኔው የተዘራው እህል በአንድ ቀን በቅሎ፤ አሽቶ ገበሬው ምግብ ይዘው ሲመለሱ አገኟቸው። ይህን ታላቅ ተአምር የተመለከቱ ባዩት ነገር ሁሉ እየተደነቁ ሁለቱን ሐዋርያት "እናንተ ከሰማይ የወረዳችሁ አማልክት ናችሁን" በማለት እግራቸው ሥር በመስገድ ጠየቋቸው። በዚህ ጊዜ ሐዋርያቱ እኛ ከሰማይ የወረድን አማልክት አይደለንም። ነገር ግን ከሰማይ ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ወንጌልን እንድናስተምር ካዘዘን በኋላ፤ ወደሰማያት ያረገው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ፤ የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮችና ስለስሙ እየዞርን ወንጌልን የምናስተምር የምንመሰክር ነን። በማለት የመጡበትን ምክንያትና የሚሄዱበትን ሀገር አስረዷቸው። ወንጌልንም ሰበኩላቸው።

ገበሬውም በአድናቆት እሸቱን ታቅፈው ለሚስታቸው ሊያሳዩ በደስታ ወደ ቤታቸው ሮጡ። የከተማዋ ሰዎችም በነገሩ ተደንቀው ከበቡአቸው። እሳቸውም ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ ተረኩላቸው። ከዚህ በኋላም ቅዱስ ጴጥሮስ ወደኢየሩሳሌም ሲመለስ፤ ሐዋርያው ታዴዎስ በሌሎችም የከተማይቱ አውራጃዎች እየተ ዘዋወረ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስተማረ። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም እያለም ምስክርነት በሕዝብ ፊት ይሰጥ ነበር። ብዙዎችም እግዚአብሔር በቅዱሱ እጅ ያሳየውን ተአምር አደነቁ አመኑም። የከተማዋ መኳንንትም የቅዱስ ታዴዎስን ተአምር ማሳየትና የተከታዩን መብዛት በሰሙ ጊዜ፤ በማድነቅ፣ ንስሐ በመግባትና በማመን ፈንታ በምቀኝነት ተነሣሱ። "ይህ ከአሥራ ሁለቱ አስማተኞች ወገን ሳይሆን አይቀርምና ወደ ከተማችን እንዳይገባ ምን እናድርግ?" ተባ ባሉ። ከመካከላቸውም አንዱ "እነዚህ አሥራ ሁለቱ አስማ ተኞች ዝሙትን ይጸየፉሉና ዘማዊት ሴት በከተማችን በር እናቁም" በማለት ስለመከሯቸው፤ በከተማቸው መግቢያ በር ላይ የታወቀች ዘማዊት ራቁትዋን አድርገው አቆሙአት።

### ፪ኛ.የዘማይቱን ሕይወት ስለ መለወጡ

ሐዋርያው ታዴዎስም ገጠር ገጠሩን ሲያስተምር ውሎ ወደማታ ወደከተማዋ ሲመጣ፤ ያቺን ዘማዊት ሴት በከተማው በር ቆማ አያት። የምታደርገው ሁሉ የሚያጸይፍ ነገር ነበር። ያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በድጋሚ እንዲህ ሲል ጸለየ። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህችን ሴት የዝሙት ሥራ የሚያሠራትና የሚያስታት ክፉ ሰይጣን ይታሠር ዘንድ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን ልከህ በአየር ላይ በራስዋ ፀጉር ይሰቀላት። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ካመነችና አጋንንቱ ከወጡላት በኋላ፤ እንድትወርድ ይሁን ብሎ አመለከተ።

እግዚአብሔርም ቅዱስ ሚካኤልን ወደ ነቢዩ ዕንባቆም ልኮ፤ ለአጫጆች ይወስድ የነበረውን ምሳ በእጁ እንደያዘ፤ በአንዲት የራስ ፀጉሩ አንጠልጥሎ በዚያው ጊዜ ባቢሎን ወደሚባል አገር አድርሶ። ለአንበሳ ምግብ በጉድጓድ ለተጣለው ለዳንኤል እንደመገበው ሁሉ። ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ፣ ከዘማይቷ አጋንንቱን አሳዶ ሴትየዋን ወደአየር አውጥቷት በነፋስ አውታር አንጠለጠላት። ( ተረፈ. ዳን. ፲፫÷፩-፵፪፤ ትንቢተ ዳን. ፮÷፳፪፣ ፲÷፲፫፤ ሰኔ ድርሳነ ሚካኤል) በኋላም ሐዋርያው ጸልዮላት ወረደች። ከሰይጣን ቁራኝነትም ተላቀቀች። ሕዝቡም ይህን ተአምር በዓይናቸው በማየታቸው ብዙዎች አመኑ፣ ከክፉ ሥራቸው ተመለሱ፣ ንስሐ ገብተውም በሐዋርያው እግር ሥር ወድቀው የቀደመውን ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ ምን እናድርግ? አሉ። በትምህርቱና በተአምራቱ ልባቸው ስለተነካ ሐዋርያውን ተከተሉት። በአብ በወልድ ስምም እያጠመቀ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አደረጋቸው። ዘማይቱ ሴትም ተጠምቃ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሆነች። በቤትዋም



www.ethiopianorthodox.org

የክርስቲያኖችን ጉባዔ መሠረተ። በብዙ በታዎች እየተዘዋወረ ሲያስተምር ብዙዎች በሽተኞች ተፈወሱ። እውራን አዩ ሙታን ተነሱ፣ ድዳዎች ተናገሩ፣ አንካሳዎችና ሽባዎች ቆመው በትክክል ሄዱ። በቅዱስ ታዴዎስ አማላጅነት፤ በአጠቃላይ የመፈወስና ሙት የማስነሳት ታላላቅ ተአምራት ተከናወኑ።

"መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ"(መዝ. ፷፯÷፴፭)። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው እንዳለ ክቡር ዳዊት በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ አሁንም ለማይጠራጠር ትውልድ ሁሉ በረከቱ በሰው ልጆች ላይ እጽፍ ድርብ ነው ብለን እናምናለን። ምክንያቱም ቅዱሳን ደማቸው በፈሰሰበት፣ አጽማቸው በተከሰከሰበት፣ ገድላቸው በተፈጸመበት፣ ወዛቸው በነጠበበት ሥፍራና እንዲሁም በስማቸው አብያተክርስቲያ ናት በታነጹበት ሁሉ፤ ተአምራት ሲያደርጉ ይኖራሉ። የክብራቸውና የቅድስናቸው ምልክትም ይህ ነው። የቅዱስ እግዚአብሔር ምስክሮች ናቸውና።(መዝ.፴፫÷፳፣ሉቃ.፳፬÷ ፵፯)

## ፫ኛ. ግመልን በመርፌ ቀዳዳ እንዳሳለፈ

አንድ ቀን ቅዱስ ታዴዎስ "ባለጸጋ መንግሥተ ሰማ ያት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብታልፍ ይቀላል።" እያለ ሲያስተምር አንድ ባለጸጋ ሰማና፤ በአጠገቡ ወደሚያል ፉት የግመል ነጋዴዎች እያመለከተ "እስኪ የተናገርከውን አድርገህ አሳይ" በማለት ጠየቀው። ሐዋርያው ታዴዎስም አንድ ብረት እንጣሪ ክርስቲያን ወዳጅ ነበረውና መርፌ ሠርቶ እንዲያመጣለት ላከበት። ያም ወዳጁ የጠቀመው መስ ሉት ቀዳዳውን አስፍቶ ሰጠው። ቅዱስ ታዴዎስ ግን ቀዳዳው እንደሌላው መርፌ እንዲሆን አስደርጎ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት ጠይቆ፣ ግመሏን በመርፌ ቀዳዳ አሾልኮ አሳ የው። በወንጌል እንደተጻፈው ደቀመዛሙርቱ ጌታችንን "እኛ ልናወጣው ያልቻልነው ስለምን ነው?" ብለው ለጠየቁት "ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው . . . የሚሳናችሁም ነገር የለም" እን ዳለ ይህንንም ልንጠራጠር አይገባም። (ማቴ .፲፯÷፲፬ - ፳፩)

## የመጨረሻ እረፍት

ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ ወንጌልን እየተዘዋወረ በመስበኩ፣ ብዙ ተአምራት በማድረግ ብዙዎችን ወደቀናች ሃይማኖት መልሶአል። በተለይም በእርሻው ላይ በአንድ ቀን ስንዴ ዘርተው ለፍሬ ያደረሱላቸው ሽማግሌ በተደረገው ነገር ልባቸው ስለተነካ፤ ሐዋርያው እግር ስር ወድቀው በመማጸን "እድን ዘንድና የቀደመውን ኃጢአቴን ፈጣሪ ይቅር ይለኝ ዘንድ ምን ላድርግ" በማለት ሲጠይቁት፤ እግዚአብሔር አምላክን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍሉም እንደበትህ ውደድ። አትግደል፣ አታመንዝር፣ በሐሰት አትማል፣ ሌሎች ሊያደርጉብህ የማትወደውን ሁሉ በሰው ላይ አታድርግ ብሏል። የህን የነገርክዎትን ምክር ከፈጸሙ የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳሉ አላቸው። እሳቸውም ያለጊዜው እርሻዩ በፍሬ ሲሞላ እያየሁ ምን አስቀምጠኛ፤ እናንተን ተከትየ እዋላችሁበት ልዋል፣ ከምታድሩበት ልደር፣ ሁሉን ትቼ ልከተላችሁ ፍቀዱልኝ እስከማለት ደረሱ፤ በቤታቸውም ወስደው ጋበዟቸው። ቅዱስ ታዴዎስ ብዙዎችን አስተምሮ፣ አጥምቆ ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደገቢረ ጽድቅ መልሶአቸዋል።

ከሕዝቡም መካከል ብዙዎች የቀደመ ኃጢአታቸውን ትተው፣ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክቡር ስም ገናንነት አምነው፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት ገድል ትሩፋት በመሥራት በጠባቧ አንቀጽ በመሄዳቸው፤ ከኃዲያን በምቀኝነት ተነሳሱና በሐዋርያው ላይ ብዙ ግፍ አደረሱበት። በገመድ አንገቱን አንቀውም እሰቃ ዩት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንዳይጠራና በስሙ እንዳያስ ተምር አጥብቀው አዘዙት።እርሱ ግን ሳይፈራ ሳያፍር የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት፣ የባሕርይ አምላክነት፣ የሁሉ ቤዛ መሆኑን እስከሞት ደርሶ መስከረለት። እንዲህ ነው የቅዱሳን ሕይወት፤ ስለ ስሙ በጸጋ በእኮቴት ሳያማርሩ በክብር ጸዋትዎ መከራን ተቀብሎአል። ሐምሌ ፪ ቀን በሰማዕትነት ያረፈበትን ዕለት በሚያስታውሰው የቤተ ክርስቲያናችን ስንክሣር መጽሐፍ የተጻፈለትን አርኬ ከዚህ እንድሚከተለው ነው።

ሰላም ለታዴዎስ ምንዳቤ ሕንቀት ዘተወክፈ፣
እንዝይነ ጥሪቱ ወብዕሉ አመባዕለ ዘለፈ፣
ለትውልድ ጸኃሪ እስከ ተአምሩ ተጽሕፈ፣
ሰቀለ በከፋስ ብእሲተ ዘትዚሙ ዘልፈ፣
በሰቁረተ መርፍዕ ካዕበ ገመለ አኅለፈ

ትርጉም

በመታነቅ መከራን የተቀበለ
ቅዱስ ታዴዎስን ሰላም እላለሁ፤
ባለጸጋን በሐብቱ ምክንያት
ሳያፍር ስለነቀፈ፤
ለቀሪው ትውልድ
ተአምሩ እስከሚጻፍለት ድረስ፤
አመንዝራዋን ሴት
በአየር ላይ እንድትሰቀል አደረጋት፤
ደግመኛም ግመልንም
በመርፌ ቀዳዳ አሳለፈ ማለት ነው።

እንግዲህ የቅዱስ ታዴዎስ የተዋሕዶ አርበኝነቱ በቤተክርስቲያናችን በክብር ተጽፎ ስለሚገኝ ሥራውና አማላጅነቱ እስከ ዕለተ ምፅአት ሲነገር ይኖራል። በብዙ መከራ ቢፈተንም"ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር" የእውነተኛ የደግ ሰው ረፍቱ በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው"ስለሚል በክብር አርፎአል።(መዝ. ፻፲፭÷፮ እንድምታ)

ጸሎቱና በረከቱ በእኛ በልጆቹ አድሮ ይኑር።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ


ምንጭ -


- ስንክሣር ሐምሌ ፪ ቀን
- ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፪፻፮ - ፫፻፭
- በኢ.ኦ.ተ.ቤተክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ገጽ ፶፬
- ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ ገጽ ፩፻፪
- The Oxford Dictionary of the xian church p. 1337
- The Oxford Dictionary of Saints p. 225 New - Bible Dictionary third eddition p.




www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



## ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል (ስምዖን ቀነናዊ)

ሐዋርያትን በአፅናፈ ዓለም ያጸና ቸር ጠባቂያችን መድኃኔዓለም ክርስቶስ በሕይወት ጠብቆ ለቀጠሮ ስላበቃን ክብር ምሥጋና ይድረሰው። ከአሥራሁለቱ ሐዋርያ አንዱ የሆነ የጌታ ባለሟል የቅዱስ ናትናኤል (ስምዖን ቀነናዊ) ገድልና ትአምር በአጭሩ ስናቀርብ ለእኛ መማለፅ እንደሚገባን ምሥጢሩን ጥበቡን፣ለአንባብያንም ማስተዋሉን ይገልጽልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ይህ ሐዋርያ ብሔረ ሙላዱም ከነገደ ብንያም ሲሆን በገሊላ አውራጃ በቃና ነበር። የትውልድ ዘመኑም ጌታ በተወለደበት በሔሮድስ ቀታሌ ሕፃናት ዘመን ሲሆን የስሙ ትርጓሜ "ናትናኤል" ማለት ውሁብ፣ ሀብተ እግዚአብሔር ቀነናዊ ማለት የቃና ሰው ቀናኢ ለሕገ አምላኩ የሚቀና ማለት ነው።

ናትናኤል ሕገ ኦሪትና የነቢያትን መጻሕፍት የሚያውቅ የተማረ ነበ ርና ለሕገ ኦሪት፣ ለሕገ ነቢያት፣ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የሚቀና ነበርና በዚህ ምክንያት ነው ቀናኢ ቀናተኛ ተብሎ የተሰየመው። እርሱም በሃይማኖቱ ደግ እውነተኛ ንጹህ ሰው ነበር ለሰው ፊትም የማያደላ አልነበረም። ባለጸጋ ነውና ልፈረው ድሃ ነውና ልድፈረው ባለጸጋ ነውና ላክብረው ድሃ ነውና ላዋርደው ፤ ባለ ዳባ ከባለ ዳባ፣ ባለካባ ከባለ ካባ የማይል ለሰው ፊት የማያደላ ጻድቅ ሰው ነበር።

በትርጓሜ ወንጌል እንደተገለጸው ቀዳማውያን አርድእተ እየሱስ የተባሉት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት የነበሩት ቅዱስ ዮሐንስና እንድርያስ ናቸው። እነርሱም የመምህራቸውን የመጥምቁ ዮሐንስን ምስክርነት ሰምተው ጌታችንን ሲከተሉት ቅዱስ እንድርያስ ደግሞ ወንድሙን ቅዱስ ጴጥሮስን (ስምዖንን) ወደ ጌታችን ወሰደው። ጌታችንም እነር ሱን ሦስቱን በደቀመዝሙርነት ከተቀ በላቸው በኋላ ወደ ገሊላ ሲሄድ ፊልጶስን አግኝቶ ተከተለኝ አለው ፊልጶስም ጓደኛውን ናትናኤልን አግኝቶ ስለእርሱ ሙሴም ነቢያትም የጻፉለትን አይሁድ የዮሴፍ ልጅ የሚሉትን ከናዝሬት የተወለደ ናዝራዊ እየሱስን አገኘነው ብሎ በነገረው ጊዜ ናትናኤል ለሰው የማያደላ በመሆኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ይወጣ ዘንድ በውኑ አለውን? ብሎ ጠየቀ እንጅ እውነት ነው ብሎ ለሰው ፊት አድልቶ አልተ ቃለለም ፊልጶስም በቃል ማስረዳት ስላልቻለ መጥተህ በዓይንህ ተመልክተህ ተረዳ አለው ።

ናትናኤል ከፊልጶስ ጋር ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ጌታ በእውነት በልቡ ክፋት ሽንገላ የሌለበት የዋህ በእግዚአብሔር የሚያምን እስራኤላዊ ብሎ ስለ ናትናኤል ተናገረ። ናትናኤልም ጌታ ያመሰገነውን ምሥጋናና ውዳሴ ሳይቀበል በምን ታውቀኛለህ የት ታውቀኛ ለህና ነው እኔን ክፋትና ሽንገላ የሌለብህ የዋህ ሰው ያልከኝ በማለት ጠየቀ። ጌታችንም ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሆነህ አየሁህ አለው ። በትርጓሜ ወንጌልም በሔሮድስ ዘመን ሕፃናት በሚገደሉበት ጊዜ እናቱ በቀፎ አድርጋ ከበለሱ ሥር ሰውራው ነበርና ይህንንም ከእናቱና ከእርሱ በስተቀር ያንን ቦታ ማንም አያውቅም። ጌታችን ግን ያን ጊዜ ያዳንኩህ እኔ ነኝ ሲል በተጨማሪም ምሁረ ኦሪት ነበርና ከበለስ በታች ሆኖ የተነገረው ትንቢት ቀረ የተቆጠረው ሱባኤ ደረሰ እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ይውል ነበርና ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ እንዳለው ተገል ጿል። ናትናኤልም ከሚገደሉት ሕፃናት አንዱ ሆኖ ሳለ እንዴት እንደተረፈ ማን እንዳዳነው በኋላም ፊልጶስ ሳይጠራው ከበለስ በታች ሆኖ በሀሊናው ያወጣ ያወርድ የነበረውን ማንም ሊያውቀው የማይችለውን የልቡናውን ምስጢር የተሰወረውን የተሸሸገውን በማወቁ የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ መሆኑን ተረዳ ስለዚህም መምህር ሆይ በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ለእስራኤልም ንጉሣቸው አንተ ነህ በማለት መሰከረ። ከናዝሬት ደግ ሰው ሊወጣ አይችልም የሚል ጥርጣሬውን አስወገደ። (ዮሐ. ፩:፵፬-፶)

ጌታችንም ከበለሱ ሥር አየሁህ ስለአልኩህ አመንክ ከእንግዲህ ወዲህ ዕውቀቱ ከሌዋውያን ካህናት ጌትነቱ ከምድራውያን ነገስታት የሚበልጥ ልዩ መሆኑን ለማስረዳት ሦስት ዓመት ከመንፈቅ የማስተምረውን ትምህርት የምሠራውን ተአምራት ታያለህ ትሰማለህ ሁላችሁም ሰማያተ ሲከፈቱ የእግዚ አብሔር መልእክተኞች ወደ ወልደ እጓለ እምሕያው ክርስቶስ ሲወጡ ሲወርዱ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ እያሉ ርደቱን ዕርገቱን ሲመሰክሩ ታያላችሁ አላቸው።

በኋላም ጌታችንን ይከተሉት የነበሩትን ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ከእነርሱም አስራ ሁለቱን መርጦ ሐዋርያት ብሎ ሲሾማቸው በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌል በ፲ኛ ተራ በሉቃስ ፲ኛውን ተራ ይዞ የሚገኘው ይህ ደቀመዝሙርም የሐዋርያነት ሹመት አግኝቷል። በጸሎተ ሐሙስም ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ ሳለ ጌታችን ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጠኛል ባላቸው ጊዜ በሁኔታው ካዘኑትና እኔ እሆንን ብለው ከጠየቁት አንዱ ነበር ከዚያም ወደ ደብረዘይት ወጥተው ጌታችን በዚህች ሌሊት ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ ከተነሳሁ በኋላ መታየትን በገሊላ እቀድማችኋለሁ በሚላቸው ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስም ሁሉም ሲክዱህ እኔ አልክድህም አለው። ይህ ሐዋርያም ከደቀመዛሙሩቱ ጋር እንደ ቅዱስ ጴጥሮሰ ሞትህን ሞት እናደርጋለን ብሎ ነበር (ማቴ.፳፮÷፴፫-፴፭)

ጌታችን ሦስቱን ባለሟሎች ቅዱስ ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ሲመለስ ከ፲ሩ ደቀመዛሙርት ጋር ቅዱስ ናትናኤልም በእንቅልፍ ተይዞ ተኝቶ ነበር። ጌታችንም ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ወደ መከራ ወደ ገሃነም እንዳትገቡ ተግታችሁ ለምኑ ብሎ መክሯቸዋል ከዚህ በኋላ የሚያሲዘኝ ይሁዳ መጥቷል ተነሡ እንሂድ ብሎ ወደ ይሁዳ፣ ሾተልና ጎመድ ይዘው ይሁዳን ተከትለው ወደመጡትም ሠራዊት በፈ ቃዱ ሄደ። እነርሱም ጌታን እጅንተው ያዙት ጌታም ዘወትር በምኩራብ ከእናንተ ጋር ሳስተምር እኖር ነበር ለምን አልያዛችሁኝም? ይህ ሁሉ የተደረገ ነቢያት የተናገሩት ነገር ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ብሎ ከተናገረ በኋላ ጥለውት ከሸሹት ሐዋርያት አንዱ ሐዋርያው ናትናኤል ነበር ሐዋርያው ናትናኤልም ሆነ ሌሎቹ ሊሸሹ የቻሉት (በማቴ. ፳፮÷፴፩) ላይ "ጌታችን እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፎ አልና። በዚህች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ" ብሎ ነቢዩ በነቢዩ ዘካርያስ ፲፫÷፯ ላይ የተናገረውን ትንቢት ጠቅሶ እንደሚፈ ጸምባቸው በመናገሩ ነው። በጌታ ትንሣኤ ጊዜ በመጀመሪያ የተገለጸላቸው ማርያም መግደላዊትና ባውፍልያ ሲሆን ጌታችን ገሊላ ይሄዱ ዘንድ ለወንድሞቼ ሄዳችሁ ንገሯቸው ብሎ እንዳዘዛቸው ከአሥሩ ደቀመዛሙርት ጋር ይህ ሐዋርያ አብሮ ወደገሊላ በመሄድ ጌታን ባየ ጊዜ ሰግዶለታል።



www.ethiopianorthodox.org

አሥራ አንዱም በዝግ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ሐዋርያው ናትናኤል አብሯቸው ነበር።

ጌታችንም በመካከላቸው ተገልጾ ትንሣኤውን እንዲያምኑ በቀናት የተቸነከሩ እጆቹን፣ እግሮቹን፣ በጦር የተወጋ ጎኑን አሳያቸው ስመ ሕይወት መድኃኒት እንደሆነ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለህዝብ ሁሉ ያስተምሩ ዘንድ መጻሕፍትን እንዲያውቁ አዕምሮአቸውን ከፈተላቸው፣ የመጻሕፍትንም ምሥጢር ገለጠላቸው፣ ከሰማይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስኪሰጣቸው በኢየሩሳሌም እንዲቀመጡ አዘዛቸው። ከዚያም እስከ ቢታንያ ድረስ አውጥቶ በአንብሮተ እድ ከአዋቂ ናነት እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕርግ ሾማቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤልም ይህንን ሹመት ከጌታችን ከተቀበሉት አስራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው።(የሐዋ. ፩÷፲፫)


በግብረ ሐዋርያትም እንደ ተገለጸው የጌታችንን ዕርገት በደብረ ዘይት ከተመለከቱ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ወደሚያድሩበት አዳራሽ ገብተው በህብረት ከሚጸልዩት ሐዋርያት አንዱ ይህ ሐዋርያ ነበር በአስቆሮቱ ይሁዳም ምትክ አስራ ሁለተኛ ሆና የሚቆጠር ለመምረጥ አብሮ ጸሎት አድርጓል።

ጌታችን ባረገ በአስረኛው ቀን ፩፻፳ ቤተሰብ በጽርሐ ጽዮን በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ ይህ ሐዋርያም ተገኝቶ ፸፩ ቋንቋ ተገልጾለታል። በመጨረሻም ይህን ዓለም ዕጣ በዕጣ ብለው ተካፍለው ለማስተማር በተሰማሩበት ጊዜ እርሱም በዐርያ፣ በባቢሉን፣ በግብጽና በኑቢያ አስተምሯል። ግንቦት ፲፩ ቀን በሚነበበው በመጽሐፈ ስንክሳር እንደተገለጸው፤ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ወደ አረማውያን ዘንድ በመሄድ ወንጌለ መንግሥትን ሰበከ፡ ብዙ አህዛብን በትምህርቱ፣ በተአምራቱ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ በመመለስ ጥምቀትን በማጥመቅ ብዙዎችን ክርስቲያኖች አድርጓቸዋል። እሊህም አረማውያን በጎቻን እየነጣጠቁ እንደሚበሉ ተኩላዎች ነበሩ እርሱ ግን በማስተማሩ የአውሬነት ጠባያቸውን ለውጦ እንደ በግ ገራሞች አድርጓቸዋል ይህም ማለት ከአረማዊነት ወደ ክርስቲያንነት መለሷቸዋል። በትምህርተ ወንጌልም ልቡናቸውን ብሩህ በማድረግ በኃጢአት ምክንያት የነበረባቸውን ድንቁርናን፣ ስንፍናን አርቆላቸዋል። ትምህርተ ወንጌልንም ለማስፋፋት ማለትም ወንጌልን ካልደረሰበት ለማዳረስ በራጥያ ወደ ሚባል ሀገር ሄደ በዚያም የክርስቶስን የጌትነቱን ነገር የምትናገር ለሚያምኑባት ደስታ፣ የምሥራች የምትሆን ወንጌልን ሰበከላቸው።

ትምህርቱን ያላመኑ፣ እግዚአብሔርን የካዱ አረማውያን፤ በጠላትነት ተነሳስተው ያዙት። እሊህም ከሀድያን ከየሀገሩ ሁሉ የተውጣጡ ነበሩ። አሥረው ወደገዢው ወሰዱት፣ ገዢውም እንዲታሠር አደረገ። ብዙ ጸዋትወ መከራ እጅግ ከባድ የሆነ ስቃያትን አደረሱበት፤ ምንም እንዲህ ያለ መከራ ቢያደርሱበት መከራውን የሚጸጸምበት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጨመረለት። እግዚአብሔርም አጸናው፣ መከራውን እንዲችል አደረገው፣ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው አምላክ በእጁም ድንቅ ድንቅ ምልክትና ተአምራትን አደረገለት። እሊህም ተአምራት ብዙዎች ነበሩ፤ ከነዚህም መካከል ሙታንን ያስነሳበት ጊዜ አለ፣ ከእነርሱም ከበሰበሱ ሰውነታቸው ከበሰበሰ ከተላ በኋላ በተአምራት አስነሳቸው። ከነሱ መካከልም ሥጋቸው ረፍፎ፣ ደረቅ አጥንታቸው ህይወትን አግኝቶ እንደገና ከሙታን እንዲነሱ አድርጓል። ሞተው የተነሱትንም ለክርስትና የሚያበቃ በሥላሴ ስም ሸማየ ገቦ አጥምቋቸዋል፣ ሌሎችንም ታመው ብዙ ዘመናት ያልጋ ቁራኛ፣ የደዌ ዳኛ ከሆኑ በኋላ ፈውሷቸዋል። አንድ ለምፃም ሰው አምኖ ክርስትና በሚነሳበት ጊዜ ብፁዕ ናትናኤል ሲያጠምቀው ከለምፁ ነጽቷል። ከዚህ በኋላ እነዚያ ከዳተኞች አረማውያን ናትናኤልን ይዘው በእንጨት ላይ ሰቀሉት። ግንቦት ፲፩ ቀን ነፍሱንም ለፈጣሪው አደራ ሰጠ። በመንግሥተ ሰማያትም የሰማዕትነት አክሊልን ተቀዳጀ። ጸሎቱና በረከቱ ከህዝበ ክርስቲያን ሁሉ ጋር ለዘላለሙ አድሮ ይኑር አሜን በእውነት ያለ ሀሰት ይሁንልን ይደረግልን።

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት



## ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ

በዲ/ኃይለ ሚካኤል ጌታሁን

የቅዱሳን አምላክ በቅድስናው ቀድሶ፣ በከኃሊነቱ ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ ጠብቆ፣ በጤንነት ለዚህች ዕለትና ሰዓት ያበቃን ልዑለ ባህርይ አምላካችን እግዚአብሔር፤ በእኛ በልጆቹ አንደበት የተመሰገነ ይሁን። የሐዋርያትን ገድልና ታሪክ በአጭሩ በምናቀርብበት በዚህ ዓምድ፤ በሐዋርያት ዝርዝር ውስጥ የመጨረሻውን ቦታ ይዞ የሚገኘውን የቅዱስ ማትያስን ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናልና፤ ምሥጢሩን ጥበቡን ለሊቃውንት የገለጸ አምላክ ለእኛም ይገልጽልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

በቅዳሴ ሐዋርያት ክፍል ፩ ቁጥር ፲፭ ገጽ ፩፻፲፬ ላይ እንደተገለጸው፤ ማትያስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው። አንድም ማትያን ማለት ምትክ ማለት ነው። ይኸውም ጌታን አሳልፎ ለ፴ ብር በመሸጥ በፍቅረ ነዋይ ክብሩን በመለወጥ፤ ራሱን ባቃለለውና በመጨረሻም በገዛ እጁ ታንቆ በሞተው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የተሾመ ሐዋርያ ነው።(ሐዋ. ፩÷፲፭-፳፮)።

አስቀድሞ ቁጥሩ ከሰባ ሁለቱ አርድእተ ክርስቶስ እንደነበር የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ መስክሮአል። በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደተገለጸው ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወጣበት በገባበት ሁሉ ከሐዋርያት ጋር አብረው ይከተሉ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ማትያስ ነበር።

የትንሣኤው ምስክር ሊሆኑ ከሚገባቸው አንዱ የነበረው የአስቆሮቱ ይሁዳ፤ ጌታን ክዶ ከሐዋርያት ማኅበር በመለየቱ በምትኩ ሌላ ሐዋርያ መተካት አስፈላጊ ስለሆነ። መቶ ሃያ ቤተሰብ በአንድ ላይ ተሰብስበው በነበሩበት ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ንግግር አድርጎ ፲፪ኛ ሰው ለመምረጥ ተስማሙ። ምርጫውም በዕጣ እንዲሆን ተወሰነ። በዚህን ጊዜ በደግነታቸው የታወቁትን "ወአቀሙ ክልኤተ ዮሴፍሃ ዘተሰምየ በርናባስ ዘይብልዎ ኢዮስጦስ ወማትያስሃ" በአንድ ልሳን ኢዮስጦስ የሚሉት በርናባስ የተባለ ዮሴፍንና ማትያስን ሁለቱን መርጠው በፊታቸው አቁመዋቸዋል። ዕጣውም በማትያስ ላይ ወጣ። (የሐዋ ፩÷፳፫)

በሐዋርያት ሥራ ፩÷፳፮ እንደተገለጸው ሐዋርያትን ሁለቱን እጣ ያጣጣሉበት ምክንያት የበቃውና ያልበቃውን የማያውቁ ሆነው አይደለም። በአእምሮ ያልበሰሉ፣ የሐዋርያትን ማዕረግ ያላወቁ፣ በሰው ሰውኛ ሥርዓት ተዘምደተ ሥጋ ቢኖራቸው ነው፤ ከእከሌ ይልቅ ለእከሌ አድልተው የመረጡት በማለት እንዳይሳሳቱ ወይም መማለጃ በልተው ይሆናል ብለው እንዳይሰናከሉ ምዕመናንን ለማሳወቅ ሲሆን በሌላ በኩል ሥርዓት መሥራታቸው ነው። ይኸውም ለመንፈሳዊ ሹመት የበቁ ሁለት ሰዎች ቢገኙ፣ በምርጫ እኩል ድምጽ ቢያገኙ ጸሎት ተደርጎ በእጣ መምረጥ እንደሚገባ ለአብነት እንዲሆን ነው።

በተጨማሪም ዕጣው ለማትያስ ወጣለት፣ ወጣበትም ተብሏል። ይኸውም ወጣለት ቢሉ ዋጋ የሚያገኝበት ስለሆነ ይኸውም መንፈሳዊ እሴት ነው። ለሐዋርያነት የበቁ፣ በሐዋርያነት ግብር ላሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ፍጹም ክብር ነው። ዕጣው ወጣበት ተብሏል በሐዋርያነት አገልግሎቱ ከኢአማንያን መከራ የሚቀበልበት ስለሆነ። የማትያስ ምርጫ ጌታ ካረገ በኋላ ስለሆነ፤ በወንጌላውያኑ ውስጥ ተጠቅሶ አይገኝም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለእርሱ ብቸኛ ምስክር የሆነው ሉቃስ የጻፈው የሐዋርያት ሥራ ብቻ ነው።

የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ሐዋርያው ማትያስ በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ በግብጽ በቀጰዶቅያና በኑቢያ እንዲሁም በኢትዮጵያ አስተምሮአል። በኢትዮጵያም ስለ ማስተማሩ በፈረንሳዊው ሊቅ በሞሬ የመጀመሪያው መጽሐፍ ገጽ፫፻፲፰ የተገለጸ ሲሆን ቃሉም " በኢትዮጵያ ንጉሥ ሰጥታ /አካጥታ/ ስመ መንግሥቱ ጽንፈ አርዕድ ዘመን በአርባ ዓመተ ምሕረት ከሐዋርያት ስድስቱ መጥተው ኢትዮጵያን ወንጌል አስተምረዋል እነሱም ፩ኛ ቅዱስ ማቴዎስ ፪ኛ ቅዱስ ማትያስ ፫ኛቅዱስ ቶማስ ፬ኛ ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ፭ኛቅዱስ ስምዖን ቀነናዊ በኋላ ናትናኤል የተባለው ፮ኛ ቅዱስ በርቶሎሚዎስ ናቸው።"(ሐዋ. ፩÷፳)

መጋቢት ፳ ቀን የሚነበበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስንክሳር የሚከተለውን ይተርካል። እንደ ሐዋርያው እንደ እንድርያስ ማትያስም ወንጌልን ለማስተማር በሄደ ጊዜ ሰውን በሚበሉ አሕዛብ እጅ ወደቀ። እነርሱም ለጊዜው በእስር ቤት አስቀምጠውት ነበር። እግዚአብሔር ጎርፍ ሰዶ እስር ቤቱን አፈራረሰው። ማዕበሉም ሕዝቡን እስከአንገታቸው ዋጣቸው። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ማዕበሉ እንዲመለስላቸውና እንዲያጠምቃቸው ለመኑት። እርሱም አስተምሮ በወንጌል አሳምኖ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የክርስትናን ጥምቀት አጠመቃቸው ይላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በገድለ ሐዋርያት እንደተገለጠው የማትያስ ሀገረ ስብከት "በላዕተ ሰብእ" የሚባሉ ሰዎች ወደሚኖሩበት ሀገር ነው ። ይህ ሀገር እስኩቴስ(ሩስያ) ሳይሆን እንደ ማይቀርና አውሳብዮስ በቤተክርስትያን ታሪክ መጽሐፉ ይህ ቦታ በጥንቱ ዓለም አጠራር በርባሮስ ይባል የነበረው ቦታ መሆኑን ሲገልጽ ዜና አይሁድን የጻፈው ዮሴፍ ወልደኮርዮን ደግሞ የበርባሮስ/እስኩቴስ/ ሰዎች በዚያ ዘመን ጨካኞችና ከአራዊት ያልተሻሉ አረመኔዎች እንደነበሩ ገልጦአል።

ይህ ሐዋርያ በዚህ ሀገር ሲያስተምር፤ እነዚህ ሰዎች ያዙትና ዓይኑን አውጥተው እንደ እንስሳ ሣር ያበሉት ጀመር። ምክንያቱም የዚህ ሀገር ሰዎች ሰውን ከመብላታቸው በፊት ዓይኑን አጥፍተው ለ፴ ቀናት ያህል ሣር ማብላት ልማዳቸው ስለነበር ነው።

ቅዱስ ማትያስ ለ፴ ቀናት በእስር ቤት ተቀመጠ። እግዚአብሔርም ጽናቱን ስለሰጠው ያቀረቡለትን ሣር ሳይበላ በጾም በጸሎት በዝማሬ አሳለፈው።

በአርባኛውም ቀን ማትያስ ሣሩን ከፊቱ ከምሮ ሲዘምር፤ ቅዱስ እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በእስር ቤቱ በር ገባ። በደስታና በናፍቆት መንፈሳዊ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፤ "እንደበጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ የሚለው ቃል ዛሬ በአንተ ተፈጸመ" ሲል የወንጌልን ቃል አስታወሰው። ከእስር ቤትም ይዞት ወጣ አብረውት በዚያ ታሥረው የነበሩ ፩፻፳፫ ሰዎችም በነሱ ትምህርትና ባሣዩት ተአምራት አምነው ተጠምቀው ከእስር ቤት ወጡ የሀገሪቱ ሰዎችም አመኑ ይላል። በስንክሣሩ ላይ የተጻፈለት አርኬ የተባለ አጭር ግጥም እንዲህ ይላል፤

ሰላም እብል ዘተኃርየ ወተፈቅረ፤<br>
ህየንተ ይሁዳ ይትኍለቁ ምስለ ሐዋርያት ኀቡረ፤<br>
ከዊና ማትያስ በላዕለ እኩያን ኄረ ፤<br>
ሥጋሁ ቅዱስ ሴሰዮሙ ወደሞ ክቡረ፤<br>
ተውላጠ ሴሰይዎ ሉቱ ከመ ሳህም ሣዕረ።

ትርጉም

ቅዱስ ማትያስ በክፉዎች ዘንድ ደግ ሆኖ፤ በይሁዳ ምትክ በሐዋርያት ስለተመረጠ ሰላም እላለሁ፤

ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ

ከገጽ ፲፭ የዞረ

እንደላም ሣርን እንዳበሉት፤ እሱ ግን አጸፋውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መገባቸው ማለት ነው::

## አሳቱ እንዳላቃጠለው

ቅዱስ ማትያስ ከዚህ በኋላ ደማስቆ ገብቶ ስብከተ ወንጌሉን ቀጥሏል:: የደማስቆ ሰዎች ግን አስቀድመው ከኢየሩሳሌም ወደከተማቸው በገቡት አይሁድና በአረማውያንም ቅስቀሳ ተቃዋሚዎች ተነስተው በብረት አልጋ በማስተኛት ከሥሩ ለሰባት ቀናት ያህል እሳት ለቀቁበት:: በሰባተኛው ቀን ፊቱ እንደ ፀሐይ እያበራ አንዳች ጉዳት ሳይደርስበት ከእግር ጥፍሩ እስከ እራስ ጸጉሩ ድረስ የእሳቱ ወላፈን ሳይነካው ጥላሸት እንኳን ሳያርፍበት ተገኘ::

ከዚህ በኋላ በተጨማሪ ለ ፳፱ መዓልትና ሌሊት በብረት አልጋ ላይ አስተኝተው ከስሩ እሳት በማንደድ መከራ ሊያጸኑበት ወደዱ ዳሩ ግን እግዚአብሔር በላዩ ላይ በፈጸመው ተአምራት ምንም ጉዳት ሳያገኘው ደህና ሆኖ በማየታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመን አዘንብለዋል። እርሱም ዝንባሌአቸውን ተመልክቶ ስለአስተማራቸው በትምህርቱ አምነው ተጠምቀዋል። ቅዱሳን ለከዊነ እሳት ማዕርግ ሲደርሱ እንደ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ፊታቸው በጸጋ ተሞልቶ እንደ ፀሐይ ያበራሉና። (ዘፀ . ፴፬ ÷፳፺–፴፭)

በመጨረሻም በይሁዳ ሲያስተምር ከኖረ በኋላ፤ ፊላዎን በተባለች ቦታ ሸምግሎ፣ ዕድሜም ጠግቦ፣ ብዙዎችንም ከክህደት ወደ አማኒነት መልሶ፣ አጥምቆ፣ ቤተክርስቲያን አሣንጸላቸው በክብር አርፏል::

ዶ/ር ሥርግው ኃብለ/ሥላሴ ባዘጋጁት የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት እንደተጻፈውም ማትያስ በሰይፍ ና በሰማዕትነት አርፎአል:: በዚህም ምክንያት በአውሮፓ የአናጺዎችና የሥጋ ቤት ሰራተኞች ተራዳኢ ሐዋርያ እንደሆነ ይታመናል:: ይህም የነሱን እምነት ለመግለጽ ያህል እንጂ የቅዱስ ማትያስ አማላጅነትና አባትነት ለአናጺዎችና ለሥጋ ቤት ሠራተኞች ብቻ ነው ለማለት አይደለም:: የጻድቃን ደሴትና የቅዱሳን ሀገር ኢትዮጵያም አክብራ ትቀበለዋለች በአማላጅነቱም ታምናለች:: የላይኛው አባባል ግን ቅዱስ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ እንደሚባለው ዓይነት ነው:: የማትያስ አጽም በሮም ከኖረ በኋላ፤ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ንግሥት እሌኒ በዚያን ጊዜ የሮም ቄሣሮች መኖሪያ ከተማ ወደነበረው ወደ ትሬር እንዲመጣ አድርጋለች:: ትሬር በጀርመንና በኢጣሊያ መካከል የሚገኝ ጥንታዊ ከተማ ነው:: የሐዋርያው ማትያስ አጽም በቤኔዲክት ገዳም በስሙ በታነጸው ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛል በምዕራብ ጀርመንየሚገኙ ትሬር፣ ጎስላር፣ ሄልድሻይምና ሃኖቨር የተባሉት ከተማዎች የሚራዳቸው ሐዋርያ በማድረግ ይቀበሉታል። በዓለ እረፍቱም በቤተክርስቲያናችን ስንክሳር እና በግጻዌው እንደተሠራው መጋቢት ፰ ቀን ይከበራል::

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ቅዱስ ማትያስ ጌታውን ለ፴ ብር በሸጠው በይሁዳ ምትክ መንፈስ ቅዱስ መርጦት የቤተክርስቲያን አባቶች ሐዋርያት ሹመውታል:: ይሁዳንም ይሁዳ ወለውሉደ ውሉዱ ይደምስስ" እያልን ድምጻችንን እንድናሰማ ቤተክርስቲያን ታዘናለች::

ዛሬስ በቤተክርስቲያናችን ስንት ይሁዳዎች አሉ? ይሁዳ ከመጀመሪያ "ጌታውን ለ፴ ብር ይሸጣል አባቱን ይገድላል እናቱን ያወስባል ተብሎ ትንቢት የተነገረበት ሲሆን በኋላም ጌታችን መርጦት ሲከተለው፤ ሌብነቱንና ከጌታው ይልቅ ገንዘብን መውደዱን አልተወም:: ማርያም እንተ ህፍረት ጌታዋን ውድ ዋጋ በሚያወጣ ሽቶ እግሩን ብትቀባው ይህ ሽቶ ተሸጦ ለድሆች ቢሰጥ መልካም ነበር ሲል ከአንጀቱ የሌለውን ርኅራኄ በሽንገላ ቃሉ ተናገረ:: የማርያም እንተ ህፍረትም ሠናይ ምግባር መንግሥተ ወንጌል በሚነበብበት አደባባይ ሁሉ ሲነገር ይኖራል:: ዛሬም በቤተክርስቲያናችን እንደ ይሁዳ የበሉበትን ወጭት ሰባሪዎች የእናት ጡት ነካሾች ቅዱሳንን እየነቀፉ ራሳቸውን ሰውረው እየማሉና እየተገዘቱ የዚህች የሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቤተክርስቲያን አባል ለመምሰል ይሞክራሉ።

ለመሆኑ የቅዱሳን ክብራቸው መድኃኔዓለም እንደሆነና ቅዱሳንን የሚያዋርድ ከሰይጣን መሆኑን አልተረዱት ይሆን (ራዕ.፲፫÷፮) ቤተክርስቲያን በእናትነቷ ከፊደል ጥናት ጀምሮ እስከ ትልቅ ማዕረግ እንጀራዋን አብልታ አጠጥታ በእውቀት ኮትኩታ አሳድጋው የራሷ የነበረ በውስጧ ያለውን ሥርዓት ተምሮ ያደገ ሣይሆን እንዲሁ ተጠግቷት በላይዋ እንደመዥገር ተጣብቆ ያደገ ሲክዳት ዝም የሚል አንጀት የላትም እያወገዘች እየለየች ወደፊት ትጓዛለች::

የቤተክርስቲያን ታሪክ ማለት ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ፤ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ያላቸው ቅዱሳን፤ በደማቸውና በአጥንታቸው የጻፉትና ያቆዩልን ታሪክ ነው::

በመሆኑም ቤተክርስቲያናችን ለቅዱሳን ሐዋርያት የምትሰጠው አክብሮት ታላቅ ነው። ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን ቀዳማውያን አበው ሲሆኑ ሥለ ቅድስት ቤተክርስቲያን ክብር የተሠውናቸውና ልዩ ክብር ትሰጣቸዋለች። ለምሳሌ ገድላቸውን በመመስከር፣ ትምህርታቸውን ሳታዛባ በመጠበቅና፣ በዓላቸውን በማክበር፣ በስማቸው ሕንፃ ቤተክርስቲያን በመሰየምና በስማቸው በመጥራት፣ ስዕላቸውን በማክበርና፣ በአማላጅነታቸውም በማመን ታስተምራለች:: የነርሱንም አሰረ ፍኖት ትከተላለች በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋልና ተብሎ የተጻፈውን ትፈጽማለች:: (ኤፌ. ፪÷፳)

እንግዲህ ከማኅበረ ሐዋርያት ይሁዳ፣ከማኅበረ ሊቃውንት አርዮስ፣ ንስጥሮስና ሌሎችም፣ ከማኅበረ መላእክት ዲያብሎስ እንደተለየ (ራዕይ ፲፪÷፯–፱) ወደ ፊትም የእኛ ያልነበሩ ግን እኛን መስለው የወይኑን ቦታ የሚያበላሹ ጥቃቅን ቀበሮዎች በየጊዜው ቢነሱ አይደንቀንም፤ በይሁዳ ላይ ያደረ ዲያብሎስ በልባቸው አድሮአልና::(ዮሐ.፲፯÷፲፪፣ ራዕይ ፪÷፲፭) የቤተክርስቲያን አምላክ ክርስቶስ ግን ሺህ ይሁዳዎች ቢክዱት ሺ ማትያሶችን ያስነሳል (ይመርጣል)።

በአሁኑ ወቅት ስለ ወይኑ ግንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፣ ትንሣኤና ምፅአት በሚገባ በማስተማሯና ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የመስቀሉን ቃል ማለትም እንከን የሌለበት ወንጌልን በተግባር ከፈጸሙት ሐዋርያት ልጆች ገድል ጋር በወይን ሐረግ የተመሰለች የድንግል ማርያምን ክብርና አማላጅነት ስለ መሰከረች ዙሪያውን እንደአሸን ፈልተው እያደቡ ይገኛሉ::

ይሁን እንጅ ዛሬም እንደትናንቱ እናት ቤተክርስቲያናችንን በጊዜአዊ ጥቅም ከሚሸጧትና የውስጧን አንድነት ለማናጋት ዙሪያውን ከሚጎሸሟት ነቅተው በመጠበቅ ይሁዳዎች መናፍቃን የቅድስት ቤተክርስቲያናቸውን ክብር ለጥቅም አሣልፈው የማይሰጡ እንደሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ ከመንጋው የማይለዩና በአባቶቻቸው የቀናች ሃይማኖት በሚጓዙ ውድ ልጆቿ ተከብራ ትኖራ ለች::

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ!

ምንጭ

- ስንክሳር መጋቢት ፰ ቀን
- የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት በዶክተር ስርግው ኃ/ሥላሴ ገጽ ፪፻፰፡-፪፻፯
- ቤተክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ ገጽ ፩፻፬
- ገድለ ሐዋርያት ገጽ ፪፳፯፡-፪፵፯
- The church of our fathers
- Oxford christian church Dictionary

"የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ ይዳረስ ዘንድ ጸልዩልን"

(፪ኛ ተሰ፫÷ ፩).



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሐዋርያት

መጨረሻ ክፍል

## አዕማደ ሃይማኖት

ዓምድ (አዕማድ) ማለት ትክል ምሰሶ ማለት ሲሆን፤ በአንድ ቤት ውስጥ ተተክለው፣ የቤቱን ጣራ ግድግዳና አጠቃላይ የቤቱን አካል በሙሉ ደግፈው፣ ቤቱ ከጊዜ ብዛት እንዳይንጋደድና እንዳይወድቅ ቀጥ አድርገው የሚሸከሙ ምሰሶዎች ናቸው። ዓምደ(አዕማድ) የሌለው ቤት ቶሎ ይወድቃል፤ ቅዱሳን ሐዋርያትም የሃይማኖት ዓምዶች፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች፣ የክርስትና ፈር ቀዳጆች፣ የወንጌሉን ምሥራች ለዓለም አብሣሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ቤተክርስቲያን የእነዚህን ቀዳማውያን አበው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት አድርጋ ለዘለዓለም ስትመሰክር ትኖራለች።

ይህችውም በነቢያት ስትነገር የኖረችና በሐዲስ ኪዳንም በአምላክ ነቢያት ወሐዋርያት በኢየሱስ ክርስቶስ የመነጨች፤ እንደ ወርቅ እየነጠረችና ተስፋ መስቀልን እያበሰረች እዚህ የደረሰችው፤ ምስጢር ገላጭ(ከሣቲ) በሆነው መንፈስ ቅዱስ ኃይል በቅዱሳን ሐዋርያት ምስክርነትና ተአምራት በምእመናን ልቡና ታንጻ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ስለቻለች ነው።

የቅዱሳን ሐዋርያት ታሪክ፣ ገድልና ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሙሉ አልሰፈረም። እንኳን የነሱ የጌታችን ታሪክ እንኳ በሙሉ እንዳልተጻፈ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። (ዮሐ.፳፩÷፴-፴፩፣፳፩÷፳፭) አራቱም ወንጌላውያን እንዴት ለሐዋርያነት እንደተመረጡና እስከ ዕርገት ድረስ የነበራቸውን ሁኔታ ቢጽፉ፤ በሐዋርያት ሥራም ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ስለ ቤተክርስቲያን ጉዞ በስብከት መልክ በንቅዱስ እስጢፋኖስ፣ ጴጥሮስ እና ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የነበሩበትን ሁኔታ ቢብራራና ባጭሩ ቢጻፍም፤ ስለሐዋርያት ሙሉ ታሪክ አይገልጥም።

ከዚህ በተጨማሪ ያለውን የሐዋርያት ታሪክ ለማወቅ ግን ዋናው ምንጩ የቤተክርስቲያን የታሪክ መጻሕፍት ናቸው። የሐዋርያት ደቀመዛሙርት(Successurs of the apostles) ወይም ሐዋርያውያን አበው ተብለው የሚጠሩ፤ እነ ፓፒየስ ፖሊካርፐስ አግናጥዮስ(ምጥው ለአንበሳ) ቀሌምንጦስ ዘሮም ወዘተ የአባቶቻቸውን ታሪክ ጽፈው አቆይተውልናል። በኋላ ጊዜም በ፪ኛውና በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱት የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍት እነ አውሳብዮስ ሩፊኖስ፣ ጀሮም ወዘተ በትውፊት የተጠቀሱትን መዝግበው አልፈዋል። ገድላቸውና ስንክሣርም ጥሩ ምንጭ በመሆኑ ከነዚህ መጻሕፍት በመመሥረት ከመለከት ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፭ እስከ ፱ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ማለትም ለዚህ የመጨረሻ ክፍል ደርሰናል። እንደሚታወቀውና ከታሪካቸው እንደተማራችሁት ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተክርስቲያን ቀዳማውያን አበው ስለ ቅድስት ቤተክርስቲያን የተሠው ሕይወታቸውን ለቤተክርስቲያን የሰጡ በመሆናቸው በቤተክርስቲያን ልዩ ክብር አላቸው። በልዩ ልዩ መልክም ታከብራቸዋለች። ይኸውም:-

### ሀ) ትምህርታቸውን ሳታዛባ በመጠበቅ

ብዙዎች በልዩ ልዩ ዘመን ከእውነተኛው ትምህርተ ሐዋርያት አፈንግጠዋል። በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በሲሞን መሰርይ መሥራችነት ከተነሱት ግኖስቲኮች ጀምሮ በኋላ ዘመን እስከተነሱት አርዮሳውያን፣ መቅዶንዮሳውያን፣ ሰባልዮሳውያን፣ ንስጥሮሳውያን፣ መሐመዳውያንና ልዩናውያን ድረስ ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተክርስቲያን ያቆየችላቸውን ትምህርተና ትውፊተ ሐዋርያት፣ ትተው በገዛ ፍልስፍናቸውና ምኞታቸው ሲመሩ ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን የሐዋርያትን ትምህርትና ትውፊት ጠብቃ እስከዛሬ ኖራለች በዚህም ሐዋርያዊት ትባላለች።

### ለ) ገድላቸውን በመመስከር

አበው ሐዋርያት የክርስትና ኑሮ ፋና ወጊዎች በመሆናቸው፤ ከከሃድያን፣ ከመናፍቃን፣ ከአረማውያን፣ ከትዕቢተኞች ነገሥታት ከዲያብሎስ አሽከላና የግብር ልጆቹ ጋር ተጋድለው በደማቸው ቀለም በአጥንታቸው ብዕር ነው ክርስትናን የጻፉት። ጽፈውም ብቻ ሳይሆን በተግባር ኑረው ጣዕሙን ቀምሰው አሳይተውናል። በሹክሹክታ የተማሩትን በጩኸት፣ በጨለማ የተማሩትን በብርሃን፣ በቤት ውስጥ የተማሩትን በአደባባይ ገልጠውታል። በዚህ ጊዜም ጨለማ የሰፈነበት ዓለም፤ የወንጌልን ብርሃን መቀበል ተስኖት ፍዳ መከራ አብዝቶባቸዋል። ይህ ያደረጉት ተጋድሎ ዛሬ በቤተክርስቲያን ታሪክ፣ በቅዱሳኑ ገድል ተዘግቦ ይገኛል።

ጽፎ መረከብ ማስተማርም ብቻ ሳይሆን፤ በእግራቸው የተተኩ አበው ሊቃውንቱም መንገዳቸውን ተከትለውታል። ዛሬም ቅድስት ቤተክርስቲያን የሐዋርያትን ተጋድሎ ለትውልድ ሁሉ ትመሰክረዋለች። እውነተኛ ልጆቿም አሰረ ፍኖታቸውን እንዲከተሉ ታስተምራለች። ልጆቿም የሚበልጠውን ተስፋ ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከሞት ድረስ ተደበደቡ። ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ በእሥራትና በወህኒ ተፈተኑ። በመጋዝ ተሰነጠቁ። በሰይፍ ተገድለው ሞቱ። ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ። "ዓለም አልተገባቸውምና (አልተቀበላቸውምና) በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ (ግበበ ምድር) ተቅበዘበዙ" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ (ዕብ. ፲፩÷፴፰) ስለ ወንጌል ክብር ስለ ርትዕት ሃይማኖት የተሰው የቤተክርስቲያን መልካም መዓዛ የሆኑ ሐዋርያትን ገድል በተግባር ያውሉታል (ራዕ. ፯÷፱-፲፩)

### ሐ) በዓላታቸውን በማክበር

ቅድስት ቤተክርስቲያን የቅዱሳን ሐዋርያት የሰማዕትነታቸውን የቅዱስ ዮሐንስን ልደቱን ታከብራለች። እርሱ ሳይሞት ወደ ብሔረ ሕያዋን ስለተወሰደ የተወሰደበት ይከበራል (ዮሐ.፳፩÷፳፪) የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነውና ይህ የሐዋርያት በዓል ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጀምሮ ይከበር ነበር።

የሰርምኔሱ ሊቀ ጳጳስ ፖሊካርፐስ ሐዋርያት በሰማዕትነት ያረፉበት በዓል በጥንታውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ይከበር እንደነበር በ፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ዘግቦ ነበር። (Dictronary of sains.P.8) የቅዱሳን ሐዋርያት መታሰቢያ በዓል እጅግ የከበረ ስለመሆኑና ልናከብር እንደሚገባ፤ በመጽሐፈ ሲኖዶስ ስለ በዓላት በሚናገረው አንቀጽ ፲ ላይ "አዕርፉ በዕለተ በዓሎሙ ለሐዋርያት እስመ እሙንቱ መምህራኑ ትእዛዘ ክርስቶስ ወመላብዋን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ።" "በሐዋርያት በዓል ቀን ዕረፍት አድርጉ። እነርሱ የክርስቶስን ትእዛዝ ያስተማሩና ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ያስረዱ ናቸውና።" ተብሎ ተደንግጓል። ይህን ምክንያት በማድረግ ቤተክርስቲያናችን በሐዋርያት በዓል ቀን ልዩ ልዩ መንፈሳውያት ተግባራትን ትፈጽማለች። በቤተክርስቲያናችን የበዓላት ቀኖና መሠረት፤ የቅዱሳን ሐዋርያት በዓል የሚከበርበት ዕለት እንደሚከተለው ነው።

፩. ጴጥሮስ ሐምሌ ፭
፪. ሐዋርያው እንድርያስ ታኅሣሥ ፬
፫. ሐዋርያው ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ሚያዝያ ፲፯
፬. ዮሐንስ ወንጌላዊ መስከረም፬ (ልደቱ)
፭. ሐዋርያው ፊልጶስ ኅዳር ፲፰
፮. በርተሎሜዎስ መስከረም ፩
፯. ሐዋርያው ቶማስ ግንቦት ፳፯
፰. ሐዋርያው ማቴዎስ ጥቅምት ፲፪
፱. ሐዋርያው ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ የካቲት ፲
፲. ስምዖን ቀነናዊ(ናትናኤል) ግንቦት ፲፭
፲፩. ታዴዎስ ሐምሌ ፪
፲፪. ሐዋርያው ማትያስ መጋቢት ፰

### መ) ለስማቸው መታሰቢያ ሕንፃ ቤተክርስቲያን በመሰየም

አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ ቃል "ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦቹ በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ።" (ኢሳ.፶፯÷፬) ብሎ ለቅዱሳን ልጆቹ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ዛሬ በቤተክርስቲያን ጽላት ተቀርጾላቸው በስማቸው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ተሠርቶላቸው ይከበራሉ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሠ) በስማቸው በመጠራት

ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተክርስቲያን መሠረት የክርስትና እምነት ፋና ወጊዎች በመሆናቸው ዘወትር ሊታሰቡ ይገባል። በመሆኑም በክርስቲያኖች ዘንድ ክርስትና ከተነሱበት ዕለት ጀምሮና በሐዋርያት ወንበር የሚሾሙ ጳጳሳትን በሐዋርያትና በሌሎችም ቅዱሳን ስም መሰየም ትውፊታችን ነው። (የሐ.፩÷፵፩-፵፫፤ማቴ.፲፯÷፲፭፤ማር.፫÷፲፯-፲፯፤ሉቃ.፯÷፲፬፤የሐ.ሥራ ፱፤፲፫÷፱)

## ረ) ሥዕላቸውን በማክበር

ከጥንቱ የኪታኮምብ (ግበበምድር) ቤተክርስቲያን ጀምሮ በቅዱሳን ሐዋርያት ሥዕል ለሥርዓተ አምልኮ (ለጸሎት፣ለምልጃና፣ለምስጋና) መጠቀም የቤተክርስቲያን ሥርዓት ነው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የቅዱሳን ሐዋርያት ሥዕል በየአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ ይገኛል። ምዕመናንም አስቀድመው የልብሳቸውን ዘርፍ እየነኩ በጥላቸው ላይ እየተኙ ይፈወሱ እንደነበሩት ሁሉ (የሐዋ. ፭÷፲፭፣፲፱÷፲፩) ዛሬም ሥዕላቸውን እየዳሰሱ ድህነተ ሥጋ ድህነተ ነፍስ ያገኙበታል።

## ሰ) በአማላጅነታቸው በመታመን

የቅዱሳን አማላጅነት በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና በቤተክርስቲያን ታሪክ በልዩ ልዩ ቦታዎች ተገልጦ ይገኛል። በዚህም መሠረት የቅዱሳን ሐዋርያት አማላጅነትም ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጀምሮ የታወቀ የታመነም ነው። ከቅዱሳት መጻሕፍት በተጨማሪም በሮማ መንግሥት ጭካኔ የተነሳ በግበበ ምድር ለመኖር የተገደዱት ጥንታውያን ክርስቲያኖች "ጳውሎስና ጴጥሮስ ሆይ ድል እናገኝ ዘንድ ጸልዩልን" ብለው የተናገሩት ተገኝቷል። (Dictronary of sains.P.8)

የቅዱሳን ሐዋርያት አማላጅነት በሐዲስ ኪዳን ግልጽ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ ተገልጾአል። ለምሣሌ ከነናዊቷ ሴት ልጇ በክፉ ጋኔን ተይዛ ብትሰቃይባት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሄዳ ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ማረኝ እያለች ስትከተለው፤ ጩኸቷን እንዳልሰማ መስሎ አንዳች ሳይመልስላት ሄደ። በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ቀርበው በኋላችን ትጮሃለችና አሰናብታት እያሉ ለመኑት። እርሷም በትህትናዋ፣ በጽኑ ሃይማኖቷና በትእግስቷ፤ቅዱሳኑ ተጨነቁላትና ጩኸቷን ወደ ጌታችን አሳሰቡላት።አሰናብታት (እዘንላት) በማለት ስለ አማለዷትም የታመመችው ልጇ ተፈወሰች።(ማቴ.፲፭÷፳፩–፳፰)

ከመጀመሪያም ዝም ብሎአት መሄዱ የሐዋርያትን አማላጅነት ሊያስተምርባትና የንጉሥ ክርስቶስ ባለሟሎች ግዳጅ ፈጻሚዎች መሆናቸውን ሊገልጽ ፈልጎ እንጂ፤ ጆሮን የሰራ አምላክ የማይሰማ ሆኖ አይደለም። ልብ ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ሁሉ ያውቃል። ስለዚህም አስረጂ ቅዱስ ዳዊት አንተ ተአምር ኩሎ ጎሊና ልብየ እምርሑቅ "የልቡናዬን ሐሳብ ሁሉ ሳይታሰብ አስቀድሞ አንተ ታውቀዋለህ።" በማለት ገልጾታል።(መዝ.፻፴፰÷፪)

በተዘጋ ቤት ውስጥ በር ሳይከፈት ገብቶ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን በማለት ለደቀመዛሙርቱ መገለጹም፤ ለባህርያዊ ጥበቡ ወሰን የሌለው ሁሉን የሚያውቅ፣ሁሉም ቦታ የሚገኝ፣ሁሉን የሚችል፣ ተራራ የማይጋርደው፣ መቃብር የማይወስነው፣ የሕግና የሥርዓት፣ የውስጥና የአፍአ፣ የግዙፋኑና የረቂቃኑ ፍጥረታት ሁሉ አምላክ መሆኑን ያመለክታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ፪ኛ ቆሮ.፭÷፲፯–፳፩ በጻፈው መልዕክቱ "ነገር ግን ሁሉም በክርስቶስ ወደርሱ ከአቀረበን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ የዕርቁን መልእክትም ሰጠን። እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለሙን ዋጅቷልና፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ፣ በደላቸውንም ሳያስብ የዕርቅ ቃሉንም በእኛ ላይ አደረገ፤ የይቅርታውን መልእክትም ሰጠን።እኛ በክርስቶስ አምሳል እንለምናለን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማላጅነት ደስታን ይሰጣችኋል እግዚአብሔርን በክርስቶስ ደስታሰኙት ዘንድ እንለምናችኋለን።ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኛን የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን ያጸድቀን ዘንድ፤ ስለ እኛ እራሱን እንደ ኃጥእ አድርጓልና።" በማለት ከፈጣሪያቸው የራቁትን በጣዕመ ስብከታቸው ወደጌታችን በማቅረብና በአማላጅነታቸው ለምናምን ወገኖች ሁሉ ማገልገላቸውን ገልጿል።

ጌታችንም በማይታበል ቃሉ "እናንተ ደግሞ በ፲፪ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በ፲፪ ዙፋን ትቀመጣላችሁ" "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ" ብሎ ስለተናገረላቸው የተሰጣቸው ቃል ኪዳን(መታሰቢያቸው) እያበራ ግዳጅ እየፈጸመ ለደካሞች ኃይልና ለድውያን ፈውስን ሰላም ለተጠሙ ሰላም በመስጠት አማላጅነታቸው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በነሱና የነሱን ሥልጣን በየዘመናቱ በተረከቡ ካህናት ይቀጥላል። በተሰጣቸውም ሥልጣን በምድር ያስሩት በሰማይ የታሰረ፣ በምድር የፈቱት በሰማይም የተፈታ መሆኑን ልንጠራጠር አይገባም። ለቅድስት ቤተክርስቲያናችን የሃይማኖት መሠረቶች(ዓምዶች) እንደመሆናቸው መጠን፤ በስማቸው አብያተ ክርስቲያናት ታንጸዋል፣ ፅላት ተቀርፆላቸዋል። አማላጂነታቸውም በክብር የታየ፣ በተግባር የተገለጸ ከምዕመናን ልቦና የማይጠፋ ነው።

ዘመኑ ያፈራቸው ሐሰተኞች መምህራን፤ የቅዱሳን ሐዋርያትን ክብርና አማላጅነት ለማስተባበል ብዙ የክህደትና የኑፋቄ መጻሕፍት በነፃ ጭምር በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ።

እኛም እንክርዳዱን ከስንዴ በመለየት የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት በክብር የገለጹትንና ያስተማሩትን ወንጌለ መንግሥት እንደ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በመተርጎም ልናስተምር ይገባል። ለዚህም የሐዋርያት ጸሎትና ምልጃ አይለየን። ዜና ሐዋርያትን ከረጅሙ ባጭሩ እዚህ ፈጽመናል። ከዚህ በኋላ ደግሞ እንደ ራሳችን ሣይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ አርድዕተ ክርስቶስና ስለዓበይት ነቢያት ታሪክ በየተራ ወደፊት በተከታታይ ለማቅረብ አስበናል። ለቀጠሮው ያብቃን ለሁላችንም ምስጢሩን ጥበቡን ይግለጽልን። ያሰብነውን ያስፈጽመን አምላክ ነቢያት ወሐዋርያት አምላክ ጻድቃን ወሰማዕታት አምላክ መላእክት ለነዚህ ሁሉ በገባላቸው ቃል ኪዳን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ይርዳን አሜን።